FSC

Forest Stewardship Council®



# The FSC Interim National Standard of

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

***FSC-STD-XXX-VV-YYYY Description LA***

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጊዜያዊ ብሔራዊ የደን ሀብት አስተዳደር አያያዝና አጠቃቀም መመዘኛ ደረጃ

ለውይይት የቀረበ ረቂቅ ሰነድ

የካቲት 2015

ትርጉም ሥራ ላይ የተሳተፉ አባላት

1. አቶ ተስፋዬ ሁንዴ
2. አቶ ወንድማገኝ በቀለ
3. አቶ ዳኘው ይበይን

FORESTS FOR ALL FOREVER™

All Rights Reserverd FSC® International 2015 FSC® F000100

Standard

# Table of Contents

ለ. አውድ ............ 6

ሐ. ማጣቀሻ ............ 8

መ. የአህጽሮተ ቃላት ዝርዝር............ 9

ረ. የእትም ታሪክ............ 9

ሰ. መርሆዎች፣ መስፈርቶች እና አመላካቾች ............ 9

መርህ* 1፡- ለህጎች ተገዢነት............ 9

መርህ 2፡ የሰራተኞች መብቶች እና የስራ ሁኔታዎች............ 14

መርህ 3፡ የአገሬው ተወላጆች መብቶች ............ 20

መርህ.4 የማህበረሰብ ግንኙነቶች............ 25

መርህ.5 ከደን የሚገኙ ጥቅሞች ............ 31

መርህ* 6 የአካባቢ እሴቶች* እና ተጽእኖዎች............ 36

መርህ* 7: የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ስለማውጣት ............ 46

መርህ* 8: ክትትልና ግምገማ ............ 52

መርህ* 9: ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች* ............ 56

መርህ* 10: የአስተዳደር ተግባራት አፈፃፀም............ 61

ሸ. አባሪዎች............ 72

| | | |
|---|---|---|
| አባሪ ሀ (መርህ 1) | ቢያንስ የሚመለከታቸውን ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የያዘ ዝርዝር | 74 |
| አባሪ ለ | ለሠራተኞች የሚያስፈልጉ ሥልጠናዎች (መርህ 2) | 78 |
| አባሪ ሐ | የጥበቃ ቦታ መረብ /Conservation Arera Network/ ጽንሰ-ሀሳባዊ ንድፍ (መርህ 6) | 79 |
| አባሪ መ | በአገሪቱ ወይም በክልሎች ውስጥ ያሉ ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች ዝርዝር (መርህ 6) | 80 |
| አባሪ ሠ | የደን አያያዝና አጠቃቀም እቅድ መሰረታዊ ነገሮች (መርህ 7) | 82 |
| አባሪ ረ | የዕቅድ እና የክትትል ፅንሰ-ሀሳባዊ ማዕቀፍ (መርህ 7) | 84 |
| አባሪ ሰ | ለክትትል የሚያስፈልጉ ነገሮች (መርህ 8) | 86 |
| አባሪ ሸ (መርህ 9) | ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታ ዋና ቦታዎች የሚመለከቱ አመልካቾችን ለማዘጋጀት ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ | 88 |
| አባሪ ቀ | ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስልቶች (መርህ 9) | 90 |
| አባሪ በ | ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ማዕቀፍ (መርህ 9) | 91 |
| አባሪ ተ | የቃላት ዝርዝር | 121 |

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጊዜያዊ ብሔራዊ የደን ሀብት አስተዳደር አያያዝና አጠቃቀም መመዘኛ ደረጃ**

| | |
|---|---|
| ርዕስ | ጊዜያዊ ብሔራዊ የደን ሀብት አስተዳደር“ አያያዝና አጠቃቀም መመዘኛ ደረጃ |
| የሰነድ ማጣቀሻ ኮድ | FSC-STD-XXX-VV-YYYY Description LA |
| ያለበት ሁኔታ | ለማህበረስብ ዉይይት የቀረበ ረቂቅ ሃሳብ |
| የተፈፃሚነት ወሰን | ለሁሉም የደን ዓይነቶች |
| የጸደቀበት ቀን | dd month YYYY |
| አስፈፃሚ አካል | ፖሊሲ እና ደረጃ መዳብ ኮሚቴ ወይም የፖሊሲ መሪ ቡድን |
| የታተመበት ቀን | dd month YYYY |
| የሚፀናበት ጊዜ | dd month YYYY |
| የሽግግር ወቅት | 12 ወራት ከሚፀናበት ጊዜ ጀምሮ |
| የጊዜ ገደብ | እስኪ ታድስ፣ በአዲስ እስኪተካ ወይም የሚቋረጥበት ጊዜ |

## 1. መቅድም

### የደን አስተዳደር ምክር ቤት /The Forest Stewardship Council (FSC)/

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካባቢና ልማት ኮንፈረንስ (የምድር ጉባዔ/Earth sumit እ.አ.አ በ 1992 በሪዮ ዴ ጄኔሮ) ከተካሄደ በኋላ እ.አ.አ በ1993 የደን አስተዳደር ምክር ቤት ሲቪል ማህበር / The Forest Stewardship Council A.C (FSC) የተቋቋመ ሲሆን በዓለም ላይ ያሉትን ደኖች ለአካባቢ ተስማሚ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ አስተዳደር የማስፋፋት ተልእኮ የተሰጠው ነው።

FSC በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ዕውቅና እና ለገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ማረጋገጫ ስርዓት ይሰጣል ። ይህ ሥርዓት የምስክር ወረቀት ባለቤቶች በአካባቢ ተስማሚ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚ አዋጭ በሆነ የደን አስተዳደር ውጤት ምርቶቻቸውንና አገልግሎቶቻቸውን ለገበያ እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል። FSC እንዲሁም በFSC መርሆዎች እና መመዘኛዎች ላይ የተመሠረቱ ብሔራዊ የደን አስተዳደር ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ለማዘጋጀት እና ለማፅደቅ ደረጃዎችን ያወጣል። በተጨማሪም FSC የ FSC ዎቹን መስፈርቶች ማሟላታቸውን የሚያረጋግጡ የተስማሚነት ምዘና አሰጣጥ አካላት /conformity assessment bodies (የማረጋገጫ አካላት ተብሎም ይጠራሉ) እውቅና ለመስጠት ደረጃዎችን ያወጣል።

በአካባቢ ተስማሚ የሆነ የደን አስተዳደር የእንጨትና የእንጨት ነክ ያልሆኑ ምርቶች እና የሥነ ምህዳራዊ አገልግሎቶች የደን ብዝሀ ሕይወትን፣ ምርታማነትን እና ሥርዓተ ምህዳራዊ ሂደቶችን እንዲጠብቅ ያረጋግጣል።

ማህበራዊ ጥቅም ያለው የደን አስተዳደር የአካባቢውን ነዋሪዎችም ሆነ አጠቃላይ ህብረተሰቡ በረጅም ጊዜ ጥቅም እንዲያገኙ ይረዳል፤ እንዲሁም የአካባቢውን ነዋሪዎች የደን ሀብቶችን ለመጠበቅ እና የረጅም ጊዜ የአስተዳደር እቅዶችን ለማክበር ጠንካራ ማበረታቻ ይሰጣል።

ከኢኮኖሚ አንፃር አዋጭ የሆነ የደን አስተዳደር ማለት የደን ስራዎች በደን ሀብት፣ በሥርዓተ ምህዳሩ ወይም በተጎዱት ማህበረሰቦች ወጪ የገንዘብ ትርፍ ሳያገኙ በበቂ ሁኔታ ትርፋማ እንዲሆኑ የተዋቀሩ እና የሚተዳደሩ ማለት ነው። በቂ የገንዘብ

ትርፍ የማግኘት አስፈላጊነት እና ኃላፊነት የሚሰማው የደን ሥራ መርሆዎች መካከል ያለው ውጥረት የተሟላውን የደን ምርቶች እና አገልግሎቶች በተሻለ ዋጋ ለገበያ ለማቅረብ በሚደረጉ ጥረቶች ሊቀንስ ይችላል።

## 2. የ FSC መርሆዎች እና መስፈርቶች

FSC ለመጀመሪያ ጊዜ የ FSC መርሆዎችን እና መመዘኛዎችን እ.ኤ.አ በኅዳር 1994 በአፈፃፀም ላይ የተመሠረተ እና በውጤት ላይ ያተኮረ ዓለም አቀፍ ደረጃ አወጣ። መርሆቹና መመዘኛዎቹ ትኩረት የሚያደርጉት የደን አስተዳደርን የመስክ አፈፃፀም ለማምጣት በሚረዱ የአስተዳደር ስርዓቶች ላይ ሳይሆን በመስክ አፈፃፀም ላይ ነው።

በመሠረታዊ መርሆዎች ወይም በመመዘኛዎች መካከል ተዋረድ የለም። እኩል ደረጃን፣ ተቀባይነትን እና ስልጣንን ይጋራሉ፤ በተጨማሪም በእያንዳንዱ ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ እርከን በጋራ እና በተናጠል ይተገበራሉ።

የ FSC መርሆዎች እና መስፈርቶች ከ IGI ጋር በመሆን ለብሔራዊ የደን አስተዳደር ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሄራዊ ደረጃዎች (INS) እድገት መሰረት ይሰጣሉ።

## *ሀ.* መግቢያ

### *ሀ.*1 ዓላማ

የዚህ ደረጃ ዓላማ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማቅረብ ነው፡-

1. ድርጅቱ ለደን አስተዳደር በለየዉ ቦታ ውስጥ ኃላፊነት የሚሰማው የደን አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ እና ተገዢነትን ለማሳየት
2. የFSC እውቅና የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት ሰጪ አካላት (CBs) የደን አስተዳደር የምስክር ወረቀትን ለመስጠት ወይም ለማቆየት እንደ መሰረት ሆኖ የዚህን ደረጃ መሟላት ለመወሰን

### *ሀ.* 2 የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደረጃ በሚከተለው ወሰን ውስጥ ይተገበራል።

| | |
|---|---|
| ጂኦግራፊያዊ ክልል | በፌደራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ |
| የደን ዓይነቶች | ሁሉም የደን ዓይነቶች፣ (ሰው ሠራሽ ደኖች፣ የተፈጥሮ ደኖች የቀርከሃ ደኖችን ጨምሮ) |
| የባለቤትነት ዓይነቶች | ሁሉም የባለቤትነት አይነቶች፡ ማህበረሰብ፣ የግል እና ሌሎችን ጨምሮ |
| መጠን እና ክብደት | ሁሉም ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ምድቦች፣ አነስተኛና ዝቅተኛ የደን አያያዝ መጠን ያላቸዉን ጨምሮ (SLIMFs) (ለዚህ አገር የSLIMF ብቁነት ተፈጻሚነት ክፍል ሐ ይመልከቱ) |
| የደን ዉጤቶች (በFSC-STD-40-004a መሰረት) | እንጨት፣ የእንጨት ነክ ያልሆኑ ምርቶች ፡ (ማር፣ የዱር ቡና (Coffea arabica) ፣ የኢትዮጵያ ረጅም በርበሬ/የአፍሪካ ረዥም በርበሬ (Piper capense) ፣ የኢትዮጵያ ካርዲሞም/ኮራሪማ (*Aframomum corrorima)* |

### ሀ.3 ለትክክለኛነት ኃላፊነት

በዚህ ደረጃ ውስጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ጋር መጣጣምን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት የምስክር ወረቀት አመልካች ወይም ባለቤት የሆነው ሰው(ዎች) ወይም አካላት ናቸዉ። ለFSC ማረጋገጫ ዓላማ እነዚህ ሰው (ዎች) ወይም አካላት እንደ 'ድርጅት' ይባላሉ። ድርጅቱ ከማኔጅመንት ክፍል ጋር በተያያዙ ውሳኔዎች፣ ፖሊሲዎች እና የአስተዳደር ስራዎች ላይ ኃላፊነቱን ይወስዳል።

ድርጅቱ ለሌሎች ሰዎች ወይም አካላት እንዲሰሩ ሲባል በድርጅቱ የተፈቀደላቸው ወይም የተዋዋሉ አካላት በዚህ መስፈርት ከተቀመጡት መስፈርቶች የደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የማሳየት ኃላፊነት አለበት። በዚህ መስፈርት ውስጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ጋር የማይስማሙ ሰዎች ወይም አካላት ካሉ ድርጅቱ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲወስድ ይጠበቅበታል።

### ሀ.4 አመላካቾችን፣ አባሪዎችን እና አረጋጋጮችን አጠቃቀም ላይ ማስታወሻ

<u>በደረጃዎች ውስጥ ያሉ መሰረታዊ ደንቦች</u> የሚከተሉት ናቸው:-

> ወሰን፣ የሚፀናበት ቀንና ጊዜ፣ የቃላት መፍቻ፣ መርሆዎች፣ መስፈርቶች፣ አመልካቾች፣ ሠንጠረዦች (እንዲሁም ከዚህ ደረጃ ጋር ተያይዞ ሊዘጋጁ የሚችሉ ሌሎች ተጨማሪዎች፣ ካለተጠቀሰ በስተቀር)

<u>በደረጃዎች ውስጥ ያሉ መሰረታዊ ደንቦች ያልተከተሉ</u> ግን ለመመሪያ ብቻ ጥቅም ላይ ሊዉሉ የሚችሉ የሚከተሉት ናቸው:-

> ማረጋገጫዎች፣ ማስታወሻዎች፣ መመሪያዎች እና አንዳንድ አመልካቾች ላይ የተያያዙ ምሳሌዎች (እንዲሁም ከዚህ ደረጃ ጋር ተያይዞ ሊዘጋጁ የሚችሉ ሌሎች መመርያዎች/የተግባራዊነት ማስታዎሻዎች)

> <u>በግራጫ ቀለም የተለዩ መሰረታዊ ደንቦች</u> በሀገሪቱ ውስጥ አይተገበሩም ነገር ግን ለግልፅነት ሲባል ደረጃ ውስጥ ይቆያሉ።

እንደ SLIMF (አነስተኛ ወይም ዝቅተኛ የደን አያያዝ መጠን) የሚያሟሉ የደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች የሚያስተዳድሩ ድርጅቶች፣ "ለ SLIMF የማይተገበር" ተብለው ከተገለጹት በስተቀር ሁሉም አመልካቾች መስማማት አለባቸው። የተወሰኑ የSLIMF አመልካቾች ካሉ (ለምሳሌ "SLIMF 3.5.1" የሚል ምልክት የተደረገባቸው)፣ በምትኩ ከላይ ያሉት ድርጅቶች ከእነሱ ጋር መስማማት አለባቸው::

| SLIMF የብቃት መስፈርት | ብሄራዊ ገደብ/ወሰን |
|---|---|
| አነስተኛ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች | እስከ 100 ሄክታር |
| ዝቅተኛ የደን አስተዳደር መጠን ያላቸዉ ቦታዎች | ከአጠቃላይ የደን የምርት ቦታዎች በየዓምቱ የሚሰበሰበዉ መጠን ከአመታዊ አማካይ የምርት ጭማሪ (MAI) 20% ያነሰ ሲሆን፣ እና<br><br>ከአጠቃላይ የደን የምርት ቦታዎች በየዓምቱ የሚሰበሰበዉ ምርት መጠን ከ5000 ኪዩቢክ ሜትር ያነሰ ሲሆን ካልሆነም አማካይ የደን የምርት ቦታዎች በየዓምቱ የሚሰበሰበዉ ምርት መጠን በሪፖርቶች እና በክትትል ኦዲቶች የተረጋገጠው የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ከ5000 ኪዩቢክ ሜትር ያነሰ ሲሆን |

በእውቅና ማረጋገጫ ወሰናቸው ውስጥ የእንጨት ነክ ያልሆኑ ምርቶች (NTFPsን) የጨመሩ ድርጅቶች በደረጃው ውስጥ ካሉ ሁሉም አመልካቾች ጋር ማጣጣም አለባቸው። በተጨማሪም ከላይ ያሉት ድርጅቶች የተለዩ የNTFP አመልካቾች ባሉበት (ለምሳሌ “NTFP 3.5.1”) ማስማማት አለባቸው።

**ድንጋጌዎችን ለመግለጽ የቃል ቅጾች**

[ከISO/IEC *መመሪያዎች* ክፍል 2 የተወሰደ፡ የአለም አቀፍ ደረጃዎችን አወቃቀር እና ማርቀቅ ደንቦች]

**"ይሆናል"**

ከደረጃው ጋር ለመጣጣም በጥብቅ መከተል ያለባቸውን መስፈርቶች ያመለክታል; አይሆንም' ማለት መከልከልን ያመለክታል።

**“መሆን አለበት”፡-**

የሚያመለክተው ከበርካታ አማራጮች መካከል አንዱ እንደሚመከር ይጠቁማል
ሌሎችንም ሳይጠቅሱ ወይም ሳያገለሉ በተለይ ተስማሚ እንደሆኑ ወይም
አንድ የተወሰነ እርምጃ የሚመረጥ ቢሆንም የግድ አስፈላጊ አይደለም ማለት ነው። ድርጅቱ እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት የሚችለዉ ይህንን በተመጣጣኝ መንገድ መረጋገጥና ማስረጃ ማግኘት ሲችል ነዉ።

**"ሊሆን ይችላል"**:

በደረጃው ገደብ ውስጥ የሚፈቀደውን የድርጊት አካሄድ ያመለክታል;

**"አያስፈልግም"**:

የሚያሳየው የተወሰነ የድርጊት አካሄድ መስፈርት እንዳልሆነ ነው።

**"ይችላል"**

የሚያገለግለዉ ለቁስዊ ፣ አካላዊ ወይም ምክንያታዊ ችሎታ እና አቅም መገለጫ አረፍተነገሮች ነዉ፣

በክፍል ‘ረ’ እና ‘ሰ’ ጽሑፍ ውስጥ የቃላት መፍቻ አባሪ ላይ ፍቺ የተሰጠባቸው ቃላቶች በሰያፍ /italic/ ተቀርጾ በኮከብ ምልክት* ተደርገባቸዋል። ይህ ሰነድ በFSC-PRO-60-007 EN መዋቅር፣ ይዘት እና ጊዜያዊ ብሄራዊ ደረጃዎች ላይ እንደተገለጸው ለግምገማ እና ለክለሳ ዑደት ሁል ጊዜ ክፍት ነው።

### ሀ. 5 ትርጓሜዎች እና ዉዝግቦች

ጊዜያዊ ብሄራዊ ደረጃዎችን በሚመለከት የትርጉም ጥያቄዎች ለአፈጻጸም ሂደቱ እና ለማጽደቅ ለFSC በቀጥታ ይቀርባል። የጸደቁ ትርጓሜዎች በአለምአቀፍ FSC ድህረ ገጽ ላይ የታተማሉ (INT-STD-60-006_01 ይመልከቱ) ።

የምስክር ወረቀት መስፈርቶችን በሚመለከት በባለድርሻ አካላት መካከል ያሉ አለመግባባቶች የሚፈቱት በFSC የዉዝግቦች አፈታት ስርዓት ነው። (FSC-PRO-01-008 ይመልከቱ) ።

## ለ. አውድ

### ለ.1 የደን ዘርፍ አጠቃላይ መግለጫ

ኢትዮጵያ አስደናቂ በሆነ የጂኦሎጂ ታሪክ፣ በሰፊው ሰፋ ያለ አካባቢና በከፍተኛ የላቲቱዲናል ስርጭት ላይ የምትገኝ አገር ስትሆን በዓለም ላይ ከሚገኙት ሰፊ ሥነ ምህዳራዊ አካባቢዎች መካከል እጅግ ብዙዎቹን ይዟል። እነዚህ አካባቢዎች ከአፋር ክልል 125 ሜትር ከባህር ጠለል በታች ከሚገኙት ዝቅተኛ ቦታዎች ጀምሮ በሰሜን በኩል ከሚገኘው የራስ ዳሼን ተራራ ጫፎች እና በደቡብ ምስራቅ ከሚገኘው የባሌ ተራሮች ይደርሳሉ። ይህ የተለያየ አካባቢዎች ደግሞ ለሀገሪቱ አጠቃላይ ባዮሎጂያዊ ብዝሃነት አስተዋጽኦ የሚያበረክት የተለያዩ ዝርያዎችን ለማኖር ምቹና ተስማሚ ሁኔታ ለመፍጠር ችለዋል። ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የማይገኙ እንስሳትና እፅዋት ያሏት አገር ናት፤ ነገር ግን እነዚህ እንስሳትና እፅዋት ከመጠን በላይ አከባቢያቸው ከመጠን በላይ በመጠቀሙና በመጎሳቀሉ የተፈጥሮ መኖሪያቸውና ምግብ በማጣት ምክንያት እስከ መጨረሻው ከዓለም ላይ ለመጥፋት አደጋ ተጋርጦባቸዋል።

በFAO የደን ሀብት ምዘና (FRA) ውስጥ የተዘረዘሩት የኢትዮጵያ የደን ሀብቶች የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ኢትዮጵያን ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ከ10 እስከ 30 በመቶ የሚደርስ የደን ሽፋን ካላቸው አገራት መካከል ያስቀምጧታል። በFRA (FAO, 2015) መሠረት የኢትዮጵያ የደን ሽፋን 12.4 ሚሊዮን ሄክታር (11.5 በመቶ) ነው ። ከ1990 እስከ 2010 ባለው ጊዜ ውስጥ በአገሪቱ ውስጥ የእፅዋት ሽፋን ማሽቆልቆል እንዲፋጠን አስተዋፅኦ ከደረጉት ምክንያቶች ከፍተኛ የድህነት መጠን ፣ ከሰው ልጅ ብዛት መጨመር ፣ እንደ ማገዶ ያሉ የደን ምርቶች ፍላጎት እና ከዚያ በኋላ ደኖችን እና የደን ቦታዎችን ወደ እርሻ መሬቶች እና ሰፈሮች መለወጥ ናቸው ። እ.ኤ.አ. ከ1990 እስከ 2000 ባለው ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ የደን መጠን ደንንና ጫካን ጨምሮ(woodland) በ1.4 ሚሊዮን ሄክታር ቀንሷል። እ.ኤ.አ. በ 2005 የደን ሽፋኑ የበለጠ እየቀነሰ እና 13.0 ሚሊዮን ሄክታር እንደሚሸፍን ተገምቷል ። በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያ ከ1990 እስከ 2005 ባለው ጊዜ ውስጥ በአማካይ 140,000 ሄክታር (FAO, 2015) በመጥፋት ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር በላይ ደን አጥታለች። በአሁኑ ወቅት በደን የተሸፈነው ቦታ 12.4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ነው ተብሎ የሚገመተው ሲሆን ይህም ከጠቅላላው የመሬት ስፋት 11.4 በመቶውን ይወክላል። የደን መጨፍጨፍ ዋነኛ ምክንያቶች ለግብርና ዓላማዎች የሚውሉ ደኖችን እና የደን ቦታዎችን ጥርግ አድርጎ መመንጠር፣ የማገዶ እንጨት ፣ የከሰል ምርት እና የግንባታ ቁሳቁሶች ናቸው። ሰው ስሠራሽ ደን የሀገሪቱን የእንጨት ፍላጎት ከማሟላት በጣም የራቀ በመሆኑ የደን መጨፍጨፍ የማይቀር መሆኑን ያመለክታል። የደን መጨፍጨፍ ዋነኛ መንስኤዎች እንደ ድህነት፣ የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ደካማ የኢኮኖሚ እድገት እና የአካባቢ ሁኔታ የመሳሰሉ እርስ በእርስ የሚጠናከሩ ምክንያቶች ከሚፈጥሩት አስከፊ ዑደት ጋር የተቆራኙ ናቸው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ችግኝ በመትከል ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፏል። ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በመላ ሀገሪቱ የችግኝ ተከላ ዘመቻው በየዓመቱ ሲካሄድ የቆየ ሲሆን የደን ሽፋን እየጨመረ መምጣቱን የመንግስት መረጃ ያመለክታል። ከ2010 እስከ 2015 ባለው ጊዜ ውስጥ የደን ቦታ መጨመሩን ተመዝግቧል። በዓመት 40 000 ሄክታር እንደሚጨምር ይገመታል (FAO ፣ 2015) ። የሀገሪቱን የደን ሀብት ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ በቁጥር 80 የሚጠጉ እና በአጠቃላይ 26 879.15 ኪ.ሜ ስኳር ስፋት ያላቸውን ጥብቅ የደን ቦታዎችን አቋቁማለች።

ኢትዮጵያ የደን ምርት ለአካባቢው ኑሮና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም ነገር ግን በአብዛኛው አልተመዘገበም፤ በዚህም ምክንያት እውቅና አላገኘም። የደን ሀብቶች በኢትዮጵያ ከፍተኛ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ሥነ ምህዳራዊ ጠቀሜታ ካላቸው በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ናቸው። ደን ሀብቶች አስፈላጊነትና በብዝሃ ህይወት፣ በስነ-ምህዳር አገልግሎቶች እና በሰዎች ደህንነት መካከል ያለውን ትስስር በተመለከተ ግንዛቤ እያደገ መጥቷል (EFS፣ 2014)። የኢትዮጵያ ደኖች የገጠርን አኗኗር የሚደግፉ NTFPsን ጨምሮ የስነ-ምህዳር አገልግሎት ምንጮች ቢሆኑም ተገቢውን ትኩረት አልተሰጣቸውም። በኢትዮጵያ ለገጠር ቤተሰቦች ከፍተኛ ገቢ እና የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያስገኙት በጣም አስፈላጊዎቹ NTFPs ቡና፣ ማር እና የተፈጥሮ ጋም እና ሙጫዎች ናቸው። ኢትዮጵያ ብሔራዊ የጥበቃ ስትራቴጂ አላት (EPA,1997) እና የአካባቢ ፖሊሲን በ1997 አወጣች። እንዲሁም የክልል መንግስታት የራሳቸውን "የክልል ጥበቃ ስትራቴጂዎች" አዘጋጅተዋል፣ የትግራይ፣ የአፋር፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የሶማሌ፣ የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ የጋምቤላ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስታትን ጨምሮ።

በኢትዮጵያ ከ2005 እስከ 2010 ባለው ጊዜ ውስጥ አጠቃላይ የእንጨት ምርት ከ100 718 ወደ 107 943 ሺህ ሜትር ኩብ (m3) አድጓል ። ከጠቅላላው የእንጨት ምርት 97 በመቶ ገደማ የሚሆነው እንጨት ለማገዶና ለከሰል ምርት ሲሆን ቀሪው 3 በመቶ ለግንባታና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ናቸው። በኢትዮጵያ የደን ምርቶች በተለያዩ ንዑስ ዘርፎች የተከፋፈሉ ሲሆን እያንዳንዳቸው ለጠቅላላው ብሔራ ምርት (GDP) ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። እነዚህ ንዑስ ዘርፎች ሙጫ፣ ማር፣ የዛፍ ዘርና ችግኝ፣ የጫካ ቡና፣ ቅመማ ቅመም፣ የቀርከሃ፣ የእንጨትና የመድኃኒት ተክሎች ናቸው። እንጨት ለግንባታ፣ ለቤት እቃዎች እና ለከሰል ምርቶች ዋና የጥሬ ዕቃ ምንጭ ነው። የኢትዮጵያ ደኖችና ጫካዎች ለበርካታ የቤት እንስሳት እና/ወይም አስፈላጊ የዱር እፅዋት እና የቤት እንስሳት የዱር ዘመዶች ማከማቻዎችና የጂን ክምችት ምንጭ ናቸው። ለምሳሌ ቡና (Coffee arabica) በሀገሪቱ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ በሚገኙ እርጥብ አረንጓዴ ተራራማ ደኖች ውስጥ ይገኛል። የደን መጨፍጨፍ፣ የእንስሳትና የእፅዋት መኖሪያ አካባቢቦታዎች ውድመት እና የተፈጥሮ ደን ዳግም ብቅለት መቀነስ፣ የደን ቃጠሎ እና የእጽዋትን መመንጠር ለእርሻና ለመኖሪያ ቦታዎች ለከፍተኛ ስጋት ተጋርጦበታል። ስብጥር የደን ልማት (አግሮፎረስትሪ) እና ከመሬት እና ከዛፍ ባለቤትነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች እና ህጎች አለመኖሩም ለፍራፍሬዎች እና ለሌሎች የጄኔቲክ ሀብት መሸርሸር አስተዋጽኦ አድርጓል ።

በጠቅላላው 277 አጥቢ እንስሳት ዝርያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገኙ ይታወቃል። ከእነዚህ ውስጥ 29 ቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ዝርያዎች ናቸው። ዋሊያ አይቤክስ (ካፕራ ዋሊ) ፣ ጭላዳ ባቡን (ቴሮፒቴከስ ጭላዳ) ፣ ተራራ ኒያላ (ትራጌላፉስ ቡክቶኒ) ፣ የኢትዮጵያ ተኩላ (ካኒስ ሲመንሲስ) ፣ ስታርክስ ሃሪ (ሌፐስ ስታርክኪ) ። ከእነዚህ አደጋ ላይ የሚገኙ ዝርያዎች መካከል አንዳንዶቹ በጣም የተገደቡ ቦታዎች ብቻ የሚኖሩ ናቸው፤ ከእነዚህም መካከል ዋሊያ አይቤክስ የተባለው በዓለም ላይ በጣም አደጋ ላይ የወደቀ አጥቢ ዝርያ ነው።

ኢትዮጵያ በጠቅላላው 861 ዝርያዎች (ከአፍሪካ አጠቃላይ 40%) ያሉት የበለፀገ የአእዋፍ ዝርያዎች አሏት ። ከጠቅላላው 29 ቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ (ኤንዴሚክ) ናቸው ። 16 ቱ በኢትዮጵያ ጂኦግራፊያዊ ድንበር ላይ ብቻ የተገደቡ ሲሆኑ 13 ቱ ከኤርትራ ጋር የተጋሩ ናቸው ። የሃርትውድ ፍራንኮሊን ፣ ፕሪንስ ሩፖሊስ ቱራኮ ፣ ታላቁ ነጠብጣብ ንስር ፣ አነስተኛ ካስትል ፣ ቢጫ አንገት ያለው ሴሪን ፣ የቅርብ ሌሊት ጃር ፣ ዋትልድ ክሬን ፣ ዲጎዲ ላርክ ፣ ነጭ ጅራት ስዋውላ ፣ ሲዳማ ረዥም ክላቭ ላርክ ፣ ላፔት-ፊት ቫልቸር ፣ አቢሲኒያን ቡሽ ፣ ኮርኒከሬክ እና ኢምፔሪያል ንስር ጨምሮ ለጥፋት የተጋለጡ 14 የወፍ ዝርያዎች አሉ ። 16 ዝርያዎች ለከፋ አደጋ የተጋለጡ ናቸው። የኢትዮጵያ የንጹህ ውሃ አካላት ከ180 በላይ የዓሣ ዝርያዎች እንዳሏቸው ይታወቃል። ከእነዚህ ውስጥ ከ37-57 የሚሆኑት በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ (ኤንዴሚክ) እንደሆኑ ተገልጿል (በተጨማሪው ሰንጠረዥ 8 ተመልከት) (Golubstov and Mina, 2003) ። የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ከ25 በላይ የዓሣ ዝርያዎች ያሉት ሲሆን ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ የዓሣ ምርት 50 በመቶውን ይይዛል። እንዲሁም በጣም አስፈላጊና ለንግድ ጠቃሚ የሆኑት የዓሣ ዓይነቶች ቲላፒያ፣ ናይል ፔርች እና ካትፊሽ እንደሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል።

ነፍሳትን ጨምሮ የኢትዮጵያ አርትሮፖድ እንስሳት እምብዛም አይታወቁም። ብዙ ነፍሳት ለሰው ልጆች በጣም ጠቃሚ ናቸው። የእጽዋት የአበባ ዘርን በማዳቀል ከፍተኛ ሚና ስለሚጫቱ፥ በመሆናቸው እና በአብዛኛዎቹ ማህበረሰቦች ውስጥ በምግብ

ሰንሰለት ውስጥ መካከለኛ ቦታዎችን ስለሚይዙ ለሰው ልጅ ትልቅ ጥቅም አላቸው። አንዳንዶቹ ለሰዎችና ለቤት እንስሳት በሽታ የሚያስተላልፉ በመሆናቸው ጎጂ ናቸው። ነፍሳት በንጹህ ውሃ ውስጥ የበላይ ናቸው፤ እናም በምድር ላይ ሊታሰቡ የሚችሉትን ሁሉንም መኖሪያ ቦታዎችን ይይዛሉ። ነገር ግን፣ የነፍሳት ሥርዓተ-ምህዳሮች በሰፊው በሶስት ዋና ዋና ሥርዓተ-ምህዳሮች ሊከፈሉ ይችላሉ፣ እነሱም የውሃ ውስጥ ሥርዓተ-ምህዳር፣ አግሮ-ሥርዓተ-ምህዳር እና የደን ሥርዓተ-ምህዳር ናቸው። አብዛኛዎቹ ሁሉም ማለት ይቻላል የነፍሳት ዝርያዎች ከጫካ ሥርዓተ-ምህዳር ጋር የተቆራኙ ናቸው።

ከ277 አጥቢ እንስሳት 29፣ ከ862 አእዋፍ 16፣ ከ201 በደረት የሚሳቡ እንስሳት 10፣ እና ከ63 አምፊቢያን 34ቱ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ናቸው። ከአእዋፍ ዝርያዎች ውስጥ 31ቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስጋት አለባቸው; ከእነዚህ መካከል 5ቱ በአደገኛ ሁኔታ ላይ ያሉ፣ 12 ቱ ለአደጋ የተጋለጡ እና 14ቱ ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች ተመድበዋል። በአለም አቀፍ ደረጃ ለአደጋ ተጋልጠዋል ተብለው የሚታሰቡ የተለያዩ ፍልሰተኛ/ስደተኛ አእዋፍ በኢትዮጵያ በየዓመቱ ወደ ሃምሳ የሚጠጉ ቦታዎችን ይጎበኛሉ ወይም ያርፋሉ። የተጠበቁ አካባቢዎች ዋነኛ ስጋት የሚመነጨው በፓርኮች ውስጥ ወይም በአቅራቢያቸው ካለው ሰፈራ፣ከእርሻ ልማት፣ከግጦሽ፣ከደን መጨፍጨፍና ከማዕድን ማውጣት ነው።

### ለ. ለደረጃ ማውጣት መነሻ ሃሳብ

(እዚህ ይዘት ለመጨመር)

## ሐ. ማጣቀሻ

የሚከተሉት የማጣቀሻ ሰነዶች ለዚህ መስፈርት አተገባበር አስፈላጊ ናቸው። የስሪት ቁጥር ለሌላቸው ማጣቀሻዎች፣ የተጠቀሰው ሰነድ የቅርብ ጊዜ እትም (ማሻሻያዎችን ጨምሮ) ተፈጻሚ ይሆናል።

FSC-POL-01-004 Policy for the Association of Organizations with FSC

FSC-POL-20-003 FSC Policy on the Excision of Areas from the Scope of Certification

FSC-POL-30-001 FSC Pesticides Policy

FSC-POL-30-602 FSC Interpretation on GMOs: Genetically Modified Organisms

FSC-STD-20-007 Forest Management Evaluations

FSC-STD-30-005 FSC Standard for Group Entities in Forest Management Groups

FSC-PRO-01-008 Processing Complaints in the FSC Certification Scheme

FSC-PRO-30-006 Ecosystem Services Procedure: Impact Demonstration and Market Tools

FSC-DIR-20-007 FSC Directive on FSC Forest Management Evaluations

FSC-GUI-30-003 FSC Guidelines for the implementation of the right to Free, Prior and Informed Consent (FPIC)

FSC-GUI-60-005 Promoting Gender Equality in National Forest Stewardship Standards

**ማሳሰቢያ፡** ይህንን መስፈርት ሲተገበሩ ከአካባቢው የFSC ተወካዮች ጋር (ለምሳሌ ብሔራዊ ቢሮዎች ወይም ተወካዮች፣ ወይም የFSC አፈጻጸም እና ደረጃዎች ክፍል፣ ምንም አይነት ብሄራዊ የFSC መኖር ከሌለ) ጋር በመጠየቅ ተገቢ ትርጉሞችን ያስቡ። ዓለም አቀፍ ትርጓሜዎች በFSC ሰነድ ማዕከል በኩል ይገኛሉ ።

## መ. የአህጽሮተ ቃላት ዝርዝር

(ዝርዝር ለመጨመር እዚህ አማራጭ መጠቀም)

## ረ. የእትም ታሪክ

(ምንም ቀዳሚ የ FSC እትም የሌለው አዲስ ደረጃ)

## ሰ. መርሆዎች፣ መስፈርቶች እና አመላካቾች

### መርህ* 1፡- ለህጎች ተገዢነት

ድርጅቱ ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያከብራል።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

ደረጃ አዘጋጆች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው።

- ልማዳዊ መብቶችን* የማስተዳደር፣ የመጠቀም እና የማግኘት ቦታ ይለያሉ፣ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እነዚህ በሰርተፍኬቱ ወሰን ውስጥ ያሉ ተግባራትን የማከናወን መብቶች መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ አማላካችን ይጽፋሉ (አመልካች* 1.1.1)፤
- ከአጠቃቀም እና ከማግኘት ጋር የትገናኙትን ልማዳዊ መብቶችን ዕውቅና እና ድጋፍ የሚሰጡ ተስማሚ ሂደቶችን ይለያሉ፣ በተጨማሪም ይመዘግባሉ (አመልካች 1.2.1)።
- በአገር አቀፍ ደረጃ ሀብትን ለማስተዳደር እና ለመጠቀም የልማዳዊ ይዞታዎች የት እንዳሉ ይለያሉ እና እነዚህም በአመላካቾች ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣሉ (አመልካች 1.2.1)።

የልማዳዊ መብቶች በመሠረታዊ መርሆች 3 እና 4 ስር ተብራርተዋል።

1.1. ድርጅት የተባለዉ ግልጽ፣ የሰነድ እና የተጣራ ሕጋዊ ምዝገባ ያለው በህጋዊ መንገድ ለተወሰኑ ተግባራት ህጋዊ ስልጣን ካለው ባለስልጣን የጽሁፍ ፈቃድ ያለው በህጋዊ መንገድ የተገለጸ አካል ነው።

1.1.1 በምስክር ወረቀቱ ወሰን ውስጥ ሁሉንም ተግባራት ለማከናወን በሰነድ የተደገፈ እና የማያከራክር ህጋዊ ምዝገባ ያለው ።

NTFP 1.1.1.1 NTFPs በምስክር ወረቀቱ ወሰን ውስጥ ያሉ ተግባራት የተመዘገቡ እና ያልተፋለሱ ናቸው።

1.1.2 ህጋዊ ምዝገባ በህጋዊ መንገድ በተደነገገው ሂደቶች መሰረት ህጋዊ ስልጣን ባለው ባለስልጣን ይሰጣል።

አረጋጋጮች፡-

የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የደን አያያዝና አጠቃቀም እቅድ፣ ከፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የምስክር ወረቀት ወይም በክልል ደረጃ የተቋቋመው የሕብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅን ለማስፈጸም፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሚመራና የሚቆጣጠር አካል ነው።

## 1.2 ድርጅቱ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ህጋዊ ሁኔታ፣ የይዞታ ጊዜ እና የመጠቀም መብቶች እና ድንበሮቹ በግልጽ የተቀመጡ መሆናቸውን ያሳያል።

1.2.1 በምስክር ወረቀቱ ወሰን ውስጥ ያሉ ሀብቶችን የማስተዳደር እና የመጠቀም የይዞታ ባለቤትነት ተመዝቧል።

NTFP 1.2.1.1 ድርጅቱ በምስክር ወረቀቱ ወሰን ውስጥ ያሉና ለክርክር የማይጋለጡ የNTFPs የማስተዳደርና የመጠቀም መብቶችን የሚያረጋግጡ ሕጋዊ የይዞታ ባለቤትነት ወይም ሌሎች ተዛማጅ ማስረጃዎችን ያቀርባል።

1.2.2 ህጋዊ ይዞታ ባለቤትነት የሚሰጠው በህጋዊ መንገድ በተደነገጉ ሂደቶች መሰረት ህጋዊ ስልጣን ባለው ባለስልጣን ነው።

1.2.3 በሰርተፍኬቱ ወሰን ውስጥ ያሉ የሁሉም ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ወሰን በግልጽ ምልክት የተደረገባቸው ወይም የተመዘገቡ እና በካርታዎች ላይ በግልፅ የሚታዩ ናቸው።

1.2.3 ሀ የNTFPs መሰብሰብ የሚካሄድበትን መሬት ህጋዊ ድንበሮችን በግልፅ የሚያሳይ ካርታ ይገኛል።

አረጋጋጮች፡-

የሊዝ ውል፣ የመሬት ኪራይ ውል፣ የመሬት ስጦታ ስምምነት፣ የመሬት ይዞታ ሰርተፍኬት፣ ቀበሌ (የክልል መንግስት) ፣ ካርታዎችና የመሬት አጠቃቀም ፕላኖች፣ ካርታዎች ።

1.3 ድርጅቱ* ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ ለመሥራት ሕጋዊ* መብቶች ያሉት ሲሆን ይህም ከድርጅቱ* እና ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ጋር በሚስማማ ሕጋዊ* ሁኔታ የሚመለከታቸው ብሔራዊና አካባቢያዊ ሕጎች* እና ደንቦች እንዲሁም የአስተዳደር መስፈርቶች የሚመለከቱትን ሕጋዊ* ግዴታዎች ማክበር ይኖርበታል። በሕግ የተሰጡት* መብቶች ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ምርቶችን ለመሰብሰብ እና/ወይም ስነ-ምህዳር አገልግሎቶች* ይሰጣል። ድርጅቱ* ከነዚህ መብቶችና ግዴታዎች ጋር የተያያዙ ህጋዊ ክፍያዎችን ይከፍላል።

### *ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ*

*የደረጃ አዘጋጆች በአባሪ ሀ ላይ እንደተገለጸው ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች፣ አስገዳጅ የአሰራር ደንቦች እና ህጋዊና ልማዳዊ መብቶች በአገር አቀፍ ደረጃ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በንዑስ ብሄራዊ ደረጃ ዝርዝር መሙላት አለባቸው።*

1.3.1 በደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በሙሉ የሚከናወኑት፡-

1) የሚመለከታቸው ህጎች እና ደንቦች እና የአስተዳደር መስፈርቶች;
2) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች; እና
3) አስገዳጅ የአሠራር ደንቦች።

NTFP 1.3.1.1 የNTFPs አስተዳደር እና አጠቃቀም ከሁሉም ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች፣ አስገዳጅ መደበኛ መስፈርቶች እና ልማዳዊ መብቶች ያከብራሉ።

1.3.1G የNTFPs ዓላማ ለሰው ልጅ ጥቅም ላይ ሲውል፣ ሁሉም የሚመለከታቸው ህጋዊ እና አስተዳደራዊ የንፅህና እና የምግብ ደህንነት መስፈርቶች ተገዢ መሆን አለባቸው።

1.3.2 ክፍያ የሚፈፀመው ከደን አያያዝ ጋር በተገናኘ በህጋዊ መንገድ የተደነገጉ ሁሉንም ክፍያዎች ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ነው።

1.3.3 በደን አያያዝ ዕቅድ የሚሸፈኑ ተግባራት ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች ለማክበር የተነደፉ ናቸው።

አረጋጋጮች:-

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት፣ አስተዳደርና መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/2005፤ አዋጅ ቁጥር 1065/2005- የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1065/2018-የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና የመሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/2005& የህዝብ ጤና አዋጅ ቁጥር 200/2000&የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1065/2018 መሠረት መሆን አለበት።

**1.4 ድርጅቱ ካልተፈቀደ ወይም ህገወጥ የሀብት አጠቃቀም፣ አሰፋፈር እና ሌሎች ህገ-ወጥ ድርጊቶችን ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎችን በዘዴ ለመከላከል እርምጃዎችን በማውጣት ይተገብራል እና/ወይም ከተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች ጋር ይተባበራል።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

ደረጃ አዘጋጆች መሬቱ በሶስተኛ ወገን ሲሆን እንዲሁም ድርጅቱ ከተቆጣጣሪ አካል፣ ከመሬት ባለቤት እና/ወይም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የትብብር ስትራቴጂን ተግባራዊ ማድረግ በሚያስፈልግበት ጊዜ በሁሉም ምክንያታዊ መንገዶች ህገ-ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚተገበሩ አመልካቾችን ማዘጋጀት አለባቸው። ይህ መስፈርት ድርጅቱ የመከላከያ እርምጃዎችን ለማስፈጸም ሁልጊዜ የማይቻል መሆኑን ይገነዘባል, ለምሳሌ ድርጅቱ የመሬት ባለቤት ካልሆነ ወይም አግባብነት ያለው ህጋዊ የመቆጣጠር መብት ከሌለው (አመላካቾች 1.4.1 እና 1.4.2)።

ለአስተዳደር የተለዩ ቦታዎችን ካልተፈቀደ ወይም ህገወጥ የሀብት አጠቃቀም፣ ሰፈራ እና ሌሎች ህገ-ወጥ ድርጊቶች ለመጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎች ከተከሰቱ በኋላ ከመቆጣጠር ይልቅ መከላከልን መሠረት ያደረገ እና የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል።

- ከፍተኛ ስጋት* ላለባቸውን ቦታዎች የደን* መንገዶች በሮች እና ቁጥጥር የሚደረግባቸው መዳረሻ ይኖራቸዋል፤
- ጊዜያዊ መንገዶች የደን ውጤቶች ከተሰበሰቡ በኋላ ይዘጋሉ፤
- ህገ-ወጥ የደን* መዳረሻን ለመለየት እና ለመከላከል የደን መንገዶች ጥበቃ ይደረግላቸዋል፤ እና
- በተሰጣቸው ህጋዊ መብት መሰረት ህገወጥ ድርጊቶችን በፍጥነት ለመለየትና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሰራተኞችና ሀብቶች ተመድበዋል።

1.4.1 ካልተፈቀደላቸው ወይም ህገወጥ የደን ውጤቶችን መሰብሰብ፣ አደን፣አሳ ማጥመድ፣ እንስሳትን ማጥመድ፣ መሰብሰብ፣ ሰፈራ እና ሌሎች ያልተፈቀዱ ተግባራትን ጥበቃ ለመስጠት እርምጃዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

NTFP1.4.1a ካልተፈቀደላቸው ወይም ህገወጥ NTFPs መቁረጥ፣ መሰብሰብ እና ሌሎች ያልተፈቀዱ ተግባራትን ጥበቃ ለመስጠት እርምጃዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

1.4.2 ጥበቃ የቁጥጥር አካላት ሕጋዊ ኃላፊነት ከሆነ ከነዚህ ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በመሆን ለመለየት፣ ሪፖርት ለማድረግ፣ ያልተፈቀዱ ወይም ህገወጥ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር እና ተስፋ ለማስቀረጥ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቷል።

NTFP 1.4.2a ጥበቃ የቁጥጥር አካላት ሕጋዊ ኃላፊነት ከሆነ ከነዚህ ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በመሆን ለመለየት፣ ሪፖርት ለማድረግ፣ ያልተፈቀዱ ወይም ህገወጥ NTFPs እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር እና ተስፋ ለማስቀረጥ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቷል።

1.4.3 ሕገ ወጥ ወይም ያልተፈቀደላቸው እንቅስቃሴዎች ከተገኙ ለመቋቋም እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

NTFP1.4.3a ህገወጥ ወይም ያልተፈቀደ የNTFPs ምርት ሲሰበሰብ ከተገኘ ችግሩን ለመቋቋም እርምጃዎች ይተገበራሉ።

አረጋጋጮች፡-

አዋጅ ቁጥር 1065/2018-የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ'አዋጅ ቁጥር 456/2005 'የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት ማስታወቂያና አጠቃቀም አዋጅ፣ ደንብ ቁጥር 151/2012፣ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ።

**1.5 ድርጅቱ የደን ዉጤቶችን ለአስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥና ከአስተዳደር የተለዩ ቦታዎች እና እስከ መጀመሪያው ሽያጭ ጣቢያ ድረስ ለማጓጓዝ የሚመለከታቸውን ብሄራዊ ህጎች፣ የአካባቢ ህጎች፤ የጸደቁ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የግዴታ የአሰራር ደንቦች ማክበር አለበት።**

1.5.1 ተፈጻሚነት ካላቸዉ ሀገራዊ ህጎች፣ የአካባቢ ህጎች፣ የፀደቁ  አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የግዴታ የአሰራር ደንቦችን ጋር በተጣጣመ መልኩ የደን ምርቶች ትራንስፖርትና ንግድ እስከ መጀመሪያው የሽያጭ ቦታ ድረስ ታይቷል።

NTFP 1.5.1.1 ተፈጻሚነት ካላቸዉ ሀገራዊ ህጎች፣ የአካባቢ ህጎች፣ የፀደቁ  አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የግዴታ የአሰራር ደንቦችን ጋር በተጣጣመ መልኩ የNTFPs የደን ምርቶች ትራንስፖርትና ንግድ እስከ መጀመሪያው የሽያጭ ቦታ ድረስ ታይቷል።

1.5.2 በማንኛውም የ CITES ዝርያዎች ውስጥ የማምረት እና የንግድ ልውውጥ የምስክር ወረቀቶችን ጨምሮ የ CITES ድንጋጌዎችን ማክበር ታይቷል ።

NTFP1.5.2.1 በሁሉም የ NTFP ዝርያዎች ማምረትና መሰብሰብ እና ንግድ የ CITES ፍቃዶችን ጨምሮ የCITES ድንጋጌዎችን ማክበርን ያሳያል።

አረጋጋጮች፡

አዋጅ ቁጥር 1065/2018-የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 575/2008 የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፤ ለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ለማቅረብ የወጣ አዋጅ ቁጥር 541/2007፤ አዋጅ ቁጥር 1223/2020 የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ።

**1.6 ድርጅቱ ከሚመለከታቸው የተጎዱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት ከህግ ወይም ከባህላዊ ህግ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶችን በጊዜው ከችሎት ውጪ መፍታት፣ይለያል፣ ይከላከል፣ ይፈታል።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

ደረጃ አዘጋጆች በደረጃዎቻቸው ውስጥ አለመግባባቶችን ለመለየት ንቁ እና ከባህል ጋር አግባብ ያለው ተሳትፎ የግጭት አፈታት ሂደትን መከተል ይሻል።

የአገሬው ተወላጆችን እና የአካባቢ ማህበረሰቦችን የሙብት መለያ መስፈርት 3.1 እና መስፈርት 4.1 የሀብት ቁጥጥር እና ነፃ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት በመስፈርት 3.2 እና በመስፈርት 4.2 ውስጥ ተስተናግዷል። የልዩ ጣቢያዎች ጥበቃ በመስፈርት 3.5 እና በ ስታንዳርድስ 4.7 የባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ በመስፈርት 3.6 እና በመስፈርት 4.8 ውስጥ ተስተናግዷል።

ግጭቶችም* ስለ ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች* የደን ባለቤትነት፣ የመሬት ባለቤትነት መብት ተከራካሪ እና የደን ኮንሰሽን ወይም የይዞታ ባለቤትነትን ተከራካሪነት ጨምሮ ሊሆኑ ይችላሉ (አመልካች 1.6.1)።

የደረጃ አዘጋጆች መስፈርት 7.6 በሚፈልገው መሰረት ለባህል ተስማሚ የሆነ የግጭት አፈታት ሂደትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ዘዴ ማዘጋጀት አለባቸው።

ከመሬት ይዞታ ጋር የተገናኙ ግጭቶች በመስፈርት 1.6 ውስጥ ይታያሉ፤ ከሠራተኞች ቅሬታዎች ጋር በተዛመደ መስፈርት 2.6፤ እና በመስፈርት 4.6 ከአካባቢው ማህበረሰቦች እና ግለሰቦች ጋር በተዛመደ የአስተዳደር ተግባራትን ተፅእኖ በተመለከተ።

1.6.1 ለሕዝብ በይፋ የሚገኝ የግጭት አፈታት ሂደት ተዘጋጅቷል፤ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በባህላዊ አግባብ ባለው ተሳትፎ የዳበረ ይሆናል።

1.6.2 ከህግ ወይም ከባህላዊ ህግ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የሚነሱ አለመግባባቶች ከፍርድ ቤት ውጪ ሊፈቱ የሚችሉ ውዝግቦች ወቅቱን የጠበቀ ምላሽ ተሰጥቷቸው እና እልባት አግኝተው ወይም በክርክር አፈታት ሂደት ውስጥ ናቸው።

1.6.3 ወቅታዊ ከህግ ወይም ከባህላዊ ህግ ጉዳዮች ጋር በተያያዙ የክርክር መዝገቦች ተይዘዋል፤ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል

1) አለመግባባቶችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች፤

2) የሁሉም የክርክር አፈታት ሂደቶች ውጤቶች፤ እና

3) ያልተፈቱ አለመግባባቶች፣ ያልተፈቱበት ምክንያቶች እና እንዴት እንደሚፈቱ።

1.6.4 አለመግባባቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ከዋኔዎች ይቆማሉ፡-

1) ከፍተኛ መጠን ያለው፤ ወይም

2) ከፍተኛ ቆይታ ያለው፥ ወይም

3) ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ፍላጎቶች ያካተተ

*አረጋጋጮች፡*

የኦሮሚያ ክልል የጉምሩክ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ፣ አዋጅ ቁጥር 240/2021፣ ደንብ ቁጥር 10/2021።

**1.7 ድርጅቱ በገንዘብም ሆነ በማንኛውም የሙስና መንገድ ጉቦ ላለመስጠት ወይም ላለመቀበል ያለውን ቁርጠኝነት ይፋ ያደርጋል፣ እና ይህ ባለበት ጊዜ የፀረ-ሙስና ህግን ያከብራል። የፀረ-ሙስና ሕግ በሌለበት ጊዜ ድርጅቱ ከሥራ አመራር እንቅስቃሴ መጠንና ከሙስና አደጋ ጋር የተመጣጠኑ ሌሎች የፀረ-ሙስና እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።**

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

*ይህ መመዘኛ ሙስና በአጠቃላይ እንደ ህገወጥ ይቆጠራል ነገር ግን ሁሉም ሀገራት የፀረ-ሙስና ህጎችን እና መመሪያዎችን አልያዙም ወይም አይተገብሩም።*

*የፀረ-ሙስና ሕጎች እና ደንቦች ውጤታማ ካልሆኑ ወይም ከሌሉ ደረጃ አዘጋጆች ሌሎች የፀረ-ሙስና እርምጃዎችን ማካተት አለባቸው ለምሳሌ ድርጅቱ በሕዝብና በግል ዘርፍ ካሉ ሌሎች ድርጅቶች ጋር በመሆን በመደበኛ የቅንነት ስምምነቶች ላይ*

ይሳተፋል ወይም ያዘጋጃል። እያንዳንዱ ተሳታፊ በገንዘብም ሆነ በማንኛውም መልኩ ጉቦ በመስጠት ወይም በመቀበል ሙስና ውስጥ ላለመሳተፍ ይፋዊ በሆኑ መግለጫዎች ይስማማል (አመልካች 1.7.4)።

እንደዚህ ባሉ ጉዳዮች ላይ ልምድ ያለው ገለልተኛ ሶስተኛ አካል ከእንደዚህ አይነት መግለጫዎች ጋር የተያያዘውን አፈፃፀም መከታተል አለበት።

1.7.1 በየትኛውንም መልኩ ጉቦ ላለመስጠት ወይም ላለመቀበል ቁርጠኝነትን የሚያካትት ፖሊሲ ተፈጻሚ ይሆናል

SLIMF 1.7.1.1 ጉቦ (ገንዘብ) ላለመስጠት ወይም ላለመቀበል ወይም በሌላ የሙስና መንገድ ላለመሳተፍ የጽሁፍ ወይም የቃል መግለጫ ለጎረቤቶች እና ለደንበኞች ይነገራል።

1.7.2 ፖሊሲው ተዛማጅ ሕጎችን ያሚላል ወይም ይበልጣል።

1.7.3 ፖሊሲው ያለ ምንም ወጪ በይፋ ይገኛል።

1.7.4 ጉቦ፣ ማስገደድ እና ሌሎች የሙስና ድርጊቶች አይፈጸሙም።

1.7.5 ሙስና ከተፈጠረ የማስተካከያ እርምጃዎች ይተገበራሉ።

SLIMF 1.7.5.1 ሙስና ከተፈጠረ የማስተካከያ እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

አረጋጋጮች፡-

አዋጅ ቁጥር 1236/2021 የተሻሻለው የፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ።

1.8 ድርጅቱ የ FSC መርሆዎችን እና መስፈርቶችን እና ተዛማጅ የ FSC ፖሊሲዎች እና ደረጃዎች በደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች በዘለቄታዊነት ስለመገዛቱ ያሳያል። የዚህ ቁርጠኝነት መግለጫ በይፋ የሚገኝ በሚገኝ ነጻ ሰነድ ውስጥ ተካትቶ ይገኛል።

1.8.1 ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ስልጣን ባለው ግለሰብ የጽሁፍ ፖሊሲ ከ FSC መርሆዎችን መስፈርቶች እና ተዛማጅ ፖሊሲዎችና ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነት የደን አያያዝ ተግባሮችን ያረጋግጣል።

1.8.2 ፖሊሲው ያለ ምንም ክፊያ በይፋ ይገኛል።

## መርህ 2፡ የሰራተኞች መብቶች እና የስራ ሁኔታዎች

ድርጅቱ የሰራተኞችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን መጠበቅ ወይም ማሻሻል አለበት።

2.1 ድርጅቱ በ ILO መሰረታዊ መርሆች እና የስራ መብቶች መግለጫ (1998) በስምንቱ ILO ዋና የስራ ስምምነቶች ላይ የተገለጹትን በስራ ላይ ያሉትን መርሆዎች እና መብቶችን ያስከብራል።

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

ደረጃ አዘጋጆች በአገር አቀፍ ህግ የተቀመጡትን መብቶች እና ግዴታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። በተመሳሳይ ጊዜ በዚህ መስፈርት ውስጥ ያሉትን የአመልካቾችን እና የንዑሳን አመላካቾችን ዓላማዎችን ያሚላሉ።

2.1.1 ድርጅቱ የህፃናት ጉልበት መጠቀም የለበትም።

2.1.1.1 ድርጅቱ በ 2.1.1.2 ከተገለፀው በስተቀር እድሜያቸው ከ15 በታች የሆኑ ሰራተኞችን ወይም በሀገር ውስጥ ወይም በአካባቢ ህጎች ወይም ደንቦች መሰረት ከዝቅተኛ እድሜ በታች ያሉ ሰራተኞችን መቅጠር የለበትም።

2.1.1.2 ከ13 እስከ 15 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች በቀላል ሥራ እንዲቀጠሩ በብሔራዊ ሕግ ወይም መመሪያ በሚፈቅድባቸው አገሮች ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ሥራ በትምህርታቸው ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም ወይም በጤናቸው ወይም በእድገታቸው ላይ ጉዳት ሊያደርስ አይገባም። በተለይም አስገዳጅ የትምህርት ሕግ ባለበት ቦታ ሕፃናት ከትምህርት ሰዓት ውጪ መስራት አለባቸው።

2.1.1.3 ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው በፀደቁ ብሄራዊ ህጎች እና መመሪያዎች ውስጥ ከስልጠና ዓላማ በስተቀር በአደገኛ ወይም ከባድ ስራ ውስጥ አይቀጠርም።

2.1.1.4 ድርጅቱ የከፋ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛን ይከለክላል።

2.1.2 ድርጅቱ ሁሉንም ዓይነት አስገዳጅ እና የግዴታ ስራዎችን ያስወግዳል።

2.1.2.1 የቅጥር ግንኙነቶች በፈቃደኝነትና በጋራ ስምምነት እና ያለምንም የቅጣት ማስፈራሪያ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

2.1.2.2 አስገዳጅ ወይም የግዴታ ሥራን የሚያመለክት ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም፤ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን ጨምሮ ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም፡-

- አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት
- ለሌላ ውለታ ማካካሻ የጉልበት ሥራ
- የጉልብት ሥራ፣ የቅጥር ሥራ እና የሥራ መግቢያ ማስከበሪያ በሚል የሚደርግ የደመወዝ ማቆየት
- የመንቀሳቀስ ገደብ
- ፓስፖርት እና የመታወቂያ ሰነዶችን ማቆየት
- ለባለሥልጣናት የዛቻ ማስፈራሪያ

2.1.3 ድርጅቱ በስራ እና በሙያ ላይ ምንም አይነት አድልዎ አለመኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2.1.3.1 የስራ እና የሙያ ተግባሮች አድሎአዊ አይደሉም።

2.1.4 ድርጅቱ የሠራተኞችን የመደራጀት እና የጋራ መደራደርን መብት ያከብራል።

2.1.4.1 ሠራተኞች የመረጡትን የሠራተኛ ማህበራትን ማቋቋም ወይም መቀላቀል ይችላሉ።

2.1.4.2 ድርጅቱ የሠራተኞችን ማህበር ከመመሥረት፣ ከመቀላቀል ወይም ከመርዳት ጋር በተያያዙ ሕጋዊ ተግባራት ውስጥ መሳተፍን ያከብራል ወይም ይህንኑ ከማድረግ የመቆጠብ መብታቸውን ያከብራል፤ እና ሠራተኞችን እነዚህን መብቶች በመጠቀማቸው አያገልም ወይም አይቀጣም።

2.1.4.3 ድርጅቱ በህጋዊ መንገድ ከተቋቋሙ የሠራተኛ ማህበራት እና/ወይም በአግባቡ ከተመረጡ ተወካዮች ጋር በቅን ልቦና እና ከፍተኛ ጥረት በማድረግ በጋራ ለመስማማት ይደራደራል።

2.1.4.4 የጋራ ድርድር ስምምነቶች ባሉበት ይተገበራሉ።

2.2 ድርጅቱ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በቅጥር ሁኔታዎች፤ የስልጠና እድሎች፤ ውሎችን መስጠት፤ የተሳትፎ ሂደቶች እና የአስተዳደር ተግባራትን ያበረታታል።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

ደረጃ አዘጋጆች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በቅጥር ሁኔታዎች፤ የስልጠና እድሎች፤ ውሎችን መስጠት፤ የተሳትፎ ሂደቶች እና የአስተዳደር ተግባራትን በተመለከተ ብሔራዊ ሕጎችንና ደንቦችን መለየት አለባቸው።

ደረጃ አዘጋጆች በዚህ መስፈርት እና በብሔራዊ ደንቦች መካከል ያሉ ክፍተቶችን በመለየት እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ድርጅቱ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች የሚገልጹ አመልካቾችን ማዘጋጀት አለባቸው። እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት በአንዳንድ ሁኔታዎች በድርጅቱ ተጨማሪ ስርዓቶችን መዘርጋት ሊያስፈልግ ይችላል እና እነዚህም የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- ለሴቶች የሥራ ሙያቸዉን ለማሳደግ ክህሎትን የሚያገኙበትን የሥልጠና እድሎችን መስጠት፤
- ሴቶች በሁሉም የድርጅቱ ደረጃዎች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ የሚረዱ ፕሮግራሞችን የአማካሪና የአመራር ሥልጠናን ጨምሮ መስጠት፤
- የሴት ሰራተኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ አማራጭ የመከፈያ ዘዴዎችን ማዘጋጀት፣ ለምሳሌ ለትምህርት ቤት ቀጥተኛ ክፍያዎች፤
- ለወላጆች ተለዋዋጭ የሥራ ፖሊሲዎችን እና ልምዶችን መስጠት፤ ለምሳሌ፡-ተለዋዋጭ የሥራ ሰዓቶች፣ የሥራ መጋራት እና በትምህርት ጊዜ ውስጥ አንደሁኔታው ሥራን ሰዓት ማመቻቸት፤
- ወንዶች ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ በወሊድ ጊዜ የአባትነት ፈቃድ እንዲወስዱ ማበረታታት፤
- በእርግዝና ወቀት የደመወዝ ቅነሳ ሳይደረግ ተለዋጭ ብዙ ጉልብት የማይጠይቅ የሥራ እድሎችን ማመቻቸት፤ እና
- ለነፍሰ ጡር እና ለሚያጠቡ እናቶች የተመቻቸ ሁኔታ ማዘጋጀት እንዲሁም ለቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ ላሉ ህፃናት የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት መስጫ ቦታዎችን ማመቻቸት።

---

2.2.1 የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የሚያበረታቱ እና የሥርዓተ-ፆታ መድልዎን የሚከላከሉ በስራ አቀጣጠር ሥርዓት፤ የስልጠና የእድገት እድሎች፤ ኮንትራቶች መስጠት፤ የተሳትፎ ሂደቶች እና የአስተዳደር ስራዎችን የሚከላከሉ ስርዓቶች ይተገበራሉ።

2.2.2 የስራ እድል ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች በተመሳሳይ ሁኔታ ክፍት ሆኖ ሴቶች በሁሉም የስራ ደረጃዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

2.2.3 በተለምዶ በሴቶች የሚከናወኑ ስራዎች (የችግኝ ጣቢያ ሥራ፣ የሲሊቪካልቸር፣የእንጨት-ያልሆኑ የደን ምርቶች አሰባሰብ፣መመዘን፣ማሸግ፣ወዘተ) በተመሳሳይ በወንዶች ከሚከናወኑ ስራዎች ጋር በስልጠናና በጤና እና ደህንነት መርሃ ግብሮች ተካቷል።

2.2.4 ሴቶች እና ወንዶች አንድ አይነት ስራ ሲሰሩ ተመሳሳይ ደመወዝ ይከፈላቸዋል።

2.2.5 በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ 1156/2019 እ.ኤ.አ. ቁጥር 2 አንቀጽ 57 ላይ በተደነገገው መሠረት ሴቶች ደሞዛቸው በአስተማማኝና ዋስትና ባለው መንገድ መከፈሉን ለማረጋገጥ በቀጥታ እና የጋራ ስምምነት ላይ በተደረሰባቸው መንገዶች (ለምሳሌ ቀጥታ የባንክ ዝውውር፣ ቀጥተኛ የትምህርት ቤት ክፍያ ወዘተ) ይከፈላል።

2.2.6 በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ምዕራፍ 1 ክፍል 88 ላይ እንደተገለጸው ከቅድመ ወሊድ ክፍያ ጋር ከ30 ተከታታይ ቀናት እና ከወሊድ በኋላ ለ90 ተከታታይ ቀናት የሚቆይ የወሊድ ፈቃድ ይሆናል።

2.2.7 የአባትነት ፈቃድ ከክፍያ ጋር የ 3 ቀናት እና ተጨማሪ አምስት ተከታታይ ቀናት ያለክፍያ ልዩ እና ከባድ ሁኔታዎች ሲኖሩ ይፈቀዳል።

2.2.8 በኢትዮጵያ ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 በተገለፀዉ መሠረት ስብሰባዎች፣ የአመራር ኮሚቴዎች እና ውሳኔ ሰጭ መድረኮች የሚዘጋጁት ሴቶችና ወንዶችን ባካተተ መልኩ ሲሆን የሁለቱም ፆታዎች የነቃ ተሳትፎ እንዲኖር ለማመቻቸት ነው።

2.2.9 በኢትዮጵያ ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 በተደነገገው መሠረት በጾታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በጎሳ፣ በወላጅነት ወይም በፆታዊ ዝንባሌ ላይ የተመሰረቱ ጾታዊ ትንኮሳ እና አድሎአዊ ጉዳዮችን ሪፖርት ለማድረግ እና ለማስወገድ ሚስጥራዊ እና ውጤታማ ዘዴዎች አሉ።

አረጋጋጮች: የክፍያ ደረሰኞች፣ የደመወዝ ዝርዝር፤ የወሊድ ፈቃድ ድንጋጌዎች በሥራ ስምሪት ኮንትራቶች እና በድርጅቱ የሰው ኃይል ፖሊሲ፤ ከሠራተኞች ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች፤ የአባትነት ፈቃድ ድንጋጌዎች በሥራ ስምሪት ውል እና በድርጅቱ የሰው ኃይል ፖሊሲ፤ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎች፤ የሪፖርት ማቅረቢያ ሥርዓቶች እና የአደጋ ጊዜ ዘጋባዎች።

**2.3 ድርጅቱ ሰራተኞችን ከስራ ደህንነት እና የጤና አደጋዎች ለመጠበቅ የጤና እና የደህንነት ልምዶችን ተግባራዊ ያደርጋል። እነዚህ ልምዶች ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ክብደትና አደገኝነት ጋር መመጣጠን አለባቸው፤ ይህም በደን ስራ ደህንነትና ጤና ላይ የILO የተግባር መመሪያን ማሟላት ወይም ከዚያ በላይ ማለፍ አለባቸው።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

ደረጃ አዘጋጆች በአባሪ ሀ ክፍል 3.4 የሰራተኞች ጤና እና ደህንነትን የሚመለከቱ ብሄራዊ ህጎች እና መመሪያዎች ILO በደን ስራ ደህንነት እና ጤና ላይ የተግባር መመሪያ እና የ ILO ስምምነት 155፣ የስራ ደህንነት እና ጤና ኮንቬንሽን (1981) መሠረት ማሟሟላታቸውን ወይም ከዚያም በላይ ማለፋቸውን ይለያሉ። ደረጃ አዘጋጆች በዚህ መስፈርት እና በብሔራዊ ደንቦች መካከል ያሉ ክፍተቶችን በመለየት እነዚህ ክፍተቶች በድርጅቱ እንዴት እንደሚፈቱ አመልካች 2.3.1 ይለያሉ።

2.3.1 የILO በደን ስራ ደህንነት እና ጤና ላይ የተግባር መመሪያ ኮድ የአሠራር ደንብ የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ የጤና እና የደህንነት ልምዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሆነዋል።

NTFP 2.3.1.1 ከNTFPs አስተዳደር እና ምርት አሰባሰብ ጋር ተያይዘው የሚመጡ የጤና እና የደህንነት ስጋቶች ተለይተው ይገመገማሉ፤ እናም ለአደጋው የማያጋልጡ ተስማሚ የሆኑ የጤና እና የደህንነት ልምዶች ይተገበራሉ።

NTFP 2.3.1.2 ድርጅቱ ከምግብ ወለድ በሽታዎች ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በመለየት ተገቢውን የNTFPs መሰብሰብ እና ማቀነባበር አደጋን ለመቀነስ የጤና እና የደህንነት መመሪያዎችን ያዘጋጃል።

NTFP 2.3.1.3 ለሰው ልጅ ፍጆታ የታሰቡትን ሁሉን የ NTFPs ምርት ለመሰብሰብ እና ለማሸግ የህዝብ ጤና አዋጅ ቁጥር 200/2000 የምግብ ጥራት ቁጥጥር እና የምግብ ደረጃ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የሰነድ ሂደቶች አሉ።

NTFP 2.3.1.4 ለምግብነት የሚውሉ NTFPsን ለማቀነባበር የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ንፁህ እና ቀደም ሲል ከተሰበሰቡ ቁሳቁሶች የፀዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የንፅህና አጠባበቅ ሂደት አለ።

NTFP 2.3.1.5 ለምግብነት የሚውሉ NTFP ቁሳቁሶችን በማቀነባበሪያ ቦታዎች ናሙናዎችን ለመውሰድ እና እነሱን ለመመዝገብ እና ለማከማቸት ሂደት ተዘጋጅቷል።

NTFP 2.3.1.6 የማምረቻው ሥራ አስኪያጅ ከNTFPs አሰባሰብ ጋር የተያያዙ ተዛማጅ የጤና እና የደህንነት መመሪያዎችን ያውቃል።

SLIMF 2.3.1.1 እያንዳንዱ ሰራተኛ ከእንቅስቃሴው ጋር የሚዛመዱ የጤና እና የደህንነት እርምጃዎች ይነገራቸዋል፤ እና እነዚህም የILO በደን ስራ ደህንነት እና ጤና ላይ የተግባር መመሪያን ያሟላሉ ወይም ከዚያ በላይ ያልፋሉ።

2.3.2 ሠራተኞች ለተሰጣቸው ሥራ ተስማሚ የሆኑ የግል መከላከያ መሣሪያዎች አሏቸው።

NTFP2.3.2.1 NTFPsን ለመሰብሰብ እና ለማቀነባበር ለሠራተኞች የሚሰጡ የግል መከላከያ መሣሪያዎች ለተመደቡበት ሥራ ተስማሚ ናቸው።

2.3.3 ተዛማጅነት ያላቸውን የግል መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀም አስገዳጅ ነው።

2.3.4 በጤና እና በደህንነት ተግባሮች የአደጋ ደግግሞሽ እና በአደጋ ጊዜ የባከኑ ሰዓቶች ጨምሮ መረጃዎች ተመዝግበው በአግባቡ ይቀመጣሉ።

SLIMF 2.3.4.1 የጤና እና የደህንነት እርምጃዎችን በሠራተኞች መጠቀማቸው ተረጋግጧል እና ይታወቃል።

2.3.5 ከአገር አቀፍ የደን ኢንዱስትሪ አማካኝ ጋር ሲነፃፀር የአደጋው ድግግሞሽ እና ክብደት በተከታታይ ዝቅተኛ ነው።

SLIMF 2.3.5.1 የአደጋ መጠን ከብሔራዊ የደን ኢንዱስትሪ አማካይ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው።

2.3.6 የጤና እና የደህንነት ተግባራት ከፍተኛ አደጋዎች ወይም አደጋዎች በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ ይገመገማሉ እና ይሻሻላሉ።

*አረጋጋጮች፡-*

*ወቅታዊ የአደጋ መዝገቦች።*

2.4 ድርጅቱ* ዝቅተኛውን የደን ደመወዝ የሚያሟላ ወይም የሚበልጥ ይከፍላል። በሀገሪቱ ከሚታወቁ ኢንዱስትሪ ደረጃዎች ወይም ሌሎች እውቅና ያላቸው የደን ኢንዱስትሪ የደመወዝ ስምምነቶች አንጻር ከሆን ግን ከህጋዊ* ዝቅተኛ ደመወዝ በላይ መሆን ይኖርበታል። ከእነዚህ መካከል አንዳቸውም ከሌሉ ድርጅቱ* ከሠራተኞች* ጋር በመደራደር ለኑሮ በቂ ደመወዝ የመወሰን ዘዴዎችን ያዘጋጃል።

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

ደረጃ አዘጋጆች ሁሉንም የደን ኢንዱስትሪ ደረጃዎች፣ እንዲሁም ሌሎች የታወቁ የደን ኢንዱስትሪ ደሞዝ ስምምነቶችን እና የኑሮ ደሞዝ መለኪያዎችን መለየት አለባቸው፤ እና ከእነዚህ ውስጥ የትኞቹ ከህጋዊ ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ ከፍ እንደሚል እና በምን ያህል እንደሚበላለጥ መለየት አለባቸው። ደረጃ አዘጋጆች በዚህ ክፍተት ትንተና ላይ ተመስርተው 2.4.2 እና 2.4.3

አመላካቾችን ማስተካከል አለባቸው። ደረጃ አዘጋጆች በ ISEAL እየተገበሩ ያሉትን መሠረታዊ የኑሮ ደመወዝ መወሰኛ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

የኑሮ ደመወዝን ለመወሰን የሚያገለግሉ ዘዴዎች በመስፈርት 7.6 (አመልካች 2.4.3) መሰረት ባህላዊ መልኩን በጠበቀ መሆን አለበት።

2.4.1 በድርጅቱ የሚከፈለው ደመወዝ በማንኛውም ሁኔታ በሀገሪቱ ከተደነገጉ ህጋዊና ዝቅተኛ የደመወዝ ተመኖችን (ተግባራዊ እይሆነ ካለ) ያሟላል ወይም ይበልጣል።

2.4.2 የሚከፈለው ደሞዝ የሚከተሉትን ያሟላል ወይም ይበልጣል፡-

1) ዝቅተኛ የደን ኢንዱስትሪ ደረጃዎች፤ ወይም
2) ሌሎች የታወቁ የደን ኢንዱስትሪ ደሞዝ ስምምነቶች፤ ወይም
3) በኢትዮጵያ የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ምዕራፍ 2 ክፍል 55.2 ከተቀመጠው ህጋዊ ዝቅተኛ ደመወዝ በላይ የሆነ የኑሮ ደመወዝ።

የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት፣ የስራ ገበያ እና ሌሎች የስራ ሁኔታዎችን ታሳቢ ባደረጉ ጥናቶች ላይ ተመስርቶ የዝቅተኛ ክፍያን በየጊዜው ይከልሳል።

2.4.3. ሚስጥራዊነትን በጠበቀ ሁኔታ፤ የደመወዝ ደረጃ እና የክፍያ ደረሰኞች ለሠራተኞች ይገለፃሉ።

2.4.4 ምንዳ፣ ደሞዝ እና ኮንትራት በወቅቱ ይከፈላሉ።

**2.5 የድርጅቱ ሰራተኞች የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ እና ሁሉንም የአስተዳደር ስራዎችን በአስተማማኝ እና በብቃት ተግባራዊ ለማድረግ ሥራ ላይ የተመሰረተ ስልጠና እና ቁጥጥር እንዳላቸው ያሳያል።**

2.5.1 ሠራተኞች ደህንነቱን በጠበቀና በአስተማማኝ ሁኔታ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ እና የአስተዳደር ተግባራት አፈፃፀም ትግበራ አስተዋፅዖ ለማድረግ ከአባሪ “K” ጋር የተጣጣመ የሥራ ተኮር ሥልጠና ቁጥጥር አላቸው።

NTFP 2.5.1.1 ሰራተኞች በስራ ላይ ደህንነት እና ልዩ ስልጠና ለማረጋገጥ ቁጥጥር እንዳላቸው ማሳየት።

NTFP 2.5.1.2 በ NTFP መሰብሰብ ሥራ ላይ የተሳተፉ የሁሉም ሠራተኞች መዝገብ አለ።

NTFP 2.5.1.3 የNTFPs የመሰብሰብ ሥራ ስራ-አስኪያጁ፡-

1) የማምረትና የምርት መሰብሰብ ቦታ በግልፅ የሚታወቅ እና በደንብ የሚያውቅ።
2) በሚመለከታቸው አካባቢዎች ካሉ ሌሎች የማምረትና የመሰብሰብ/የማጨድ ሥራዎች ጋር ትብብርና ቅንጅት መኖሩን ያረጋግጣል።
3) ከአካባቢው ማህበረሰብ/አምራች ቡድኖች ጋር ተባብሮ ይሰራል።

NTFP 2.5.1.4 NTFPs ን በማምረትና በማቀነባበር የተሰማሩ ሠራተኞች ወይም ተወካዮቻቸው (ለምሳሌ የማህበረሰብ ተወካይ ወዘተ) ምን እንደሚመረትና እንዴት እንደሚካሄድ ስምምነትን ጨምሮ የተፈራረመ ውል አላቸው።

2.5.2 ወቅታዊ የሥልጠና መዝገቦች ለሁሉም የሚመለከታቸው ሠራተኞች ተቀምጠዋል።

አረጋጋጮች፡

የሥልጠና መዝገቦች፣ የሥልጠና ሰርተፍኬቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤ እንዲሁም ከሠራተኞች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

**2.6 ድርጅቱ ከሠራተኞች ጋር በመገናኘት ለሠራተኞች በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ውድመት ፣ ለድርጅቱ በሚሰሩት ሥራ ጋር በተያያዘ በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ወይም በስራ ላይ ለደረሰ ጉዳት ቅሬታዎችን ለመፍታት እና ፍትሃዊ ካሳ የመስጠት ዘዴዎች ሊኖሩት ይገባል ።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

ከሠራተኞች ጋር የሚነሱ ቅሬታዎች ብዙውን ጊዜ መነሻቸው በዘር፣ በጾታ ወይም በጾታዊ ትንኮሳ ላይ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ማለት ደረጃ አዘጋጆች መስፈርት 7.6 (አመልካች 2.6.1) ተከትለው የክርክር አፈታት ሂደቶችን ለመወሰን ባህላዊና አግባብ ያለው ተሳትፎ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ አመላካቾችን ማዘጋጀት አለባቸው።

2.6.1 ከሠራተኞች ጋር የሚደረግ የግጭት አፈታት ሂደት ባሕላዊና አግባብነት ባለው ግንኙነት የዳበረ ነው።

2.6.2 የሰራተኞች ቅሬታዎች ተለይተው ምላሽ ተሰጥተዋል ወይ ተፈትተዋል ወይም በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ናቸው።

2.6.3 ከሠራተኞች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ማለትም ከንብርት ጉዳት ወይም ውድመት፣ በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ወይም ጉዳቶች በወቅቱ ተመዝገብበው ይያዛሉ። በተጨማሪም፡-

1) ቅሬታዎችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች፤
2) የሁሉም አለመግባባቶች አፈታት ሂደተ ውጤቶችና ፍትሀዊ ማካካሻ*፤ እና
3) ያልተፈቱ አለመግባባቶች፤ ያልተፈቱበት ምክንያቶች እና እንዴት እንደሚፈቱ ያጠቃልላል።

2.6.4 ለሠራተኞች ከሥራ ጋር በተያያዘ ለሚደርስ የንብረት ማጣት ወይም ጉዳት እና በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ወይም ጉዳቶች ፍትሃዊ ማካካሻ ይሰጣል።

## ***መርህ 3፡ የአገሬው ተወላጆች መብቶች***

ድርጅቱ የአገሬውን ተወላጆች በደን አያያዝ ተግባራት የተጎዱትን የመሬት፣የግዛት እና የሀብት ባለቤትነት፣የመጠቀም እና የማስተዳደር መብት በመለየት ይደግፋል።

**3.1 ድርጅቱ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች የሚኖሩ እና በደን አያያዝ ተግባራት የተጎዱ የአገሬው ተወላጆች ይለያል። ድርጅቱ ከነዚህ ተወላጆች ጋር በመገናኘት የይዞታ መብቶቻቸውን፣ የደን ሃብትና የስነ-ምህዳር አገልግሎት የማግኘትና የመጠቀም መብቶቻቸውን፣ ልማዳዊ መብቶቻቸውን፤ ህጋዊ መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪም ድርጅቱ እነዚህን መብቶች አስመልክቶ የሚከራከሩባቸውን ቦታዎች ይለያል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

ይህ መመዘኛ ከደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ጥቅማ ጥቅሞችን፣ ምርቶች ወይም የስነ-ምህዳር አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲፈቀድላቸው ፍትሃዊ እና ህጋዊ የይገባኛል ጥያቄ ያላቸውን የሀገሬ ተወላጆችን መለየት ይጠይቃል። ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ በማዋል የመሬት፣ የደን እና ሌሎች ሃብቶች መብታቸውን ያረጋገጡ እና እንዲሁም ይህን ያላደረጉትን (ለምሳሌ በግንዛቤ እጥረት ወይም በስልጣን ማነስ) (አመልካች 3.1.1) ይገኙበታል።

ደረጃ አዘጋጆች እነዚህን የመብቶች ጥያቄዎች የሚደግፉ የጽሁፍ ወይም መዛግብት በሌሉበት ጊዜ የሀገሬ ተወላጆችን መብቶች እና ግዴታዎች የመለየት ፣ የመስማማት እና የመመዝገብ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ሲውል ለማረጋገጥ አመልካቾችን ያዘጋጃሉ።

ደረጃ አዘጋጆች መስፈርት 7.6 (አመልካች 3.1.2) የሚፈልገውን በባህላዊ ሁኔታ ተስማሚ* የሆኑ የአገሬው ተወላጆች* መብትና ግዴታዎችን ለመለየትና ለመመዝገብ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማዘጋጀት አለባቸው።

የደረጃ አዘጋጆች የአገሬው ተወላጆች ባህላዊ ገጽታዎችን ጨምሮ የአገሬው ተወላጅ ህዝቦችን መብቶች እና ግዴታዎች ለመለየት እና ለመመዝገብ በባህላዊ ተስማሚ የሆን* እና በነጻ፣ በቅድሚያና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ከተጎዱ የመብት ባለቤቶች ጋር በመስማማት*ዘዴን ያዘጋጃሉ፣ ይህም በመሥፈርት* 3.1, 3.4, 3.5 እና 4.1 መሠረት ከተገለጹት ሌሎች ህጋዊ* እና የተለመዱ መብቶች* ጋር የሚስማማ እና ከመስፈርት 7.6 መስፈርቶች (አመልካች 3.1.2) ጋር የሚጣጣም ነው።

በተጨማሪም፣ መገናኘት ለማይፈልጉ ተወላጆች (ለምሳሌ ፔሩ፣ ብራዚል) ተዛማጅ አመልካች (አመልካች 3.1.2) በማዘጋጀት መከበር አለባቸው። በአስተዳደር ተግባራት የተጎዱት የሀገሬ ተወላጆች ከደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች አጎራባች እና ርቀው የሚገኙና በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ምክንያት አሉታዊ ተጽእኖ የሚያጋጥማቸውን ያጠቃልላል።

ከሕጋዊ መሬት ይዞታ ጋር በተገናኘ የአገሬው ተወላጆች አለመግባባቶችን ለመፍታት መመዘኛ 1.6 ላይ የተገልጽውን ይመልከቱ፤ እና 4.6 ውስጥ ያሉትን መስፈርቶችና ከአስተዳደር ተግባራት ተጽእኖዎች ጋር የሚዛመዱ አመልካች (3.1.2) መከተል አለባቸው።

3.1.1 በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉ የሀገሬው ተወላጆች ተለይተዋል።

3.1.2 በ3.1.1 ውስጥ በተገለፀው መሠረት፣ ከሀገሬው ተወላጆች ጋር አግባብነት ባለው ባህላዊ መስተጋብር የሚከተሉት በሰነድ እና/ወይም በካርታ ተቀርፀዋል፡-

1) የይዞታ ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው፤
2) ህጋዊ እና ልማዳዊ የደን ሀብቶች እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶች የመጠቀም መብት፤
3) ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው እና ተፈጻሚነት ያላቸው ግዴታዎች፤
4) እነዚህን መብቶች እና ግዴታዎች የሚደግፉ ማስረጃዎች፤
5) በአገሬው ተወላጆች፣ መንግስታት እና/ወይም ሌሎች መካከል የመብት ክርክር የሚካሄድባቸው አካባቢዎች፤
6) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እና ተከራካሪ መብቶች በድርጅቱ የሚቀርቡበት መንገዶች ማጠቃለያ፤ እና
7) የአገሬው ተወላጆች ምኞቶች እና ግቦች ከአስተዳደር ተግባራት፣ ያልተነኩ የደን ገፅታዎች እና የአገሬው ተወላጅ ባህላዊ ገፅታ ጋር የተያያዙ።

NTFP3.1.2.1 ውስጥ በተገለፀው መሠረት፣ ከሀገሬው ተወላጆች ጋር አግባብነት ባለው ባህላዊ መስተጋብር የሚከተሉት በሰነድ እና/ወይም በካርታ ተቀርፀዋል፡-

1) የደን መሬት ይዞታ ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው፤
2) እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶች ህጋዊ እና ልማዳዊ የመጠቀም መብት፤
3) የእነርሱ ህጋዊ እና የልማዳዊ መብቶች እና ተፈጻሚነት ያላቸው ግዴታዎች፤
4) እነዚህን መብቶች እና ግዴታዎች የሚደግፉ ማስረጃዎች፤
5) በአገሬው ተወላጆች፣ መንግስታት እና/ወይም ሌሎች መካከል የመብት ክርክር የሚካሄድባቸው አካባቢዎች፤
6) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እና የተከራከሩበት መብቶች እና በድርጅቱ የሚቀርቡበት የተፈቱበት መንገዶችና ማጠቃለያ፤
7) ከአስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ የአገሬው ተወላጆች ምኞቶች እና ግቦች።

***አረጋጋጮች፡-***

የአገሬው ተወላጆችን የመለየት ሂደት፣ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች እና አጎራባች ቦታዎች ውስጥ ተለይተው የታወቁ የአገሬው ተወላጆች የሚገልጹ ሪፖርቶች፤ ከአገሬው ተወላጆች ጋር የተደረገ የምክክር እና የውይይት ማስረጃ፤ በአመላካቾች 3.1.2 እና NTFP 3.1.2.1 በተዘረዘሩት ጉዳዮች 1-8 ላይ ያለው መረጃ።

**3.2 ድርጅቱ* የአገሬው ተወላጆች* ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ ወይም ከእሱ ጋር በተያያዘ በሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት ላይ ቁጥጥርን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ሕጋዊ* እና ልማዳዊ* መብቶች* እውቅና ይሰጣል እንዲሁም ያከብራል።* የአገሬው ተወላጆች* የአስተዳደር ተግባራትን ለመቆጣጠር የሶስተኛ ወገን ውክልና ለመስጠት ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* ያስፈልጋል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

ደረጃ አዘጋጆች በብሔራዊ እና በንዑስ ብሔራዊ ደረጃ (አመልካች 3.2.1 እና 3.2.4) የነቃ ተሳትፎ እና የጋራ አስተዳደርን ተግባራዊነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። የደረጃ አዘጋጆች መልካም እምነት* በILO ኮንቬንሽኖች* ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ሆኖ እንዲታወቅ እና እንደ ኦዲት የሚደረግለት አካል እንዲታወቅ ያደርጋሉ (አመልካች 3.2.5) ።

3.2.1 ባህላዊ አግባብ ባለው*ተሳትፎ* የአገሬው ተወላጆች* መቼ፣ የት እና እንዴት አስተያየታቸውን ሊሰጡና መብቶቻቸውን፣ ሀብቶቻቸውን፣ መሬቶቻቸውንና ግዛቶቻቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን የአስተዳደር ተግባራትን እንዴት አስተያየት እንደሚሰጡና ማሻሻያዎችን እንደሚጠይቁ መረጃ ያገኛሉ።

3.2.2 የአገሬው ተወላጆች ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸው በድርጅቱ አይጣሱም።

3.2.3 ከአስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ የአገሬው ተወላጆች ሕጋዊ* እና ልማዳዊ መብቶች* የተጣሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ሲኖር ሁኔታው አስፈላጊ ከሆነ በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ* በሆነ* ተሳትፎ* እና/ወይም በ1፣6 ወይም በ4.6 መስፈርት* በተጠየቀው የክርክር መፍቻ* ሂደት ይስተካከላል።

3.2.4 ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* በአገሬው ተወላጆች* የሚሰጥ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን የሚያካትት ሂደት በመጠቀም የተለዩ መብቶቻቸውን የሚነኩ የአስተዳደር ተግባራትን ከማካሄድ በፊት ነው፡-

1) የአገሬው ተወላጆች ሀብቱን በሚመለከት መብታቸውን እና ግዴታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤
2) በኢኮኖሚያዊ ፣ በማህበራዊ እና በአካባቢያዊ ሁኔታዎች የሀብቱን ዋጋ ለአገሬው ተወላጆች በደንብ ማሳወቅ ፣
3) የአገሬው ተወላጆች* መብታቸውን፣ ሀብታቸውን፣ መሬታቸውንና ግዛታቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን ለታቀዱት የአስተዳደር ተገባራት ፈቃዳቸውን የመከልከል ወይም የመቀየር መብታቸውን ማሳወቅ*፤ እና
4) ለአካባቢው ተወላጆች ወቅታዊ እና የወደፊት የታቀዱ የደን አስተዳደር ተግባራትን ማሳወቅ ።

3.2.5 በነፃ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* ሂደት እስካሁን ድረስ የ FPIC* ስምምነት ካልተደረገ ድርጅቱ* እና የተጎዱት የአገሬው ተወላጆች* በጋራ በስምምነት የ FPIC* ሂደት ውስጥ ገብተዋል፤ ይህ ሂደት በመልካም እምነት* እየተከናወነ ሲሆን ማህበረሰቡም በዚህ ስምምነት ረክቷል።

***አረጋጋጮች፡***

በግልጽ የተመዘገቡ የአገሬው ተወላጆች መብቶች፤ ለአገሬው ተወላጆች በመብታቸው ላይ የግንዛቤ ፈጠራ መዝገብ፤ በግልጽ የተመዘገበ የFPIC ሂደት እና ስለ ተወላጆች ተመሳሳይ ግንዛቤ።

**3.3 በአስተዳደር ተግባራት ላይ የቁጥጥር ውክልና በሚሰጥበት ጊዜ በድርጅቱ እና በአገሬው ተወላጆች መካከል ያለው አስገዳጅ ስምምነት በነጻ፣ በቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት ይጠናቀቃል። ስምምነቱ የቆይታ ጊዜውን፣ ለዳግም ድርድር ዕድል የሚሰጥ፣ የእድሳት፣ የማቋረጥ፣ የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን እና ሌሎች ውሎችን እና ሁኔታዎችን ይገልፃል። ስምምነቱ የድርጅቱን የአገሬው ተወላጆች* የስምምነቱን ውሎችና ሁኔታዎች መፈጸማቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

ደረጃ አዘጋጆች የአገሬው ተወላጆች* በጽሑፍ ወይም በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ* ተሳትፎ* በሚመርጡት ሌላ ፎርማት* አስገዳጅ ስምምነቶችን* ለማፅደቅ መምረጥ እንደሚችሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት አመልካቾችን* ያዘጋጃሉ።

አስገዳጅ የሆኑ ስምምነቶች* ባህላዊ መስፈርቶችን የሚያንጸባርቁ ሲሆኑ በቃልና በክብር ስርዓቶች ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይችላሉ፤ እነዚህ ስምምነቶች በአገሬው ተወላጆች* ዘንድ በጽሑፍ የተደረጉ ስምምነቶች በተግባርም ሆነ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት በማይኖራቸው ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

የአገሬው ተወላጆች* በራሳቸው ምክንያቶች ነፃ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* ለመስጠት እና/ወይም ቁጥጥርን ለማስተላለፍ የማይፈልጉ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመገንዘብ የአገሬው ተወላጆች* ለአስተዳደር ተግባራት በተለየ መንገድ ድጋፍ ለመስጠት መምረጥ ይችላሉ (አመልካች 3.3.1 እና 3.3.2) ።

3.3.1 የአስተዳደር ተግባራት ቁጥጥር በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ* ተሳትፎ ላይ በመመርኮዝ በነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* የተሰጠ ከሆነ፣ አስገዳጅ ስምምነቱ* የቆይታ ጊዜውን፣ እንደገና ለመደራደር፣ ለማደስ፣ ለማቋረጥ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እና ሌሎች ውሎችን ይዟል።

3.3.2 የአስገዳጅ ስምምነቶች መዝገቦች ተጠብቀዋል።

3.3.3 አስገዳጅ ስምምነቱ* የድርጅቱን የአገሬው ተወላጆች* የስምምነቱን ውሎችና ሁኔታዎች መፈጸማቸውን እንዲከታተሉ የሚያስችል ድንጋጌ ይዟል።

***አረጋጋጮች፡-***

የFPIC አስገዳጅ ስምምነቶች አብሮ ተያይዟዋል።

**3.4 ድርጅቱ በተባበሩት መንግስታት ለአገሬው ተወላጆች መብት መግለጫ (2007) እና ILO ኮንቬንሽን 169 (1989) በተደነገገው መሠረት የአገሬው ተወላጅ ሕዝቦች* መብቶች፣ ልማዶችና ባህልን* እውቅና ይሰጣል እንዲሁም ይደግፋል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

ደረጃ አዘጋጆች የተባበሩት መንግስታት ለአገሬው ተወላጆች መብቶች መግለጫ (2007) እና ILO ስምምነት 169 (1989) መስፈርቶች በብሔራዊ ደረጃዎች እና በጊዜያዊ ብሄራዊ ደረጃዎች ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣሉ። ይህ መስፈርት የተባበሩት መንግስታት ለአገሬው ተወላጆች መብቶች መግለጫ (2007) እና ILO ኮንቬንሽን 169 (1989) በአገሬው ተወላጆች እና ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች መካከል ያለውን መብቶች፣ ልማዶች እና ባህል እንዲሁም መንፈሳዊ ግንኙነትን በግልፅ የሚሸፍኑ አንቀጾችን አስመልክቶ ነው።

ይህ መስፈርት* የተባበሩት መንግስታት መግለጫን ያልደገፉ እና/ወይም የአለምአቀፍ የስራ ድርጅት ኮንቬንሽን 169* ያላጸደቁ አገራትና ግዛቶችም ይሠራል። በዚህም ምክንያት የዚህ መስፈርት* መሟላት ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች * በሚገኝበት አገር ወይም ስልጣን ውስጥ ያለው የድርጅቱ* የሕግ ግዴታዎች ሊበልጥ ይችላል።

ይህ መስፈርት* ከህግ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ የ FSC ልዩ ሂደቶች ይተገበራሉ (የ FSC-STD-20-007 የደን አስተዳደር ግምገማዎችን ይመልከቱ) ። እንዲህ ዓይነቶቹ ግጭቶች መርሆዎችን* እና መስፈርቶችን* እና ህግን በአንድ ጊዜ ማክበር የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ናቸው ተብለው ይተረጎማሉ (ምንጭ: FSC-STD-01-001 V5-2) ።

በዚህ መስፈርት ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የ ILO ስምምነት 169 አንቀጾች ከተወሰነ ብሄራዊ ህግ ጋር ይቃረናሉ (አመልካች 3.4.1) ምሳሌ ሊሆን ይችላል። እንደዚህ መስፈርት* መሠረት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የአለም ሥራ ድርጅት ILO* 169 አንቀጾች ከተወሰነ ብሔራዊ ሕግ ጋር የሚጋጩ መሆናቸው አንድ ምሳሌ ነው (አመልካች*3.4.1)

3.4.1 በUNDRIP እና ILO ስምምነት 169 የተገለጹት የአገሬው ተወላጆች መብቶች፣ ልማዶች እና ባህል በድርጅቱ አልተጣሱም።

3.4.2 በUNDRIP እና በ ILO ኮንቬንሽን* 169 እንደተገለጸው የአገሬው ተወላጆች መብቶች፣ ልማዶችና ባህል* በድርጅቱ* እንደተጣሱ የሚጠቁም ማስረጃ በሚገኝበት ጊዜ፣ እነዚህ መብቶች፣ ልማዶችና ባህል* ለአገሬው ተወላጆች* እንዲመለሱ የሚደረጉ እርምጃዎችን ጨምሮ ሁኔታው በጽሑፍ ይቀርባል።

***አረጋጋጮች:***

ከአገሬው ተወላጆች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።

**3.5 ድርጅቱ የአገሬው ተወላጆችን በማሳተፍ ልዩ ባህላዊ፣ *ሥነ-ምህዳራዊ፣* ኢኮኖሚያዊ፣ *ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች* እና የአከባቢ ተወላጆች *ህጋዊ ወይም ልማዳዊ መብቶች ያሏቸው ቦታዎችን* ይለያል። እነዚህ ልዩ ቦታዎች የሆኑት በድርጅቱ እና በአስተዳደሩ እውቅና ያገኛሉ እና/ወይም ከእነዚህ ተወላጆች ጋር በመገናኘት የጥበቃ ስምምነት ላይ መድረስ አለባቸው።**

3.5.1 የአገሬው ተወላጆች* ሕጋዊ* ወይም ልማዳዊ መብቶች* ያላቸውን ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች በባህል ተገቢ* ተሳትፎ* ይለያሉ።

3.5.2 እንዲህ ያሉ ቦታዎችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎች ከባህል አንጻር ተገቢ* በሆነ መንገድ ከአገሬው ተወላጆች ጋር* በመተባበር ይስማማሉ፣ ይመዘገባሉ እንዲሁም ይተገበራሉ። የአገሬው ተወላጆች* በዶክመንት ወይም በካርታ ላይ የተገለጹ ቦታዎችን አካላዊ መለያ መስጠት የቦታዎቹን ዋጋ ወይም ጥበቃ* አደጋ ላይ እንደሚጥል ሲወስኑ ሌሎች መንገዶች ይጠቀማሉ።

3.5.3 ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች አዲስ ሲታዩ ወይም ሲገኙ ከአገሬው ተወላጆች ጋር የጥበቃ እርምጃዎች እስኪስማሙ ድረስ የአካባቢው እና ብሔራዊ ሕጎች* በሚወስዱት መሠረት በአካባቢ የሚደረግ የማስተዳደር ተግባራት ወዲያውኑ ያቆማሉ።

***አረጋጋጮች:***

ካርታዎች፤ የሥራ ጣቢያዎች ምርመራ&ከአገሬው ተወላጆች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።

**3.6 ድርጅቱ* የአገሬው ተወላጆች* ባህላዊ እውቀታቸውን* የመጠበቅና የመጠቀም መብታቸውን* ይጠብቃል፤ እንዲሁም የአካባቢው ማህበረሰቦች* እንዲህ ዓይነቱን እውቀትና የአዕምሯዊ ንብረታቸውን* በመጠቀም ካሳ ይከፍላቸዋል። እንደ መስፈርት 3.3 መሠረት አንድ አስገዳጅ ስምምነት* ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በድርጅቱ* እና በአገሬው ተወላጆች* መካከል እንዲህ ዓይነቱ አጠቃቀም በነፃ፣ በቅድሚያ እና በመረጃ በተደገፈ ስምምነት* እንዲካሄድ ይደረጋል፤ ይህ ስምምነት* የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች* ጥበቃ ጋር የሚስማማ ይሆናል።**

3.6.1 ባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የሚደረግላቸው እና ጥቅም ላይ የሚውሉት የዚያ ባህላዊ እውቀት ባለቤቶች እና አእምሯዊ ንብረታቸው እውቅና ያላቸው የነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ፈቃዳቸውን በማያያዝ ስምምነት ሲሰጡ ብቻ ነው።

NTFP 3.6.1.1 የአገሬው ተወላጆች* የ NTFPs ባህላዊ ዕውቀት* እና የአዕምሯዊ ንብረት* ጥበቃ የሚደረግላቸውና የሚጠቀሙት የእነዚህ ባህላዊ ዕውቀቶች* እና የአዕምሯዊ ንብረት* እውቅና ያላቸው ባለቤቶች ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ* ስምምነታቸውን* አስገዳጅ በሆነ ስምምነት* ሲያቀርቡ ብቻ ነው።

3.6.2 የአገሬው ተወላጆች* በባህላዊ እውቀት* እና በአዕምሯዊ ንብረት* አጠቃቀም ላይ በነፃ፣ በቅድመ እና በመረጃ በተደገፈ መስማማት* የተደረሰውን አስገዳጅ ስምምነት* መሠረት ክፍያ ያገኛሉ።

***አረጋጋጮች፡***

በግልጽ የተመዘገበ የFPIC ሂደት፣ አስገዳጅ ስምምነቶች በቦታቸው ላይ ይገኛሉ።

## ***መርህ.4 የማህበረሰብ ግንኙነቶች***

ድርጅቱ የአካባቢ ማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋል።

**4.1 ድርጅቱ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ ያሉትን የአካባቢ ማህበረሰቦችን እና በአስተዳደር ተግባራት የተጎዱትን ይለያል። ድርጅቱ ከነዚህ ማህበረሰቦች ጋር በመገናኘት የይዞታ መብቶቻቸውን፣ የደን ሃብትና የስነ-ምህዳር አገልግሎት የማግኘትና የመጠቀም መብቶቻቸውን፣ ልማዳዊ መብቶቻቸውን፤ ህጋዊ መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪም ድርጅቱ እነዚህን መብቶች አስመልክቶ የሚከራከሩባቸውን ቦታዎች ይለያል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

ይህ መመዘኛ ከደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ጥቅማ ጥቅሞችን፣ ምርቶች ወይም የስነ-ምህዳር አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲፈቀድላቸው ፍትሃዊ እና ህጋዊ የይገባኛል ጥያቄ ያላቸውን ማህበረሰቦች መለየት ይጠይቃል። ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ በማዋል የመሬት፣ የደን እና ሌሎች ሃብቶች መብታቸውን ያረጋገጡ እና እንዲሁም ይህን ያላደረጉትን (ለምሳሌ በግንዛቤ እጥረት ወይም በስልጣን ማነስ) ይገኙበታል።

በአስተዳደር ተግባራት የተጎዱት የአከባቢ ማህበረሰቦች ከደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች አጎራባች እና ርቀው የሚገኙና በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ምክንያት አሉታዊ ተጽእኖ የሚያጋጥማቸውን ያጠቃልላል (አመልካች 4.1.1) ።

ከሕጋዊ መሬት ይዞታ ጋር በተገናኘ የአከባቢ ማህበረሰቦች አለመግባባቶችን ለመፍታት መመዘኛ 1.6 ላይ የተገልጽውን ይመልከቱ፤ እና 4.6 ውስጥ ያሉትን መስፈርቶችና ከአስተዳደር ተግባራት ተጽእኖዎች ጋር የሚዛመዱ አመልካች (4.1.2) መከተል አለባቸው።

4.1.1 ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች የሚገኙ የአከባቢ ማህበረሰቦች እና በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉ ተለይተዋል።

4.1.2 በ4.1.1 ውስጥ በተገለፀው መሠረት፣ ከአከባቢው ማህበረሰቦች ጋር አግባብነት ባለው ባህላዊ መስተጋብር የሚከተሉት በሰነድ እና/ወይም በካርታ ተቀርፀዋል፡-

1) የይዞታ ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው፤
2) ህጋዊ እና ልማዳዊ የደን ሀብቶች እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶች የመጠቀም መብት፤
3) ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው እና ተፈጻሚነት ያላቸው ግዴታዎች፤
4) እነዚህን መብቶች እና ግዴታዎች የሚደግፉ ማስረጃዎች፤
5) በአከባቢው ማህበረሰቦች ፣ መንግስታት እና/ወይም ሌሎች መካከል የመብት ክርክር የሚካሄድባቸው አካባቢዎች፤
6) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እና ተከራካሪ መብቶች በድርጅቱ የሚቀርቡበት መንገዶች ማጠቃለያ፤ እና
7) የአከባቢው ማህበረሰቦች ምኞቶች እና ግቦች ከአስተዳደር ተግባራት፣ ያልተነኩ የደን ገፅታዎች እና ማህበረሰቦች ባህላዊ ገፅታ ጋር የተያያዙ።

NTFP 4.1.2.1 ውስጥ በተገለፀው መሠረት፣ ከአከባቢው ማህበረሰቦች ጋር አግባብነት ባለው ባህላዊ መስተጋብር የሚከተሉት በሰነድ እና/ወይም በካርታ ተቀርፀዋል፡-

1) የደን መሬት ይዞታ ህጋዊ እና ባህላዊ መብቶቻቸው፤
2) እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶች ህጋዊ እና ልማዳዊ የመጠቀም መብት፤
3) የእነርሱ ህጋዊ እና የልማዳዊ መብቶች እና ተፈጻሚነት ያላቸው ግዴታዎች፤
4) እነዚህን መብቶች እና ግዴታዎች የሚደግፉ ማስረጃዎች፤
5) በአከባቢው ማህበረሰቦች፣ መንግስታት እና/ወይም ሌሎች መካከል የመብት ክርክር የሚካሄድባቸው አካባቢዎች፤
6) ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶች እና የተከራከሩበት መብቶች እና በድርጅቱ የሚቀርቡበት የተፈቱበት መንገዶችና ማጠቃለያ፤
7) ከአስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ የአከባቢው ማህበረሰቦች ምኞቶች እና ግቦች።

**አረጋጋጮች:-**

የማህበረሰብ መለያ ሂደት መዝገብ ዝርዝር፤ ተለይተው የታወቁ ማህበረሰቦች ዝርዝር፤ በአመልካች 4.1.2 ከተዘረዘሩት 1-7 ጉዳዮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል የሚያሳይ በግልፅ የተመዘገበ ተሳትፎ ሂደት።

**4.2 ድርጅቱ* የአከባቢው ማህበረሰቦች* ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ ወይም ከእሱ ጋር በተያያዘ በሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት ላይ ቁጥጥርን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ሕጋዊ* እና ልማዳዊ* መብቶች* እውቅና ይሰጣል እንዲሁም ያከብራል።* የአከባቢው ማህበረሰቦች* የአስተዳደር ተግባራትን ለመቆጣጠር የሶስተኛ ወገን ውክልና ለመስጠት ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* ያስፈልጋል።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

ደረጃ አዘጋጆች ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ፈቃድ የማግኘት መብት ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ ለተቋቋሙ ህጋዊ ወይም ልማዳዊ መብቶች ላላቸው የአካባቢ ማህበረሰቦች ብቻ መሰጠቱን ለማረጋገጥ አመልካቾችን ማዘጋጀት አለባቸው። የአካባቢው ማህበረሰቦች ነፃ፣ ቅድመ እና መረጃ የተገኘበት ስምምነት* የሚተገበርበት ቦታ ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ላሉት መብቶች ብቻ የተወሰነ ሲሆን የአስተዳደር እርምጃዎች በእነዚህ መብቶች ላይ ተጽዕኖ በሚኖራቸው መጠን ብቻ ነው (አመልካች* 4.2.4)።

የደረጃ አዘጋጆች መልካም እምነት* በILO ኮንቬንሽኖች* ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ሆኖ እንዲታወቅ እና እንደ ኦዲት የሚደረግለት አካል እንዲታወቅ ያደርጋሉ (አመልካች 4.2.5) ።

4.2.1 ባህላዊ አግባብ ባለው*ተሳትፎ* የአካባቢው ማህበረሰቦች* መቼ፣ የት እና እንዴት አስተያየታቸውን ሊሰጡና መብቶቻቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን የአስተዳደር ተግባራትን እንዴት አስተያየት እንደሚሰጡና ማሻሻያዎችን እንደሚጠይቁ መረጃ ያገኛሉ።

4.2.2 የአከባቢው ማህበረሰቦች* በህጋዊ* እና በባህላዊ* የቁጥጥርና የአስተዳደር ተግባራት የመጠበቅ መብታቸው በድርጅቱ አይጣስም።

4.2.3 ከአስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ የአካባቢው ማህበረሰቦች ሕጋዊ* እና ልማዳዊ መብቶች* የተጣሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ሲኖር ሁኔታው አስፈላጊ ከሆነ በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ* በሆነ* ተሳትፎ* እና/ወይም በ1፣6 ወይም በ4.6 መስፈርት* በተጠየቀው የክርክር መፍቻ* ሂደት ይስተካከላል።

4.2.4 ነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* በአካባቢው ማህበረሰቦች* የሚሰጥ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን የሚያካትት ሂደት በመጠቀም የተለዩ መብቶቻቸውን የሚነኩ የአስተዳደር ተግባራትን ከማካሄድ በፊት ነው፡-

1) የአካባቢው ማህበረሰቦች ሀብቱን በሚመለከት መብታቸውን እና ግዴታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤
2) በኢኮኖሚያዊ ፣ በማህበራዊ እና በአካባቢያዊ ሁኔታዎች የሀብቱን ዋጋ ለአካባቢው ማህበረሰቦች በደንብ ማሳወቅ ፤
3) የአካባቢው ማህበረሰቦች* መብታቸውን እና ሀብታቸውን ለመጠበቅ በሚያስፈልገው መጠን ለታቀዱት የአስተዳደር ተግባራት ፈቃዳቸውን የመከልከል ወይም የመቀየር መብታቸውን ማሳወቅ*፤ እና
4) ለአካባቢው ማህበረሰቦች ወቅታዊ እና የወደፊት የታቀዱ የደን አስተዳደር ተግባራትን ማሳወቅ ።

4.2.5 በነፃ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ስምምነት* ሂደት እስካሁን ድረስ የ FPIC* ስምምነት ካልተደረገ ድርጅቱ* እና የተጎዱት የአካባቢው ማህበረሰቦች * በጋራ በስምምነት የ FPIC* ሂደት ውስጥ ገብተዋል፤ ይህ ሂደት በመልካም እምነት* እየተከናወነ ሲሆን ማህበረሰቡም በዚህ ስምምነት ረክቷል።

**አረጋጋጮች:**

ከማኅበረሰቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፣ የአለመግባባቶች የተመዘገቡበት መረጃ፤ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤ የ FPIC ሂደት መዝገብ፤ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።

**4.3 ድርጅቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ፣ ተቋራጮችና አቅራቢዎች የሥራ ዕድል፣ ስልጠናና ሌሎች አገልግሎቶችን በአስተዳደር እንቅስቃሴው ስፋት* እና ጥንካሬ* የሚመጥን ምክንያታዊ* ዕድል ይሰጣል።**

4.3.1 በመነጋገርና በመወያየት ምክንያታዊ* ዕድሎች ለአካባቢያዊ ማህበረሰቦች*፣ ለአካባቢያዊ ተቋራጮችና ለአካባቢያዊ አቅራቢዎች ይተላለፋሉ፤

1) ሥራ፤
2) ስልጠና፤ እና
3) ሌሎች አገልግሎቶች።

SLIMF 4.3.1.1 ድርጅቱ ለአካባቢው ነዋሪዎችና አገልግሎቶች ቅድሚያ ይሰጣል

***አረጋጋጮች:***

ለአከባቢው ማህበረሰብ ያስቀደመ ግዥ እና ቅጥር ፖሊሲ፤ የኮንትራክተሮች ዝርዝር፤ ለህብረተሰቡ የተሰጡትን ዕድሎች የሚገልጽ መረጃ፤ ከሠራተኞች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ የስልጠና መዝገቦች

**4.4 ድርጅቱ* ከአካባቢው ማህበረሰቦች* ጋር በመተባበር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገታቸው ላይ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ተጨማሪ ተግባራትን በማከናወን የአስተዳደሩ ተግባራት* መጠንና*፣ ጥንካሬ* ፣ እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖን የሚመጥን ተግባር ይሰራል።**

4.4.1 ለአካባቢያዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚሆኑ ዕድሎች በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ መንገድ ከየአካባቢው ማህበረሰቦች* እና ከሌሎች አግባብነት ያላቸው ድርጅቶች ጋር በመሳተፍ ተለይተዋል።

SLIMF 4.4.1.1 ድርጅቱ ለአካባቢያዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚሆኑ ዕድሎችን ይለያል እንዲሁም ተግባራዊ ያደርጋል።

4.4.2 ፕሮጀክቶች እና ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች የሚተገበሩ እና/ወይም የሚደገፉ ሲሆን እነዚህም ለአካባቢያዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አስተዋፅኦ የሚያደርጉና የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖን የሚመጥን ነው።

SLIMF 4.4.2 ድርጅቱ የአገር ውስጥ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ለመጠቀም ቅድሚያ ይሰጣል።

***አረጋጋጮች:***

እድሎችን የመለየት ሂደት ተመዝግቧል፤ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮጀክቶች ምዝገባ እና የተጠቃሚዎች ቁጥር

**4.5 ድርጅቱ* ከአካባቢው ማህበረሰቦች* ጋር በመተባበር፣ በአካባቢው ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሰውን ከፍተኛ* አሉታዊ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመለየት፣ ለማስወገድና ለመቀነስ እርምጃ ይወስዳል። የተወሰደው እርምጃ ከነዚህ እንቅስቃሴዎች ስፋት፣ ጥንካሬና አደጋ* እንዲሁም ከአሉታዊ ተፅዕኖዎች ጋር ተመጣጣኝ ነው።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:-***

*ይህ መስፈርት* ድርጅቱ* ለአካባቢያዊ ማህበረሰቦች* አገልግሎቶችን እንዲያቀርብና በዚህም የአካባቢውን ንግዶች ከሚሰጡት አገልግሎቶች ጋር እንዲወዳደር አይከለክልም፤ ለምሳሌ የትራንስፖርት አገልግሎት ወይም የድርጅት መደብሮች ለሰራተኞች ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ሰዎችም ክፍት ናቸው።*

*የደረጃ አዘጋጆች ድርጅቱ ለተጎዱት ማህበረሰቦች የሚያስከትለውን አሉታዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ አስተዋፅኦ የማድረግ ኃላፊነት ያለበትን ደረጃ ለመወሰን አመላካቾችን* ያዘጋጃሉ (መረጃ አመልካች* 4.5.1) ።*

4.5.1 በባህላዊ አግባብ ከአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር በመገናኘት የአስተዳደር ተግባራት ከፍተኛ* አሉታዊ* ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን ለመለየት፣ ለማስወገድና ለመቀነስ የሚረዱ እርምጃዎች ይተገበራሉ።

NTFP 4.5.1.1 በባህላዊ አግባብ ከአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር በመገናኘት የአስተዳደር ተግባራት እንጨት-ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ጨምሮ ከፍተኛ* አሉታዊ* ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን ለመለየት፣ ለማስወገድና ለመቀነስ የሚረዱ እርምጃዎች ይተገበራሉ።

NTFP 4.5.1.2 የ NTFPs ምርት እና አሰባሰብ ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ አከባቢያዊ ጥቅሞች (ለመድኃኒትነት፣ ለምግብ ፣ለእደ ጥበብ ፣ ወዘተ) እና የሚሰበሰቡበት ቦታ ዓይነት (በግለሰብ መኖሪያ ቤቶች ዙሪያ ፣ በገጠር ወይም በጫካ ውስጥ) መገምገምን ያካትታል።

SLIMF 4.5.1.1 በአስተዳደር ተግባራት የተጎዱ ማህበረሰቦች ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ማረጋገጥ።

SLIMF 4.5.1.2 በጎረቤቶች እና በአጎራባች የመሬት ባለቤቶች ጥያቄ ላይ እነዚህ እርምጃዎች ለእነሱ ይነገራቸዋል ።

***አረጋጋጮች፡***

*ወቅታዊ የክትትል ሪፖርቶች፤ የተመዘገቡ የመቀነስ/mitigation/ እርምጃዎች፤ የመቀነስ እርምጃዎች የአፈፃፀም መዝገብ።*

4.6 ድርጅቱ* ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር* ቅሬታዎችን ለመፍታት እና የአካባቢው ማህበረሰቦች* እና ግለሰቦች የአመራር እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ በተመለከተ ፍትሃዊ ካሳ* ለማቅረብ የሚያስችል አሠራር ይኖረዋል።

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

*የደረጃ አዘጋጆች የደረጃ አሰጣጥ መስፈርት* 7.6 መስፈርቶችን በመከተል ለባህል ተስማሚ የሆነ* የግጭት አፈታት* ሂደት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ዘዴ ያዘጋጃሉ።*

4.6.1 በአካባቢው ካሉ ማህበረሰቦች ጋር በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ በሆነ* ተሳትፎ* የተገነባ በይፋ የሚገኝ* የክርክር* አፈታት ሂደት ተግባራዊ ተደርጓል።

4.6.2 የአስተዳደር ተግባራት ተፅዕኖዎች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች በወቅቱ ምላሽ ይሰጣሉ* እና መፍትሄ ያገኛሉ ወይም በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ይገኛሉ።

4.6.3 የአስተዳደር ተግባራት ተፅዕኖን የሚመለከቱ ቅሬታዎች ወቅታዊ መዝገብ ተይዟል፣ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡

1) ቅሬታዎችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች፤
2) ፍትሃዊን ጨምሮ የሁሉም አለመግባባቶች የመፍታት ሂደቶች ውጤቶች ማካካሻ ለአካባቢ ማህበረሰቦች እና ግለሰቦች፤ እና
3) ያልተፈቱ አለመግባባቶች፤ ያልተፈቱ ምክንያቶች እና እንዴት መፍትሄ ያገኛሉ።

4.6.4 አለመግባባቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ክዋኔዎች ይቆማሉ፡-

1) ከፍተኛ መጠን፤
2) ከፍተኛ ቆይታ፤ ወይም
3) ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ፍላጎቶች ያካተተ

***አረጋጋጮች፡***

*የተሰነደ የግጭት አፈታት ሂደት ይኖራል፤ ወቅታዊ የሆነ የቅሬታ መዝገብ፤ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።*

**4.7 ድርጅቱ የአካባቢው ማህበረሰቦችን በማሳተፍ ልዩ ባህላዊ፣ *ሥነ-ምህዳራዊ፣* ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች እና የአካባቢው ማህበረሰቦች ህጋዊ ወይም ልማዳዊ መብቶች ያሏቸው ቦታዎችን ይለያል። እነዚህ ልዩ ቦታዎች የሆኑት በድርጅቱ እና በአስተዳደሩ እውቅና ያገኛሉ እና/ወይም ከእነዚህ ማህበረሰቦች ጋር በመገናኘት የጥበቃ ስምምነት ላይ መድረስ አለባቸው።**

4.7.1 የአካባቢ ማህበረሰቦች ሕጋዊ* ወይም ልማዳዊ መብቶች* ያላቸውን ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች በባህል ተገቢ* ተሳትፎ* ተለይተው በድርጅቱ እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

4.7.2 እንዲህ ያሉ ቦታዎችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎች ከባህል አንጻር ተገቢ* በሆነ መንገድ ከአካባቢው ማህበረሰቦች* ጋር* በመተባበር ይስማማሉ፣ ይመዘገባሉ እንዲሁም ይተገበራሉ። የአካባቢ ማህበረሰቦች* በዶክመንት ወይም በካርታ ላይ የተገለጹ ቦታዎችን አካላዊ መለያ መስጠት የቦታዎቹን ዋጋ ወይም ጥበቃ* አደጋ ላይ እንደሚጥል ሲወስኑ ሌሎች መንገዶች ይጠቀማሉ።

4.7.3 ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎች አዲስ ሲታዩ ወይም ሲገኙ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር የጥበቃ እርምጃዎች እስኪስማሙ ድረስ የአካባቢው እና ብሔራዊ ሕጎች* በሚወስዱት መሠረት በአካባቢ የሚደረግ የማስተዳደር ተግባራት ወዲያውኑ ያቆማሉ።

***አረጋጋጮች፡***

*ባህላዊ ቦታዎች በካርታዎች ላይ በግልፅ የተከለሉ፤ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ የተከለሉ ቦታዎች፤ የተሳትፎ ሂደቶች በግልጽ ተመዘግበዋል፤ ካርታዎች፤ የጥበቃ እርምጃዎች ተሰንደዋል፤ አዲስ የታወቁ ቦታዎች ተመዘግበዋል*

**4.8 ድርጅቱ* የአካባቢው ማህበረሰቦች* ባህላዊ እውቀታቸውን* የመጠበቅና የመጠቀም መብታቸውን* ይጠብቃል፤ እንዲሁም የአካባቢው ማህበረሰቦች* እንዲህ ዓይነቱን እውቀትና የአዕምሯዊ ንብረታቸውን* በመጠቀም ካሳ ይከፍላቸዋል። እንደ መስፈርት 3.3 መሠረት አንድ አስገዳጅ ስምምነት* ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በድርጅቱ* እና በአካባቢው ማህበረሰቦች* መካከል እንዲህ ዓይነቱ አጠቃቀም በነፃ፣ በቅድሚያ እና በመረጃ በተደገፈ ስምምነት* እንዲካሄድ ይደረጋል፤ ይህ ስምምነት* የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች* ጥበቃ ጋር የሚስማማ ይሆናል።**

4.8.1 ባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የሚደረግላቸው እና ጥቅም ላይ የሚውሉት የዚያ ባህላዊ እውቀት ባለቤቶች እና አእምሯዊ ንብረታቸው እውቅና ያላቸው የነፃ፣ ቅድመ እና በመረጃ የተደገፈ ፈቃዳቸውን በማያያዝ ስምምነት ሲሰጡ ብቻ ነው።

4.8.2 የአካባቢ ማህበረሰቦች* በባህላዊ እውቀት* እና በአዕምሯዊ ንብረት* አጠቃቀም ላይ በነፃ፣ በቅድመ እና በመረጃ በተደገፈ መስማማት* የተደረሰውን አስገዳጅ ስምምነት* መሠረት ክፍያ ያገኛሉ።

NTFP 4.8.2.1 የአካባቢው ማህበረሰቦች* በ NTFPs አጠቃቀም ላይ ባህላዊ ዕውቀትን* እና የአዕምሯዊ ንብረት* ለመጠቀም በነፃ፣ በቅድመ እና በመረጃ በተደገፈ ስምምነት* በተደረሰባቸው አስገዳጅ ስምምነት* መሠረት ይካሳሉ።

***አረጋጋጮች፡***

አስገዳጅ ስምምነት ተቀምጧል፤ በግልጽ የተመዘገበ የ FPIC ሂደት፤ ከአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።

## ***መርህ.5 ከደን የሚገኙ ጥቅሞች***

ድርጅቱ* ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች የረጅም ጊዜ* ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን* እና ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል በርካታ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በብቃት ያስተዳድራል።

**5.1 ድርጅቱ* ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙትን ሀብቶችና የሥነ ምህዳር አገልግሎቶች* በመጠቀም የአካባቢውን ኢኮኖሚ ለማጠናከርና ለማባዛት፣ ከአስተዳደር ተግባራት መጠን* እና ጥንካሬ* ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ የተለያዩ ጥቅሞችን እና/ወይም ምርቶችን ይለያል፣ ያመርታል ወይም ማምረት ያስችላል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

በዚህ መስፈርት ውስጥ የአስተዳደር ግቦች* የሚለው ቃል አጠቃቀሙ በመስፈርት* 7.1 (አመልካች* 5.1.2) ውስጥ ተብራርቷል።

የደረጃ አዘጋጆች የድርጅቱ ዋና የአስተዳደር ግቦች* ጥበቃ* ወይም ክለላ* ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው (አመልካች* 5.1.2)

5.1.1 የአከባቢውን ኢኮኖሚ ሊያጠናክሩና ሊያበዙ የሚችሉ ሀብቶችና የሥነ ምህዳር አገልግሎቶች* ተለይተዋል።

NTFP 5.1.1.1 ድርጅቱ የአከባቢውን ኢኮኖሚ ሊያጠናክሩና ሊያበዙ የሚችሉ የ NTFPs ይለያል።

SLIMF 5.1.1.1 ሥራ አስኪያጆች የአካባቢን ኢኮኖሚ ሊያጠናክሩ እና ዓይነቶችን ሊያበዙ የሚችሉ ልዩ ልዩ የግብአት እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶችን ይገነዘባሉ።

5.1.2 ከአስተዳደር ዓላማዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ የተገለጹት ጥቅሞችና ምርቶች በድርጅቱ* የሚመረቱና/ወይም ለሌሎች ለማምረት፣ የአካባቢውን ኢኮኖሚ ለማጠናከርና ለማባዛት የሚውሉ ናቸው።

NTFP5.1.2.1 ድርጅቱ የ NTFPs ማምረትና መሰብሰብን (በዘላቂ ገደቦች ውስጥ) ፣ ማቀነባበርን፣ የምርቱን ብዝሃነት በአከባቢ ደረጃ እና አዳዲስ ገበያዎችን ከአስተዳደር አላማው ጋር ማፈላለግ ያበረታታል።

SLIMF 5.1.2.1ሀ ከአስተዳደር ዓላማዎች ጋር በሚጣጣምና ወጥነት ባለው መልኩ፣ ተለይተው የሚታወቁ ጥቅሞች እና ምርቶች በድርጅቱ ይመረታሉ።

SLIMF 5.1.2.1ለ የተመረቱት ጥቅሞችና ምርቶች ለሌሎች ለማምረት፣ ለማጠናከርና ለማባዛት ተደራሽ ይሆናሉ።

5.1.3 ድርጅቱ የFSC ምህዳር አገልግሎቶችን የይገባኛል ጥያቄዎችን ሲጠቀም፣ ድርጅቱ በFSCPRO-30-006 ውስጥ የሚመለከታቸውን መስፈርቶች ማክበር አለበት።

***አረጋጋጮች፡***

የሀብት እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶች መዝገብ ይገኛል፤ የደን አያያዝና አጠቃቀም እቅድ ፤ የመነሻ ዳሰሳ ጥናቶች፤ በአገር ውስጥ ድርጅቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ የሀብቶች እና የስነ-ምህዳር አገልግሎቶች ዝርዝር፤ የአካባቢ ሀብቶችን እና NTFPs የሚጠቀሙ ድርጅቶች ዝርዝር ።

**5.2 ድርጅቱ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች በቋሚነትና ዘላቂነት ሊቆይ በሚችል ደረጃ ወይም ከዛ በታች ይሰበስባል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

*ደረጃ አዘጋጆች ቀደም ሲል ትንታኔው ጥቂት የሆነበት ወይም ያልተጠናቀቀበት እና/ወይም መረጃው ደካማ ወይም የሌለበት ከሆነ የእንጨት መሰብሰብ ደረጃን ለማስላት ትንታኔውን እንዴት ማጠናቀቅ እንደሚቻል ለአነስተኛ ደን ባለይዞታዎች ግልጽ መመሪያ ይሰጣሉ (መለኪያዎች 5.2.1 እና 5.2.2) ። በተጨማሪም የደረጃ አዘጋጆች የደን ምርታማነትን በተመለከተ ተገቢውን የቦታ እና የጊዜ ሚዛን ይወስናሉ።*

*ለትላልቅ እና በክልል የተበተኑ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች የማምረት መጠን ዓመታዊውን ምርት በአንድ ንዑስ ክፍል ውስጥ ማሰባሰብ እንደማይፈቅድ ለማረጋገጥ ደረጃ አዘጋጆች አመልካቾችን ማዘጋጀት አለባቸው፤ ወይም የትኛውም ዝርያ የድርጅቱን ሁሉንም ሌሎች የደረጃውና የዓመቱን የምርት መጠን የማሟላት ዘላቂነትን በሚጎዳ መንገድ መሆን የለበትም።*

*ደረጃ አዘጋጆች ከሁሉም ተሸሎ የሚገኝ መረጃ መጠቅም አስገዳጂ ሲሆን ለእያንዳንዱ አመላካች ከሁሉም ተሸሎ የሚገኝ መረጃ መለየት አለባቸው (መስፈርቶች 5.2፣ 6.1፣ 6.4፣ 6.5፣ 6.10፣ 9.1፣ 9.2) ።*

*በመስፈርት ደረጃ ላይ ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጡ መመሪያዎች ውስጥ የቀረቡት ዝርዝሮች የሚፈለጉትን መረጃዎች ምሳሌዎች (መስፈርት * 5.2) ወይም ከሁሉም ተሸሎ የሚገኙ መረጃዎችን ምንጮች (መስፈርት * 6.1 እና መርህ * 9) ይሰጣሉ ።*

*የደረጃ አዘጋጆች ድርጅቱ ለአመልካቾች 5.2.1 እና 5.2.4 የሚጠቀምበትን ከሁሉም ተሸሎ የሚገኝ መረጃ ይገልፃሉ። ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:*

- *ወቅታዊ የእድገት እና የምርት መረጃ፤*
- *ወቅታዊ የዳሰሳ ጥናት መረጃ፤*
- *በእሳት፣ በነፍሳት እና በበሽታ የመሳሰሉ የተፈጥሮ መቃወሶች ጨምሮ በደን መጥፋት የምርት መጠን እና የቦታ ስፋት መቀነስ*
- *በዚህ መስፈርት ውስጥ ያሉትን ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በሙሉ ማክበርን ከግምት ውስጥ ለማስገባት ያልተነኩ የደን ገጽታዎችን ዋና ቦታዎች ጨምሮ የምርት መጠን እና የቦታ ስፋት ቅነሳዎች።*

*ድርጅቱ* በአንድ ዓመት ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይ መጠን መቁረጥ ይችላል፣ ይህ መደበኛ ሌሎች መስፈርቶች በሙሉ ከተሟሉ እና ከአስር ዓመታት አማካይ ሲቆጠር የምርት መጠን ከሚፈቀደው መቁረጥ አይበልጥም።*

*የአስር ዓመት ጊዜ ገደብ የተለመደ ሲሆን፣ ልዩነቶች በብሔራዊ ደረጃ መረጋገጥ አለባቸው። የደረጃ አዘጋጆች በሀገር አቀፍ ደረጃ ደን የሚቆረጥበትን ዕድሜ * እና አሁን ባሉት የፕሮግራም ዑደቶች ላይ በመመርኮዝ ተገቢውን የተወሰነ ጊዜ ይወስናሉ ((አመልካች* 5.2.3)*

*ደረጃ አዘጋጆች ከተፈቀደላቸው የመቁረጥ ደረጃዎች (አመላካች 5.2.3) በላይ የሆነ ጊዜያዊ እና መደበኛ ያልሆነ ዓመታዊ የምርት መጠን ሊያስከትሉ የሚችሉ አስከፊ የተፈጥሮ መቃወሶች (እንደ ነፋስ ፣ እሳት እና ተባዮች ወረርሽኝ) ወይም የደን መልሶ ማቋቋም ግቦችን መለየት ይችላሉ ።*

*የደረጃ አዘጋጆች በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ ስጋት እንዳይፈጥር ለማረጋገጥ በአስተዳደር ተግባራት ሊያስከትሉ የሚችሉትን እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች በሀገር ውስጥ እና በክልል አውድ ውስጥ መለየት አለባቸው (አመልካች* 5.2.4)*

አደን፣ አሳ ማስገር እና ምርትን መሰብሰብን መቆጣጠር እና ማስተዳደር በመስፈርት 6.6 ተደራሽ ሆኗል። ሕገ-ወጥ አደን፣ አሳ ማስገር እና ምርትን መሰብሰብን መቆጣጠር በመስፈርት 1.4ተደራሽ ሆኗል።

5.2.1 የእንጨት መሰብሰብ ደረጃዎች በእድገትና ምርት፣ የደን መጠን ልኬት፣ የደን መጥፋት መጠን እና የስነ-ምህዳራዊ ሥርዓቶች ተግባር ጥገና በሁሉም ተሸሎ የሚገኝ መረጃ ትንተና ላይ የተመሠረተ ነው።

5.2.2 የእንጨት መሰብሰብ ደረጃ ትንታኔ ላይ በመመርኮዝ የእንጨት መሰብሰብ መጠን እድገትን እንዳይበልጥ በማረጋገጥ ጨምሮ በቋሚነት ሊቆይ ከሚችለው የመሰብሰብ መጠን የማይበልጥ ከፍተኛውን ዓመታዊ የመቁረጥ መጠን ይወሰናል

NTFP 5.2.2.1 የNTFPs ዘላቂነት ያለው የምርት መሰብሰብ ደረጃ በእድገትና በምርት ወቅታዊ ከሁሉ ተሸሎ የሚገኝ መረጃ ትንታኔ ላይ የተመሰረተ ነው።

NTFP 5.2.2.2 ለNTFPs ትክክለኛ ዓመታዊ ምርት መሰብሰብ መጠን ይመዘገባል።

5.2.3 ትክክለኛ አመታዊ የደን ምርት መሰብሰብ መጠን ይመዘገባል እናም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ያለው ምርት በ 5.2.2 ለተፈቀደው ተመሳሳይ ወቅት የሚከናወን የደን ምርት መሰብሰብ ከተፈቀደው የእንጨት መቁረጥ አይበልጥም።

5.2.4 በድርጅቱ ቁጥጥር ስር ለሆኑ ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ አገልግሎቶችና የደን ምርቶች* የማውጣት/ማንሳት ሥራ ዘላቂ ምርት የሚገኝበት ደረጃ ይገመታል እንዲሁም ይከበራል። ቀጣይነት ያለው የመሰብሰብ መጠን ከሁሉ ተሸሎ በተገኘው መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው።

NTFP 5.2.4.1 በድርጅቱ ቁጥጥር ስር ለሆኑ ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ NTFPs የማውጣት/ማንሳት ሥራ ዘላቂ ምርት የሚገኝበት ደረጃ ይገመታል እንዲሁም ይከበራል። ቀጣይነት ያለው የመሰብሰብ መጠን ከሁሉ ተሸሎ በተገኘው መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው።

NTFP 5.2.4.2 የNTFPs መሰብሰብ/ማምረት በዓመቱ ውስጥ በተገቢው ጊዜ ይከናወናል፡-

1) የዕፅዋትን ሀብቱን ውጤታማ አጠቃቀም ለማሳደግ፤
2) የአካባቢ ተፅእኖን ለመቀነስ&
3) ሊሰበሰቡ የሚችሉ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ የደረሱ/የበሰሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ።

NTFP 5.2.4.3 የ NTFPs ማምርትና መሰብሰብ በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በተመረጡ ዛፎች ወይም የደን ክፍሎች ብቻ የተገደበ ነው።

NTFP 5.2.4.4 ስለ NTFPs እድገትና ዳግም-ብቅለት አስተማማኝ መረጃ በማይኖርበት ግዜ ለወደፊቱ አስተዳደር ዝርዝር መረጃ ለመሰብሰብ ፕሮግራም አለ።

NTFP 5.2.4.5 የሁሉም የ NTFP የማምረትና መሰብሰቢያ ቦታዎች ካርታዎች አሉ።

***አረጋጋጮች፡-***

*ወቅታዊ የእድገት እና የምርት መረጃ፤ ወቅታዊ የዳሰሳ መረጃ፤ በደረቁና በጠፉ ዛፎች ምክንያት የሚከሰተውን የምርት መጠን እና የመሬት ስፋት መቀነስ እንዲሁም እንደ እሳት፤ ነፍሳት እና በሽታ የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች፤ እና በዚህ መስፈርት ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሌሎች መስፈርቶች ከምርት መጠን እና የመሬት ስፋት መቀነስ ጋር በተያያዘ፤ ትክክለኛ ዓመታዊ ምርት መዝገብ፤ የሚፈቀደው አመታዊ የሚቆረጠው የምርት መጠን።*

**5.3 ድርጅቱ* የድርጊቶች አዎንታዊ እና አሉታዊ ውጫዊ ውጤቶች* በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ ውስጥ መያዛቸውን ማሳየት ይኖርበታል*።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

*የማኔጅመንት ተግባራት ማህበራዊና አካባቢያዊ ወጪዎችና ጥቅሞች ብዙውን ጊዜ ከግምት ውስጥ የማይገቡ ሲሆን ውጫዊ ውጤቶች ተብለው ይጠራሉ። ውጫዊ ውጤቶች በእነዚህ መርሆዎች* እና መመዘኛዎች* መሠረት አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል፣ ለማቃለል፣ ለማደስ* ወይም ለማካካስ ስለሚያስፈልግ ወጪ ሊያስከትሉ ይችላሉ።*

*የደረጃ አዘጋጆች የፋይናንስ እቅድ ማውጣት እና ወጪዎችን መቆጣጠር በድርጅቱ* ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች* መከናወኑን ለማረጋገጥ አመልካቾችን* ያዘጋጃሉ። ከዚህ በታች ያለውን መስፈርት*5.5 ይመልከቱ።*

5.3.1 የአስተዳደር ተግባራት አሉታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል፣ ለማቃለል ወይም ለማካካስ የሚደረጉ ወጪዎች በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ውስጥ ይወሰናሉ እንዲሁም ይገለጻሉ።

NTFP 5.3.1.1 የNTFPs የአስተዳደር ተግባራት አሉታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል፣ ለማቃለል ወይም ለማካካስ የሚደረጉ ወጪዎች በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ውስጥ ይወሰናሉ እንዲሁም ይገለጻሉ።

SLIMF 5.3.1.1 *ሥራ አስኪያጆች የአስተዳድር ተግባራትን አሉታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል፣ ለመቀነስ ወይም ለማካካስ የሚደረጉ ወጪዎችን እንዲሁም በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ውስጥ መመዝገባቸውን ያውቃሉ።*

5.3.2 ከአስተዳደር ተግባራት አዎንታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖ ጋር የተያያዙ ጥቅሞች ተለይተው በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ውስጥ ተካትተዋል*።

NTFP 5.3.2.1 የNTFP አስተዳደር ተግባራት አዎንታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖ ጋር የተያያዙ ጥቅሞች ተለይተው በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ውስጥ ተካትተዋል*።

***አረጋጋጮች፡ -***

*ዓመታዊ በጀት እና የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ።*

**5.4 ድርጅቱ* የድርጅቱን* መስፈርቶች ለማሟላት አካባቢያዊ ማቀነባበሪያ፣ አካባቢያዊ አገልግሎቶች እና አካባቢያዊ እሴት መጨመርን ከመጠን፣ ከጥንካሬ እና ከአደጋ ጋር በማመጣጠን ይጠቀማል። እነዚህ አገልግሎቶች በአካባቢው የማይገኙ ከሆነ ድርጅቱ ለማቋቋም የሚረዳውን ሁሉ ያደርጋል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

*ደረጃ አዘጋጆች በዚህ መስፈርት ውስጥ "አካባቢያዊ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ። የዚህ መስፈርት* ዓላማ ድርጅቱ* ከድርጅቱ* ቀጥተኛ የሥራ ስምሪት ባሻገር ባሉ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች አማካኝነት ተጨማሪ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለማስፋፋት ነው። የሚፈለገው ውጤት ድርጅቱ* አግባብነት ያላቸውን የአካባቢ አገልግሎቶችና ምርቶች በመግዛት የአካባቢውን ኢኮኖሚ ማነቃቃት ወይም አግባብነት ያላቸውን አዳዲስ የአካባቢ አገልግሎቶች መፍጠርና አግባብነት ያላቸውን የአካባቢ ምርቶች አቅርቦት መደገፍ ነው። የአካባቢ አገልግሎት ሰጪዎች ቀድሞውኑ ባሉባቸው አካባቢዎች ከሌሎች የአካባቢ አገልግሎት ሰጪዎች ከመቅጠር በፊት እነዚህን ንግዶች መደገፍ ተመራጭ ነው።*

5.4.1 በተቻለ መጠን የአካባቢያዊ ምርቶችን፣ አገልግሎቶችን፣ ማቀነባበሪያዎችን እና የአካባቢያዊ የተጨማሪ እሴት መገልገያዎችን መጠቀም ቅድሚያ ይሰጣል።

NTFP 5.4.1.1 በተቻለ መጠን NTFPs በአካባቢያዊ የተጨማሪ እሴት ተቋማት ውስጥ ለማቀናበር ቅድሚያ ይሰጣል።

SLIMF 5.4.1.1 በአካባቢው የሚገኙ ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ማቀነባበሪያና የተጨማሪ እሴት መገልገያዎች በወጪ፣ በጥራትና በአቅም ከሌላ አካባቢ አማራጮች ጋር እኩል እስከሆኑ ድረስ ቅድሚያ ይሰጣል።

5.4.2 በአካባቢው የሚገኙ ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ማቀነባበሪያና የተጨማሪ እሴት መገልገያዎች በማይገኙበት ቦታ አቅም ለመፍጠርና ለማበረታታት ምክንያታዊ* ሙከራዎች ይደረጋሉ።

NTFP 5.4.2.1 በአካባቢው የሚገኙ ከNTFPs ጋር ተዛማች የሆኑ ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ማቀነባበሪያና የተጨማሪ እሴት መገልገያዎች በማይገኙበት ቦታ አቅም ለመፍጠርና ለማበረታታት ምክንያታዊ* ሙከራዎች ይደረጋሉ።

SLIMF 5.4.2.1 በአካባቢው የሚገኙ ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ማቀነባበሪያና የተጨማሪ እሴት መገልገያዎች በማይገኙበት ቦታ አቅም ለመፍጠርና ለማበረታታት ምክንያታዊ* ሙከራዎችን ማድረግ።

***አረጋጋጮች፡-***

የአካባቢ ማቀነባበሪያ እና የተጨማሪ እሴት ማሚያ ተቋማት መዝገብ፣ የተከናወኑ የአቅም ግንባታ ተግባራት መዝገብ፤ በድርጅቱ የአቅም ግንባታ ተነሳሽነት የሚደገፉ የአካባቢ ሰዎች እና መገልገያዎች ስም ዝርዝር፤ የኮንትራክተሮች እና የአገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር፤ የስልጠና መዝገቦች፤ የቅጥር ፖሊሲ እና የቅጥር መዝገቦች።

**5.5 ድርጅቱ* ለረጅም ጊዜ* ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት* ያለውን ቁርጠኝነት በመጠን፣ በጥንካሬ እና በስጋት/አደጋ የሚመጥን እቅድ እና ወጪ በማውጣት ያሳያል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ፡-***

በዚህ መስፈርት* ላይ የተጠቀሱት ወጪዎች ለምሳሌ የሚከተሉትን ወጪዎች ያካትታሉ፡-

- በመስፈርት 5.2 መሠረት ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ዝርያዎችን ከመጠን በላይ ከመጠቀም ወይም ከመጠን በላይ ያለፈ የደን ምርት መርጦ መሰብሰብ የመከላከል እርምጃዎች፤ እና
- መርሆች እና መሥፈርቶች* የሚጠየቁትን አሉታዊ ውጫዊ ተፅዕኖዎች* መከላከል፣ ማቃለል ወይም ማካካስ (መሥፈርት* 5.3ን ይመልከቱ)

5.5.1 ይህንን መስፈርት ለማሟላት እና የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነትን ለማረጋገጥ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድን ለመተግበር በቂ ገንዘብ ተመድቧል።

SLIMF 5.5.1.1 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚያስችል በጀት ተዘጋጅቷል።

5.5.2 ይህንን መስፈርት ለማሟላት እና የረጅም ጊዜ* ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱን* ለመተግበር ወጪዎች እና ኢንቨስትመንቶች ይደረጋሉ።

***አረጋጋጮች፡-***

የደን አያያዝና አጠቃቀም እቅድ፥ ዓመታዊ በጀት፥ ትክክለኛ ወጪዎች እና ኢንቨስትመንቶች መዝገብ፥ የድርጅቱ ኦዲት የተደረገባቸው አካውንቶች

## መርህ* 6 የአካባቢ እሴቶች* እና ተጽእኖዎች

ድርጅቱ ለደን አስተዳድር በተለዩ ቦታዎች ላይ የሥነ ምህዳራዊ አገልግሎቶችን እና የአካባቢያዊ እሴቶችን ያስከብራል፣ ይጠብቃል፣ እንዲሁም ወደ ነበሩበት ይመልሳል፤ በተጨማሪም አሉታዊ የሆኑ የአካባቢ ተፅዕኖዎች ካሉ ያስወግዳል፣ ይጠግናል ወይም ይቀንሳል።

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

የደረጃ አዘጋጆች ከመስፈርት* 6.1 እስከ 6.3 ያሉትን አመላካቾች* ፍሰት እንደሚከተለው ይጠብቃል፤

- **6.1 የአካባቢ እሴቶች ግምገማ**
- **6.2 የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ**
- **6.3 የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል ውጤታማ እርምጃዎችን መለየት እና ተግባራዊ ማድረግ**

የደረጃ አዘጋጆች በተገቢው ሁኔታ በመርህ ቁጥር 6 ላይ በተጠቀሱት አመላካቾች ውስጥ በሀገሪቱ ወይም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብርቅዬ እና በምጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን ዝርዝር (አባሪ መ) በግልፅ ያመለክታሉ።

6.1 ድርጅቱ* ለደን አስተዳድር በተለየ ቦታ ውስጥ ያሉ የአካባቢያዊ እሴቶችን* እና ከደን አስተዳድር በተለየ ቦታ ውጭ ያሉትን* በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉ እሴቶችን ይገመግማል። ይህ ግምገማ የሚከናወነው ከቁጥጥር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬና አደጋ* ጋር የሚመጣጠን እና አስፈላጊውን የጥበቃ* እርምጃ ለመወሰን እንዲሁም የእነዚህ ተግባራት ሊያስከትሉ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመለየት እና ለመከታተል በዝርዝር የተተነተነበት ደረጃ፣ ስፋት እና ድግግሞሽ ነው።

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

ድርጅቱ በ6.1.1 አመልካቾች መሰረት ለመተግብር እንድያስችል ደረጃዎችን የሚያወጣዉ አካል የሚጠቀመውን ከሁሉ ተሽሎ የተገኘን መረጃን ያገናዝባል። ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው -

- የአካባቢ እሴቶችን በተፈጥሮ ገጽታቸው ውስጥ የሚያሳዩ ወኪል ናሙና ቦታዎች
- የመስክ ዳሰሳ;
- ከአካባቢያዊ እሴቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የመረጃ ቋቶች
- ከአካባቢና ከክልል ባለሙያዎች ጋር የሚደረግ ምክክር፤
- ከአከባቢዉ ተወላጆች ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ እና የአከባቢ ተጽኖ ሊያገኛቸዉ የሚችል ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የአከባቢዉን ባህል ባማከለ መልኩ የምክክር መስተጋብር ማድረግ

6.1.1 ለደን አስተዳድር በተለየ ቦታ ውስጥ ያሉ የአካባቢ እሴቶችን* በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉበትን ለመለየት እንዲሁም ከአስተዳደር ክፍሉ ውጭ ያሉትን ለመለየት የተሻለ የሚገኝ መረጃን መጠቀም። ማስታወሻ: - የተሻለ የሚገኝ መረጃ* የሚከተሉትን ያካትታል:-

1) የአካባቢ እሴቶችን በተፈጥሮ ገጽታቸው ዉስጥ የሚታዩበት የወኪል ናሙና ቦታዎች

2) የመስክ ጥናቶች.

3) ከአካባቢያዊ እሴቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የመረጃ ቋቶች፣ ለምሳሌ:- በአቅራቢያዉ የሚገኝ የደን መዘክር እና ከክልል ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የተፈጥሮ ጥበቃ ስትራቴጂክ መረጃ

4) ከክልል እና አከባቢው ላይ ከሚገኙ ባለሙያዎች ጋር የሚደረግ ምክክር

5) ከአገሬው ተወላጆች ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ እና የአከባቢ ተጽኖ ሊያገኛቸዉ ከሚችል ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከባህል አንጻር ተገቢ የሆን ተሳትፎ ማድረግ

NTFP 6.1.1.1 ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ የአካባቢ እሴቶችን* ለመለየት እና በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉ ከሆነ ለደን አስተዳደር ከተለዩ ቦታዎች ውጭ ለመለየት ጥቅም ላይ ይውላል*። ማስታወሻ: - ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* የሚከተሉትን ያካትታል፡

1) የአካባቢ እሴቶችን በተፈጥሮ ገጽታቸው ዉስጥ የሚታዩበት የወኪል ናሙና ቦታዎች

2) የመስክ ዳሰሳ

3) ከአካባቢያዊ እሴቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የመረጃ ቋቶች፣ ለምሳሌ:- በአቅራቢያዉ የሚገኝ የደን መዘክር እና ከክልል ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የተፈጥሮ ጥበቃ ስትራቴጂክ መረጃ

4) ከክልል እና አከባቢው ላይ ከሚገኙ ባለሙያዎች ጋር የሚደረግ ምክክር

5) ከአገሬው ተወላጆች ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ እና የአከባቢ ተጽኖ ሊያገኛቸዉ ከሚችል ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከባህል አንጻር ተገቢ የሆን ተሳትፎ ማድረግ

SLIMF 6.1.1.1 ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ የአካባቢ እሴቶችን* ለመለየት እና በአስተዳደር ተግባራት ሊጎዱ የሚችሉ ከሆነ ለደን አስተዳደር ከተለዩ ቦታዎች ውጭ ለመለየት ጥቅም ላይ ይውላል*።

6.1.2 የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን* የሚመለከቱ ግምገማዎች በሚከተለው ዝርዝር እና ድግግሞሽ ይካሄዳሉ፤ ስለዚህ

1) የአስተዳደር ተግባራት በተለዩ የአካባቢ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ* በ6.2 መስፈርት መሠረት ሊገመገም ይችላል፤

2) ለአካባቢያዊ እሴቶች* የሚጋለጡ አደጋዎች* በመስፈርት* 6.2 መሰረት መለየት ይችላሉ

3) እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ አስፈላጊ የጥበቃ* እርምጃዎች እንደ በመስፈርት* 6.3 መሰረት መለየት ይችላሉ፤ እና፣

4) የአካባቢ ተፅዕኖዎችን ወይም ለውጦችን መከታተል በመርህ 8 መሠረት ሊከናወን ይችላል.

NTFP 6.1.2.1 ከ NTFP ጋር የተያያዙ የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን* የሚመለከቱ ግምገማዎች በሚከተለው ዝርዝር እና ድግግሞሽ ይካሄዳሉ፤ ስለዚህ

1) የአስተዳደር ተግባራት በተለዩ የአካባቢ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ* በ6.2 መስፈርት መሠረት ሊገመገም ይችላል፤

2) ለአካባቢያዊ እሴቶች* የሚጋለጡ አደጋዎች* በመስፈርት* 6.2 መሰረት መለየት ይችላሉ

3) እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ አስፈላጊ የጥበቃ* እርምጃዎች እንደ በመስፈርት* 6.3 መሰረት መለየት ይችላሉ፤ እና፣

4) የአካባቢ ተፅዕኖዎችን ወይም ለውጦችን መከታተል በመርህ 8 መሠረት ሊከናወን ይችላል.

SLIMF 6.1.2.1 የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን* የሚመለከቱ ግምገማዎች በሚከተለው ዝርዝር እና ድግግሞሽ ይካሄዳሉ።

*አራጋጋጮች: - መነሻ የአካባቢ ግምገማ ሪፖርት፣ አባሪ ቀ - HCV ማዕቀፍ፣*

*የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ* ሪፖርት እና በአካባቢ ባለሥልጣናት የተረጋገጠ አጠቃላይ ተፅዕኖ ቅነሳ ዕቅድ*

**6.2 የቦታውን ሁኔታ የሚረብሹ ተግባራት ከመጀመራቸው በፊት ድርጅቱ የአስተዳደር ተግባራት በተለዩ የአካባቢ እሴቶች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተፅዕኖዎች መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ* ይለያል እንዲሁም ይገመግማል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

*የደረጃ አዘጋጆች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎች* የሚከናወኑበትን በዝርዝር የተተነተነበት ደረጃ፣ የአካባቢ እሴቶችን የሚመለከቱ የአመራር ተግባራት ስፋት፣ ጥንካሬና አደጋ* ላይ በመመርኮዝ ይገልጻሉ።*

6.2.1 የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ*በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩት የአሁኑና ወደፊት ሊክሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ከደን እስከ መሬት ገፅታ ደረጃ ያለውን ይለያል።

NTFP 6.2.1.1 የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የአስተዳደር እንቅስቃሴዎች የአሁኑና የወደፊት በአካባቢያዊ እሴቶች እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከደን እስከ መሬት ገፅታ ደረጃ ያለውን ይለያል።

NTFP 6.2.1.2 የተጠናቀቁ የ NTFP አያያዝና አጠቃቀም እና የመሰብሰብ ተግባራት ሥነ ምህዳራዊ ተፅእኖ ግምገማ የሚከተሉትን ያጠቃልላል:- ደኑ በሚገኝበት ቦታዎች በብዝሃ ህይወት ላይ ሊኖረው የሚችለው ተፅዕኖ፣ በተለይም ብርቅዬ ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች * እና ቢጋራ የሚኖሩ ዝርያዎች ወይም የጋራ-ሕይወት ግንኙነት/symbiotic relationship/ ያላቸው ወይም ካለበለዚያም ጥገኛ የሆኑበት፣ ወይም ተመሳሳይ ዝርያዎች በቅርበት የሚያድጉበት፤

SLIMF 6.2.1 የቦታውን ሁኔታ የሚረብሹ ተግባራት ከመተግበራቸው በፊት የታቀዱ የአስተዳደር ተግባራት ሊያስከትሉ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅእኖዎች ለመለየት ግምገማ ይካሄዳል።

6.2. 2 የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው የአካባቢ አስተዳደር ተግባራት የቦታውን ሁኔታ የሚረብሹ ሥራዎች ከመጀመራቸው በፊት የሚከሰቱትን ተፅዕኖዎች ይለያል እንዲሁም ይገመግማል።

NTFP 6.2.2.1 አስፈላጊዉ የ NTFPs ምርት አሰባሰብ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት በቦታዉ ላይ የሚከናወኑ ተግባራት በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ይገመገማል።

*አረጋጋጮች: - የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሪፖርት፣ የአካባቢ ጥበቃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የተሟላነት ሪፖርት፣ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ፣ በአካባቢ እሴቶች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ከፍተኛ ተፅዕኖዎች መዝገብ፣* የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣ ቦታ-ተኮር የግምገማ ሂደት።*

6.3 ድርጅቱ* የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል ውጤታማ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ለእነዚህ ተፅዕኖዎች በመጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ* ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ፣ የሚከሰቱትን ለመቀነስ እና ለማስተካከል በመለየት ይተገበራል።

## ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

ከደን* ባዮማስ ለሚመነጨው የኃይል ፍላጎት የሚጠበቀው የወደፊት እድገት የካርቦን ማመቅን እና ማከማቸትን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉትን የደን* አስተዳደር መስፈርቶች መመርመርን ሊያካትት ይችላል። ከ6.3.1 እስከ 6.3.3 የሚደርሱ አመልካቾች ካርቦን ማጠራቀምን እና ማከማቸትን ጨምሮ በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚደርሰውን ተፅእኖ መከላከል ፣ መቀነስ እና ማስተካከል ይጠይቃሉ። የደረጃ አዘጋጆች የብሔራዊ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ከዚህ የአካባቢ እሴት ጋር የተያያዙ ልዩ አመልካቾችን የሚጠይቁ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር አለባቸው።

6.3.1 የአስተዳደር ተግባራት አካባቢያዊ እሴቶችን ለመጠበቅ እና አሉታዊ ውጤቶችን ለመከላከል የታቀዱና የሚተገበሩ ናቸው

NTFP 6.3.1.1 ድርጅቱ በደን አስተዳደሩ በተለዩ ቦታዎች ውስጥ የ NTFPs አያያዝ፣ አሰባሰብ እና ማቀነባበሪያ ሥራዎች አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ ውጤታማ እርምጃዎችን ያዘጋጃል እንዲሁም ይተገብራል ።

NTFP 6.3.1.2 ከ NTFP ዝርያዎች ጋር የተዛመዱ ተህዋሲያን-ፍጥረታት ብዝሃነት በየጊዜዉ መጠበቁን ወይም መጨመሩን ለማሳየት ክትትል ይደረግበታል።

6.3.2 የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ይከላከላሉ*

NTFP 6.3.2.1 የእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ዉጤቶች/NTFPs አስተዳደር ተግባራት በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ይከላከላሉ።

6.3.3 አካባቢያዊ እሴቶች* ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በሚኖርበት ጊዜ ተጨማሪ ጉዳቶችን ለመከላከል እና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ እና/ወይም ለመጠገን እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

NTFP 6.3.3.1 NTFPs ለገበያ ማምረትና መሰብስብ በአካባቢያዊ እሴቶች* ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በሚኖርበት ጊዜ ተጨማሪ ጉዳቶችን ለመከላከል እና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ እና/ወይም ለመጠገን እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

*አረጋጋጮች: - የክትትል ሪፖርቶች፤ ፕሮጀክት ሃሳብ/ፕሮፖዛል፤ የመነሻ የአካባቢ ግምገማ ሪፖርት፤ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሪፖርት፤ የአካባቢ ጥበቃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የተሟላነት ሪፖርት፣ ቦታ-ተኮር የግምገማ ሂደት፣ በአካባቢ እሴቶች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ከፍተኛ ተፅዕኖዎች መዝገብ፣ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*

6.4 ድርጅቱ* ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ ብርቅዬ* እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን* እና መኖሪያ ቦታዎቻቸውን* በጥበቃ ዞኖች*፣ በመከለያ አካባቢዎች*፣ በመገናኛ ቦታዎች* እና/ወይም (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) ለህልውናቸው እና ለኑሮአቸው መቀጠል ሌሎች ቀጥተኛ እርምጃዎችን በመውሰድ ይጠብቃል። እነዚህ እርምጃዎች ከአስተዳደሩ ተግባራት ስፋት፣ ጥንካሬ እና አደጋ እንዲሁም ከብርቅዬ* እና በመጥፋት ላይ ከሚገኙ ዝርያዎች የጥበቃ ሁኔታ እና ከሥነ ምህዳራዊ መስፈርቶች ጋር የሚመጣጠን መሆን አለባቸው። ድርጅቱ* ለደን አስተዳደሩ በተለየ ቦታ* ውስጥ የሚወሰዱትን እርምጃዎች ሲወስን ለደን አስተዳደሩ ከተለየ ቦታ* ውጪ ያሉትን ብርቅዬና በመጥፋት ላይ የሚገኙ ዝርያዎች ጂኦግራፊያዊ ክልል እና ሥነ ምህዳራዊ ፍላጎቶች* ግምት ውስጥ ያስገባል።

## ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:

የደረጃ አዘጋጆች ለአንዳንድ ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ የሚገኙ ዝርያዎች ጥበቃ የሚደረጉ እርምጃዎችን ወደ ብሔራዊ ደረጃዎች የሚወስዱ አመልካቾችን* ያዘጋጃሉ። ዋነኛው ትኩረት የሚሰጠው ለደን አስተዳደሩ በተለየ ቦታ* ውስጥ በሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች* የተጎዱትን የመኖሪያ አካባቢዎች፣ በየዝርያዎች ያለ ብዛት/population እና አካል/individual ጥበቃ* ላይ

ነው። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የደረጃ አዘጋጆቹ ድርጅቱን* በመሬት ገጽታ* ደረጃ ጥበቃ* ላይ ከሚደረጉ ጥረቶች ጋር እንዲያስተባብር የሚመሩትን* በአገር ደረጃ አመልካቾችን* ያዘጋጃሉ። ይህ መመሪያ በ FSC-STD-60-002 አንቀጽ 3.5 (ሐ) መሠረት ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን የሚዘረዝር አስቀድሞ የግዴታ የሆነውን የሀገር አቀፍ ደረጃዎች አባሪ ማሟያ ነው።

የደረጃ አዘጋጆች ለደረጃ አመልካች* 6.4.1 ድርጅቱ* የሚጠቀምበትን ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* ይገልጻሉ።

6.4.1 ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ የሚጠቀሙት ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን እና መኖሪያ ቦታዎቻቸውን ለመለየት ሲሆን ይህም CITES ዝርያዎችን (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) እና ለደን አስተዳደሩ በተለዩ ቦታዎች ውስጥ እና በአቅራቢያቸው የሚገኙ ወይም ሊኖሩ የሚችሉ ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች በብሔራዊ፣ በክልላዊ እና በአካባቢያዊ ዝርዝሮች ላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ ነው።

SLIMF 6.4.1 ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ የሚጠቀሙት ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን እና መኖሪያ ቦታዎቻቸውን ለመለየት ሲሆን ይህም CITES ዝርያዎችን (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) እና ለደን አስተዳደሩ በተለዩ ቦታዎች ውስጥ እና በአቅራቢያቸው የሚገኙ ወይም ሊኖሩ የሚችሉ ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች በብሔራዊ፣ በክልላዊ እና በአካባቢያዊ ዝርዝሮች ላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ ነው።

6.4. 2 በብርቂዬና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች እና የጥበቃ ሁኔታቸው* እና መኖሪያቸው* ላይ የሚፈጠር የአስተዳደር ተግባር ከፍተኛ ተፅዕኖ ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለማስወገድ የአስተዳደር ሥራዎች ይሻሻላሉ።

NTFP 6.4.2.1 በብርቂዬና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች እና የጥበቃ ሁኔታቸው* እና መኖሪያቸው* ላይ የሚፈጠር የNTFPs የአስተዳደር ተግባር ከፍተኛ ተፅዕኖ ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለማስወገድ የአስተዳደር ሥራዎች ይሻሻላሉ።

SLIMF 6.4.2.1 የአስተዳደር ተግባራት የተቀረፁት ወይም የተሻሻሉት ብርቂዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችና የመኖሪያ ቦታዎቻቸው አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖር ነው።

6.4.3 ብርቅዬ* እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን* እና መኖሪያ ቦታዎቻቸውን* በጥበቃ ዞኖች*፣ በመከለያ አካባቢዎች*፣ በመገናኛ ቦታዎች* እና/ወይም (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) ለህልውናቸው እና ለኑሮአቸው መቀጠል ሌሎች ቀጥተኛ እርምጃዎችን በመውሰድ ይጠብቃሉ፤ እንደ ዝርያዎች መልሶ ማቋቋም ፕሮግራሞች ያሉ ናቸው።

SLIMF 6.4.3.1 ብርቅዬ* እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን* እና መኖሪያ ቦታዎቻቸውን* በጥበቃ ዞኖች*፣ በመከለያ አካባቢዎች*፣ በመገናኛ ቦታዎች* እና/ወይም (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) ለህልውናቸው እና ለኑሮአቸው መቀጠል ሌሎች ቀጥተኛ እርምጃዎችን በመውሰድ ይጠብቃሉ፤ እንደ ዝርያዎች መልሶ ማቋቋም ፕሮግራሞች ያሉ ናቸው።

6.4.4 ብርቅዬ ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን* ማደን፣ ማጥመድ፣ መያዝና መሰብሰብ የተከለከለ ነው።

NTFP 6.4.4.1 NTFPs በአካባቢ እና/ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለአደጋ የተጋለጡ ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች ዝርዝር (ለምሳሌ፣ CITES እዝል 1፣ የ IUCN ዝርዝር፣ በከፍተኛ ሁኔታ አደጋ ላይ ያሉ (CR) እና አደጋ ላይ ያሉ (EN) ዝርያዎች በ IUCN ቀይ ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ) እንዲሁም ብርቂዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች መኖሪያዎቻቸው ቦታዎች ላይ የሚገኙ NTFPs አይሰበሰቡም።

SLIMF 6.4.4.1 ብርቅዬ ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን* ማደን፣ ማጥመድ፣ መያዝና መሰብሰብ ለመከላከል ሥርዓት ተዘርግቷል።

አረጋጋጮች፦አባሪ ቀ HCV ማዕቀፍ፤ ብርቂዬና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችና መኖሪያ ቦታዎቻቸው ዝርዝር*፤ ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ* ውስጥ የሚገኙ ዝርያዎች፤ የመስክ ዳሰሳ ሪፖርቶች፤ የተከለሉ* ቦታዎች፣ በግልጽ የተለዩና ካርታ ላይ የተቀመጡ የስደት መተላለፊያዎች፤ ብርቅዬ ወይም በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን* ማደን፣ ማጥመድ፣ መያዝና መሰብሰብ የሚከለክሉ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች*

**6.5 *ድርጅቱ የአካባቢውን ሥነ ምህዳሮች የሚወክሉ የናሙና * ቦታዎች ለይቶ ይንከባከባል እና/ወይም ወደ ተፈጥሯዊ ሁኔታ እንዲመለሱ* ያደርጋል። ወኪል ናሙና አካባቢዎች በማይኖሩበት ወይም በቂ በማይሆኑበት ጊዜ ድርጅቱ* የተወሰነ ተመጣጣኝ ቦታ ለደን አስተዳደር ከተለየ ቦታ ውስጥ* ወደ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ይመልሳል*። የቦታዎቹ ስፋትና በሰዉ ሰራሽ ደኖች ውስጥም ጭምር ለመከላከያ ወይም ለመልሶ ማቋቋም የተወሰዱት እርምጃዎች በመሬት ገጽታ ደረጃ የሥነ ምህዳሮች የጥበቃ ሁኔታ እና እሴት እንዲሁም የአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

የደረጃ አዘጋጆች የናሙና አካባቢዎች*ለመለየት የሚያስችሉ ዘዴዎችን መለየት አለባቸው።

ወኪል የሆኑ የናሙና አካባቢዎች* የሚከተሉትን ጨምሮ በርካታ ተግባራትን ያከናውናሉ።

- በነባር ሥርዓተ ምህዳሮች ውስጥ የሚገኙትን የአካባቢያዊ እሴቶች የሚወክል* እናም ለደን አስተዳደር ከተለየ ቦታ ውስጥ* ለአካባቢያዊ እሴቶች* እና ሥርዓተ ምህዳር ግሏጋሎቶች ማጣቀሻ ሆኖ የሚያገለግል። ለሁሉም ሥርዓተ ምህዳሮች እንደ ማጣቀሻ የሚሆኑትን ወካይ ናሙና ቦታዎች* ለመጠቀም ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ሊገኝ የሚችል ለ 6.1.1 ዓላማዎች ሲባል ለደን አስተዳደር ከተለየ ቦታ* ውጭ ያሉትን ወኪል ናሙናዎችን* መለየት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ በዋናነት ሰው ሠራሽ ደኖች ባሏቸው ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ* ውስጥ ላይ ሊከሰት ይችላል።

- የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ* ዳግም ብቅለትን ጨምሮ የደን አያያዝና አጠቃቀምን ማሳወቅ።

- ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ የጥበቃ ቦታዎች መረብ* /Conservation Area Network ክፍል መፍጠር። የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅና ለማቆየት* ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ* ወኪል የሆኑ የናሙና አካባቢዎችን* መለየትና መልሶ ማቋቋም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የተከለሉ ቦታዎች*፣ የጥበቃ ዞኖች*፣ የወካይ ናሙና ቦታዎች* እና የከፍተኛ ጥበቃ እሴት ያላቸው ቦታዎች*/High Conservation Value Areas ፣ የጥበቃ ቦታዎች መረብ ለመፍጠር ተመሳሳይ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ በቦታ ደረጃ ሊደጋገፉ ይችላሉ። እባክዎን ወደ አባሪ **ሐ** ይመልከቱ።

የጥበቃ ቦታ መረቦች* እንዴት እንደሚገለጹ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ወደ አባሪ **ሐ** ይመልከቱ።

የጥበቃ ቦታዎች መረብ የሰው ልጅ በቀጥታ ጣልቃ ሳይገባ ተፈጥሯዊ ሂደቶች እንዲከናወኑ የሚያስችል በቂ ስፋት ሊኖረው ይገባል። ያልተነኩ የደን መልከዓ ምድሮች* በሚገኙባቸው አካባቢዎች ላይ የጥበቃ ቦታዎች መረብ እንዲኖር አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው። ከ 2011 ጀምሮ የ FSC ፖሊሲ እና ደረጃዎች ኮሚቴ በ FSC ዳይሬክተሮች ቦርድ ስም በሀገር አቀፍ ደረጃ አሰጣጥ ማረጋገጫ ሂደት በኩል ለሁሉም የ FSC ብሔራዊ ደረጃዎች ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ቢያንስ የ 10% ገደብ* ያለማቋረጥ ተግባራዊ እያደረገ ነው። ይህ ገደብ በ FSC Forest Stewardship ደረጃዎች: መዋቅር, ይዘት እና የቀረቡ አመላካቾች* FSC-GUI-60-004 V1-0 ውስጥ በ መስፈርት* 6.2 ላይ ተጽፏል። ይህ ሰነድ በ 2011 ከፀደቀበት ጊዜ አንስቶ ለደረጃ ዝግጅት ቡድኖች ቁልፍ ማጣቀሻ ሆኖ ቆይቷል ።

6.5.1 ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ በተፈጥሮ ሁኔታዎች* ውስጥ ያሉ ወይም ሊኖሩ የሚችሉ የአካባቢያዊ ነባር ሥረዓተ ምህዳሮችን* ለመለየት ይጠቅማል።

SLIMF 6.5.1.1 ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ በተፈጥሮ ሁኔታዎች* ውስጥ ያሉ ወይም ሊኖሩ የሚችሉ የአካባቢያዊ ነባር ሥረዓተ ምህዳሮችን* ለመለየት ይጠቅማል።

6.5.2 የነባር ሥረዓተ ምህዳሮች* ወካይ ናሙና ቦታዎች በሚገኙበት ጊዜ የተጠበቁ ናቸው።

6.5.3 ወኪል ናሙና ቦታዎች* በማይኖሩበት ወይም ነባር የናሙና ሥረዓተ ምህዳሮችን* በበቂ ሁኔታ በማይወክሉበት ወይም በሌላ መንገድ በቂ ካልሆኑ፣ ለደን አስተዳደር ከተለዩ ቦታዎች ውስጥ የተወሰነ ክፍል* ወደ በለጠ ተፈጥሯዊ ሁኔታ* ይመለሳል።

6.5.4 ወኪል ናሙና ቦታዎች* እና/ወይም የመልሶ ማቋቋም ቦታዎች* መጠን በመሬት ገጽታ ደረጃ ላይ ካለው የሥረዓተ ምህዳሮች ጥበቃ ሁኔታ እና እሴት፣ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች መጠን እና የደን አያያዝና አጠቃቀም ጥንካሬ ጋር ተመጣጣኝ ነው።

SLIMF 6.5.4.1 ወኪል ናሙና ቦታዎች* እና/ወይም የመልሶ ማቋቋም ቦታዎች* መጠን በመሬት ገጽታ ደረጃ ላይ ካለው የሥረዓተ ምህዳሮች ጥበቃ ሁኔታ እና እሴት፣ ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች መጠን እና የደን አያያዝና አጠቃቀም ጥንካሬ ጋር ተመጣጣኝ ነው።

6.5.5 ወኪል ናሙና ቦታዎች ከሌሎች የጥበቃ ቦታዎች መረብ ክፍሎች ጋር ተዳምሮ* ቢያንስ 10% የሚሆነውን ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ ይይዛሉ*

አረጋጋጮች: - በግልጽ የተከለሉና በካርታ የተቀመጡ ነባር ሥረዓተ ምህዳሮች*፤ አባሪ **ቀ** HCV ማዕቀፍ፤ በቦታዉ ያሉ የጥበቃ እርምጃዎች፤ በግልጽ የተከለሉና በካርታ የተቀመጡ አዲስ የተመለሱ ነባር ሥረዓተ ምህዳሮች*፤ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*

6.6 ድርጅቱ* በተፈጥሮ የሚገኙ ሀገር በቀል ዝርያዎችን* እና ዘረመል ቀጣይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይጠብቃል እንዲሁም የሥነ-ሕይወት ብዝሃነት* ማጣት እንዳይኖር በተለይም ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ዉስጥ የመኖሪያ ቦታዎቻቸውን በሚገባ በማስተዳደር* ይከላከላል። ድርጅቱ* አደን፣ ዓሣ ማስገር፣ ማጥመድ እና መሰብሰብን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ውጤታማ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያሳያል።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:**

የደረጃ አዘጋጆች በሀገር ውስጥ ደረጃዎች ለየመኖሪያ ቦታዎች የሚያስፈልጉ ዋና ባህሪያት* የአስተዳደር ገደቦችን ይገልጻሉ። ሊታሰብባቸው የሚገቡ የአካባቢ ባህሪያት* ገደቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- የተፈጥሮን ደንን ብዝሃነት፣ ስብጥርና መዋቅር የሚጠብቁና የሚመልሱ የእንጨት ማምረት፣ መሰብሰብና የሲልቪካልቸር /Silviculture/ ዘዴዎች፣
- በጠቅላላው ለምርት ከሚሰበሰቡብት ቦታዎች በሕይወት ያሉ ዛፎችን እና የደረቁ እንጨቶችን እንደ ነጠላ ዛፍ ወይም በፓች ወይም በቡድን፣ በተፈጥሮ ኅልቶ የሚታዩ ዝርያዎችን የሚወክሉ ዛፎችን ጨምሮ ዛፎችን ለማቆየት የሚረዱ ገደቦች እና መመሪያዎች፤
- የእንጨት ቅርቶች እና ሌሎች የተፈጥሮ ደን ዛፎች የሚወክሉ ዕፅዋትን ለማቆየት እና እንደገና እንዲበቅሉ የሚረዱ ገደቦች እና መመሪያዎች፤

- የደን ዛፎች ዕድሜ ወሰን ለማረጋገጥ ሁሉንም የተፈጥሮ መኖሪያ ቦታዎች፣ የተቆራረጡ የደን ቦታዎችን ለመከላከል እና ተደራራቢ የውሃ ተፋሰስ ተፅእኖዎችን ለመጠበቅ የመሬት ክፍተት መጠንን እና በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ዛፎች የሚቆረጥበት ዙር ርዝመቶችን ለመቆጣጠር የሚረዱ ገደቦች እና መመሪያዎች፣ እና

- የደን ምረት መሰብሰብ አወቃቀር ቅንብር ማረጋገጥ*

6.6.1 ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች* የአስተዳደር ተግባራት ሲከናወኑ ነባር ሥርዓተ ምህዳሮች* ውስጥ የሚገኙትን ማህበረ-እጽዋት እና ለመኖሪያ ቦታዎች የሚያስፈልጉ ዋና ቦታዎች ይጠብቃሉ።

NTFP 6.6.1.1 የ NTFPs ምርት አሰባሰብ እና አስተዳደር ለNTFPs እና ሌሎች ተጓዳኝ ዝርያዎችን ሥርዓተ ምህዳራዊ ሚና እና መስፈርቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው ፤ ለምሳሌ ለአእዋፍ እና አጥቢ እንስሳት ምግብ ፤ በእንስሳት አማካኝነት ዘር ማሰራጨት፣ የተለዩ ሥነ ምህዳራዊ ቆርኝነቶችን መጠበቅ ፤ ወዘተ

6.6.2 ቀድሞ የነበረዉ አስተዳደር ማህበረ-እጽዋትን ወይም ለመኖሪያ ቦታዎች የሚያስፈልጉ ዋና ቦታዎችን ያጠፋ እንደሆነ እነዚህን የመኖሪያ ቦታዎች መልሶ ለማቋቋም የሚረዱ የአስተዳደር ተግባራት ይከናወናሉ።

6.6.3 አስተዳደሩ በተፈጥሮ የሚገኙ ዝርያዎችን እና ዘረመል ብዝሃነታቸውን ለመደገፍ ከተፈጥሮ ሥርዓተ ምህዳሮች ጋር የተያያዙ ለመኖሪያ ቦታዎች የሚያስፈልጉ ዋና ቦታዎችን የአካባቢ ባህሪያትን* ይጠብቃል፣ ያሻሽላል ወይም ይመልሳል።

6.6.4 በተፈጥሮ የሚገኙትን የሀገር በቀል ዝርያዎች*፣ በዝርያቸው ውስጥ ያለው ብዝሃነት እና ተፈጥሯዊ ስርጭታቸው እንዲጠበቁ ለማድረግ የተገደበ የአደን፣ የዓሣ ማስገር፣ ማጥመድ እና የመሰብሰብ ተግባራትን ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር ውጤታማ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

NTFP 6.6.4.1 በተፈጥሮ የሚገኙትን የሀገር በቀል ዝርያዎች*፣ በዝርያቸው ውስጥ ያለው ብዝሃነት እና ተፈጥሯዊ ስርጭታቸው መጠበቁን ለማረጋገጥ የNTFPs የማምረት ወይም የመሰብሰብ ተግባራትን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ውጤታማ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

6.6. 4ሀ የዱር እንስሳትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዘዴዎች* ተተግብረዋል፤ በአደን እና በእንስሳት ወይም የአካል ክፍሎቻቸው (ቀንዶች) ንግድ በብሔራዊ እና/ወይም ዓለም አቀፍ የጥበቃ ደንቦች ላይ የሚታወቁና የሚከበሩ መሆን አለባቸው፤

6.6.4ለ በድርጅቱ መገልገያዎችና ተሽከርካሪዎች ውስጥ የዱር እንስሳት ሥጋ እና የተኩስ መሳሪያዎችን ማጓጓዝ እና ንግድ የሚከለክል እና የሚቀጣ የውስጥ ደንብ*፤

6.6.4ሐ የአደን ፖሊሲዎች መከበሩን ለማረጋገጥ መደበኛ እና ወቅታዊ ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፤

6.6.4መ ሰራተኞች* የዱር እንስሳት ሥጋን ወይም የዱር ዓሣዎችን ማደንን ወይም መሰብሰብን እንዳያባብሱ ለማድረግ ውጤታማ የመቀነስ እርምጃዎች ተቀምጠዋል።

*አረጋጋጮች; - የእሳት አደጋ መከላከያ ዕቅድ፤ ወራሪ አረም መቆጣጠሪያ ዕቅድ፣ የግጦሽ ቁጥጥር ዕቅድ፤ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፤ የመኖሪያ ቦታዎችን መልሶ ማቋቋም* ዕቅዶች፤ ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ የሚከናወኑ ሕገ ወጥ ተግባራትን የሚገልጹ ሪፖርቶች*፤ ነባር የሥርዓተ ምህዳሮችን ስርጭት በግልጽ የሚያሳይ ካርታ**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:***

አደን የዝርያ ብዝሃነትን አደጋ ላይ በሚጥልባቸው ክልሎች የሚከተሉት አመልካቾች* በብሔራዊ ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ውስጥ ይካተታሉ።

6,6X የዱር እንስሳትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዘዴዎች* ተተግብረዋል፤ በአደን እና በእንስሳት ወይም የአካል ክፍሎቻቸው (ቀንዶች) ንግድ በብሔራዊ እና/ወይም ዓለም አቀፍ የጥበቃ ደንቦች ላይ የሚታወቁና የሚከበሩ መሆን አለባቸው፤

6,6X በድርጅቱ መገልገያዎችና ተሽከርካሪዎች ውስጥ የዱር እንስሳት ሥጋ እና የተኩስ መሳሪያዎችን ማጓጓዝ እና ንግድ የሚከለክል እና የሚቀጣ የውስጥ ደንብ*፤

6,6X የአደን ፖሊሲዎች መከበሩን ለማረጋገጥ መደበኛ እና ወቅታዊ ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፤

6,6X ሰራተኞች* የዱር እንስሳት ሥጋን ወይም የዱር ዓሣዎችን ማደንን ወይም መሰብሰብን እንዳያባብሱ ለማድረግ ውጤታማ የመቀነስ እርምጃዎች ተቀምጠዋል።

**6.7 ድርጅቱ* የተፈጥሮ የውሃ ፍሰት፣ የውሃ አካላትን፣ የወንዞች ዳርቻ ዞኖችን* እና ግንኙነታቸውን* ይጠብቃል ወይም ወደነበረበት ይመልሳል። ድርጅቱ በውሃ ጥራትና ብዛት ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ያስወግዳል እንዲሁም የሚከሰቱትን ተፅዕኖዎች ይቀንሳል እንዲሁም ያክማል።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:**

የደረጃ አዘጋጆች የሚከተሉትን የሚያካትቱ የመከላከያ እርምጃዎችን መወሰን አለባቸው፤ እነዚህ እርምጃዎች በቂ ጥበቃ የሚያደርጉ ከሆነ አሁን ያሉ ደንቦችን እና/ወይም ምርጥ ልምዶችን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የመከላከያ ዞኖች/ቀጠናዎች እና ሌሎች የተፈጥሮ የውሃ ፍሰትን* እና የውሃ አካላትን*፣ የእነሱን ተያያዥነት*፣ በጅረት ውስጥ ያሉትን መኖሪያ ቦታዎች* እንዲሁም ዓሦችን፣ አከርካሪ አልባ እንስሳትን እና ውሃ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ዝሪያዎች ለመጠበቅ የሚረዱ እርምጃዎች፣

- በወንዞችና በውሃ አካላት ዳርቻ አካባቢዎች የሚገኙትን ነባር ዕፅዋት ለመጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎች፤ የመሬት ላይ እና የውሃ ውስጥ ዝርያዎችን መመገብ፣ ማባዛት ወይም መኖሪያ ቦታቸውን መሸፈን * ጨምሮ እንዲሁም የውሃ አካባቢዎች የሚያስፈልጋቸውን የእንጨትና የቅጠል ቆሻሻ ግባት ማስገባት፣

- የውሃውን ብዛትና ጥራት አሉታዊ ለውጦችን ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎች፣ ይህም ከተፈጥሮ ገደቦች በላይ ከሚሆኑ የሙቀት ለውጦች ለመከላከል የሚያስችል በቂ የጅረት ጥላ የሚያጠሉ ዛፎችን በመጠበቅ፣

- ተፈጠሮአዊ የዉሃዎች ፍሰት ሥርዓት እና የጅረት ፍሰቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ እርምጃዎች፣

- የመንገድ አካባቢ፣ ግንባታ፣ ጥገና እና አጠቃቀም የሚያስከትሉ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎች፣

- በውሃ አካላት ውስጥ የሚከሰተውን የደለል ክምችት እና በምርት መሰብሰብ ሂደት ውስጥ፣ በመንገድ እና በሌሎች ተግባራት ምክንያት የሚከሰተውን የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል የሚደረጉ እርምጃዎች፣ እና

- ከኬሚካሎች ወይም ማዳበሪያዎች የሚመጡ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎች*

6.7.1 የተፈጥሮ የውሃ ፍሰት፣ የውሃ አካላትን፣ የወንዞች ዳርቻ ዞኖችን* እና ግንኙነታቸውን* በውሃ ጥራትና ብዛት ለመጠበቅ የጥበቃ* እርምጃዎች ይተገበራሉ።

6.7.2 የተተገበሩ የጥበቃ* እርምጃዎች የውሃ ፍሰቶችን፣ የውሃ አካላትን፣ የወንዞች ዳርቻ ዞኖችን* እና ግንኙነታቸውን*፣ የውሃውን መጠን ወይም የውሃውን ጥራት ከደን አስተዳደር* ተፅዕኖዎች የማይጠብቁ ከሆነ ወደነበረበት የመመለስ ተግባራት ይከናወናሉ።

6.7.3 የተፈጥሮ የውሃ ፍሰት፣ የውሃ አካላት*፣ የወንዞች ዳርቻ ዞኖች* እና ግንኙነታቸውን፣ የውሃው መጠን ወይም የውሃው ጥራት* ላይ ቀደም ሲል በድርጅቱ ተገባራት መሬትና ዉሃዉ ላይ ጉዳት ከደረሰ ወደነበረበት የመመለስ ተግባራት ይከናወናሉ።

6.7.4 የውሃ ፍሰቶች*፣ የውሃ አካላት*፣ የውሃ መጠንና የውሃ ጥራት በቀደሙት አስተዳዳሪዎችና በሶስተኛ ወገኖች ትግባራት ምክንያት ያለማቋረጥ እየቀነሰ ከመጣ ይህንን ጉዳት የሚከላከሉ ወይም የሚቀንሱ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

አረጋጋጮች: - የደን አያያዝና አጠባበቅ ዕቅድ*፤ የውሃ ፍሰቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሂደቶች*፤ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ፤ የአፈር መከላት መቆጣጠሪያ ዕቅድ፤ ወደነበረበት የመመለስ ተግባራት ዕቅዶች፤ የውሃ ጥራትና መጠን የክትትል ሪፖርቶች፤ የውሃ ፍሰቶች በግልጽ ከመከላከያ ዞኖቻቸው ጋር ካርታ ተቀርጾላቸዋል፤ ወሰን በግልጽ ተቀምጦላቸዋል

**6.8 በተለያዩ ሕብር ዉስጥ ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ዝርያዎች፣ መጠኖች፣ እድሜዎች፣ የሚገኙበት ቦታ ደረጃዎች* እና የመልሶ ማቋቋም ዑደቶች ለመጠበቅ እና/ወይም ወደነበረበት ለመመለስ እንዲሁም የአካባቢ እና ኢኮኖሚያዊ የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ ድርጅቱ በአስተዳደር ክፍሉ ውስጥ ያለውን የመሬት ገጽታ ያስተዳድራል።**

6.8.1 በተለያዩ ሕብር ዉስጥ ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ዝርያዎች፣ መጠኖች፣ እድሜዎች፣ የሚገኙበት ቦታ ደረጃዎች* እና የመልሶ ማቋቋም ዑደቶች ለመሬት ገጽታ ተስማሚ ሆነው ይቆያሉ።

6.8.2 የተለያዩ ዝርያዎች ሕብር፣ መጠኖች፣ እድሜዎች፣ የሚገኙበት ቦታ ደረጃዎች* እና የመልሶ ማቋቋም ዑደቶች ለመሬት ገጽታ ተስማሚ ሆኖ ካልተጠበቀበት ቦታ ተመልሶ ይመጣል።

አረጋጋጮች: - የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፤ የምርት መዝገብ፤ ወደነበረበት የመመለስ ተግባራት ዕቅድ

**6. 9 ድርጅቱ* የተፈጥሮ ደን* ወደ ሰው ሠራሽ ደን* አይቀይርም፣ እንዲሁም የተፈጥሮ ደን* ወይም ሰው ሠራሽ ደን* በቀጥታ ከተፈጥሯዊ ደን* ወደ ደን ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም በተቀየሩ ቦታዎች አይቀይርም፥ ሆኖም ግን የሚቀየረው፡-**

**1) በጣም ውስን የሆነ ክፍል ለደን አስተዳደር ከተለዩ ቦታዎች ላይ የሚነካ ሲሆን* እና**

**2) ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪና አስተማማኝ የረጅም ጊዜ የጥበቃ* ጥቅሞችን ሲያስገኝ፣**

**3) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን አይጎዳም ወይም አደጋ ላይ አይጥልም፣ እንዲሁም እነዚህን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ቦታዎችን ወይም ሀብቶችን አይጎዳም።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:**

በቀጥታ ከተፈጥሮ ደን የተለወጠ ማለት የተተከለው ቦታ ወደ ሰው ሠራሽ ደን ቦታ ከመቀየሩ በፊት የተፈጥሮ ደን ከሆነ ከዚያም ወደ ደን ያልሆኑ ጥቅምሞች ሊለወጥ አይችልም የሚለዉን ለማስተላለፍ የታሰበ ነው። ይሁን እንጂ የተከላ ቦታው ወደ ሰው ሠራሽ ደን ከመቀየሩ በፊት የደን ያልሆነ ከሆነ ወደ ደን ያልሆነ አጠቃቀም ሊለወጥ ይችላል። ለውጦቹ ከ መስፈርት* 1.8 ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው እና ለ FSC መርሆዎች* እና መስፈርቶች* እና ለተዛማጅ የ FSC ፖሊሲዎች እና ደረጃዎች የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነትን ማሳየት አለባቸው።

6.9.1 የተፈጥሮ ደን* ወደ ሰው ሠራሽ ደን* አይለወጥም፣ የተፈጥሮ ደን* ወደ ደን ያልሆነ መሬት አጠቃቀም አይለወጥም፣ አንዲሁም ሰው ሠራሽ ደን ከተፈጥሮ ደን* ወደ ደን ያልሆነ መሬት አጠቃቀም በቀጥታ በተለወጡ ቦታዎች ላይ * አይለወጥም፤ የሚለወጡበት ሁኔታም፡-

1) በጣም ውስን የሆነ ክፍል ለደን አስተዳደር ከተለዩ ቦታዎች ላይ የሚነካ ሲሆን* እና

2) ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪና አስተማማኝ የረጅም ጊዜ የጥበቃ* ጥቅሞችን ሲያስገኝ፣

3) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን አይጎዳም ወይም አደጋ ላይ አይጥልም፣ እንዲሁም እነዚህን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ቦታዎችን ወይም ሀብቶችን አይጎዳም።

6. 10 እ.ኤ.አ ከህዳር 1994 በኋላ ከተፈጥሮ ደን በተለወጡ አካባቢዎች የተቋቋሙ ሰው ሠራሽ ደኖች የያዙ የደን አስተዳደር ቦታዎች ለዕውቅና ማረጋገጫ ብቁ አይደሉም፣ ከሚከተሉት በስተቀር፣

ድርጅቱ* ለለውጡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሃላፊነት እንደሌለው ግልጽና በቂ ማስረጃ ሲያቀርብ፣ ወይም ይህ ለውጥ ለደን አስተዳደር በተለየው ቦታ በጣም ውስን የሆነ ክፍል* ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ሲሆን እና ለደን አስተዳደር በተለየው ቦታ ውስጥ ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪና አስተማማኝ የረጅም ጊዜ የጥበቃ* ጥቅሞችን እያመጣ ከሆነ።

6.10.1 እ.ኤ.አ ከኅዳር 1994 ወዲህ ባሉት ጊዜያት ስለተደረጉት ለውጦች ትክክለኛ መረጃዎች የተዘጋጁት ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* በመጠቀም ነው።

6.10.2 እ.ኤ.አ ከኅዳር 1994 ጀምሮ ከተፈጥሮ ደን* ወደ ሰው ሠራሽ ደን የተለወጡ ቦታዎች ከእውቅና ወረቀት ዉጪ ይሆናሉ* ከሚከተሉት በስተቀር፦

1) ድርጅቱ* ለለውጡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠያቂ አለመሆኑን በግልፅና በቂ ማስረጃ ሲያቀርብ፣ ወይም

2) ማሻሻያው ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች ውስጥ ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና የረጅም ጊዜ የጥበቃ* ጥቅሞችን እያመጣ ሲሆን፤ እንዲሁም

3) እ.ኤ.አ ከኅዳር 1994 ጀምሮ ከተፈጥሮ ደን* ወደ ሰው ሠራሽ ደን የተለወጡ አጠቃላይ ቦታዎች ለደን አስተዳደር ከተለዩ ቦታዎች አጠቃላይ መሬት* ከ5% በታች ሲሆን።

***መርህ* 7: የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ስለማውጣት***

**ድርጅቱ* ከፖሊሲዎቹና ዓላማዎቹ* ጋር የሚስማማና ከአስተዳደሩ ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬና አደጋዎች* ጋር የሚመጣጠን የደን አያያዝና አጠቃቀም* ዕቅድ ይኖረዋል። የደን አያያዝና አጠቃቀም* ዕቅዱ* የሚተገበረውና ወቅታዊ የሚሆነው ከሁኔታዎች ጋር የሚስማማ አስተዳደርን ለማስፋፋት በሚደረገው ክትትል መረጃ ላይ ተመስርቶ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የተዘጋጀው የዕቅድ እና የአሰራር ሰነድ ሰራተኞቹን ለመምራት፣ የተጎዱትን ባለድርሻ አካላት* እና ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት* ለማሳወቅ እና የአመራር ውሳኔዎችን ለማመሳከር በቂ መሆን አለበት።**

**7.1 ድርጅቱ* ከአስተዳደር ተግባሩ መጠን፣ ጥንካሬና አደጋ* ጋር የሚመሳሰል፣ ከአካባቢያዊ ሁኔታ አንፃር ጤናማ፣ ከማህበራዊና ከኢኮኖሚ አንፃር ጠቃሚ የሆኑ የአስተዳደር ፖሊሲዎችን (ራዕዮችንና እሴቶችን) እና ዓላማዎችን* ያወጣል። የእነዚህ ፖሊሲዎች እና ዓላማዎች* ማጠቃለያዎች በአስተዳደር ዕቅዱ* ውስጥ ይካተታሉ እንዲሁም ይፋ ይሆናሉ።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

በዚህ ደረጃ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው የአስተዳደር ዓላማዎች* የሚለው ቃል የዚህን ደረጃ አስፈላጊ ነገሮች ለማሳካት የተቋቋሙ የተወሰኑ የአስተዳደር ግቦችን፣ ልምዶችን፣ ውጤቶችን እና አቀራረቦችን ያመለክታል። የደረጃ አዘጋጆች ድርጅቱ በዚህ ደረጃ ከሚጠየቁት የተወሰኑ የአስተዳደር ዓላማዎች፣ ልምዶች፣ ውጤቶችና አቀራረቦች ጋር የሚስማሙ የተወሰኑ

የአስተዳደር ዓላማዎችን* ማቋቋሙን ለማረጋገጥ አመላካቾችን* ያዘጋጃሉ። ድርጅቱ* በተጨማሪም የደን አያያዝን በተመለከተ አጠቃላይና ተፈላጊ የሆኑ ዓላማዎችን* ሊመድብ ይችላል፤ እነዚህ ግቦች የዚህን ደረጃ የማይቃረኑ ናቸው።

7.1.1 የዚህን ደረጃ መስፈርቶች ለማሟላት የሚረዱ ፖሊሲዎች (ራዕይ እና እሴቶች) ተወስነዋል።

NTFP 7.1.1.1 የዚህን ደረጃ መስፈርቶች ለማሟላት የሚረዱ ፖሊሲዎች (ከ NTFPs ጋር የተዛመዱ ራዕዮች እና እሴቶች) ተወስነዋል።

SLIMF 7.1.1.2 የዚህን ደረጃ መስፈርቶች ለማሟላት የሚረዱ ፖሊሲዎች (ራዕይ እና እሴቶች) ተወስነዋል።

7.1.2 የዚህን መስፈርት ደረጃ የሚያሟሉ የተለዩ የአሠራር አስተዳደር ዓላማዎች ተወስነዋል።

NTFP 7.1.2.1 የዚህን ደረጃ መስፈርቶች የሚያሟሉ ለ NTFPs የተወሰኑ የአሠራር አስተዳደር ግቦች* ተወስነዋል።

SLIMF 7.1.2.2 የዚህን ደረጃ መስፈርቶች የሚያሟሉ የተለዩ የአሠራር አስተዳደር ዓላማዎች ተወስነዋል።

7.1.3 የተገለጹት ፖሊሲዎች እና የአስተዳደር ዓላማዎች* ማጠቃለያዎች በደን አያያዝና አጠቃቀም* ዕቅዱ* ውስጥ ተካትተው ይፋ ይሆናሉ።

NTFP 7.1.3.1 ለNTFPs የተገለጹት ፖሊሲዎች እና የአስተዳደር ዓላማዎች* ማጠቃለያዎች በደን አያያዝና አጠቃቀም* ዕቅዱ* ውስጥ ተካትተው ይፋ ይሆናሉ።

*አረጋጋጮች: - የደን አያያዝና አጠቃቀም* ዕቅድ፤ ምርት የመሰብሰብ አሰራሮች፤ የአሠራር ዕቅዶች፤ የምርት አሰባሰብ እቅድ*

7.2 ድርጅቱ* ለደን አስተዳድር በተለየ ቦታ ውስጥ ለደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ የሚሆን የአመራር ዕቅድ* ሊኖረውና ሊተገበር ይገባል፤ ይህ ዕቅድ* በመስፈረት* 7.1 መሠረት ከተቀመጡት ፖሊሲዎችና የአመራር ዓላማዎች* ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ ነው። የአስተዳደር ዕቅዱ* ለደን አስተዳድር በተለየ ቦታ ውስጥ ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች ይገልጻል* እንዲሁም እቅዱ የ FSC የምስክር ወረቀት የሚያስፈልጉ ነገሮች እንዴት እንደሚያሟላ ያብራራል። የአስተዳደር ዕቅዱ* ከደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ * እና ከማህበራዊ አስተዳደር ዕቅድ* ከታቀዱት ተግባራት መጠን*፣ ጥንካሬ* እና አደጋ* ጋር የሚመጣጠን ይሸፍናል።

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

የደረጃ አዘጋጆች የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ* የሚፈጀው ጊዜ ከመስፈርት* 1.8 ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ አመላካቾችን* ያዘጋጃሉ እንዲሁም ለ FSC መርሆዎች* እና መስፈርቶችን* እና ለተዛመዱ የ FSC ፖሊሲዎች እና ደረጃዎች የረጅም ጊዜ* ቁርጠኝነትን ያሳያሉ።

7.2.1 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ* የአስተዳደር ዓላማዎችን ለማሳካት የሚረዱ የአስተዳደር እርምጃዎችን፣ አሰራሮችን፣ ስትራቴጂዎችን እና እርምጃዎችን ያካትታል።

NTFP 7.2.1.1 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ* የአስተዳደር ዓላማዎችን ለማሳካት የ NTFPs እርምጃዎችን፣ አሰራሮችን፣ ስትራቴጂዎችን እና እርምጃዎችን ያካትታል።

SLIMF 7.2.1.1 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ* የአስተዳደር ዓላማዎችን ለማሳካት የሚረዱ የአስተዳደር እርምጃዎችን፣ አሰራሮችን፣ ስትራቴጂዎችን እና እርምጃዎችን ያካትታል።

7.2.2 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ* በአባሪ መ ላይ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ነገሮች ተደራሽ ያደርጋል እና ይተገበራል።

NTFP 7.2.2.1 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ* በአባሪ መ ላይ የተዘረዘሩትን የ NTFPs መሰረታዊ ነገሮች ተደራሽ ያደርጋል እና ይተገበራል።

SLIMF 7.2.2.1 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ* በአባሪ መ ላይ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ነገሮች ተደራሽ ያደርጋል እና ይተገበራል።

*አረጋጋጮች: - የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፣ አሰራር ሂደቶች*

**7. 3 የደን አያያዝና አጠባበቅ ዕቅዱ* በእያንዳንዱ የተቀመጠ የአስተዳደር ዓላማዎች ላይ የተደረገውን እድገት ለመገምገም የሚያስችሉ ሊረጋገጡ የሚችሉ ዒላማዎች* ያካትታል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

*መዘጋጀት ያለባቸው ሊረጋገጡ የሚችሉ ዒላማዎች* ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-*

- የቦታው ምርታማነት፣ የተሰበሰቡ ሁሉም ምርቶች ምርታማነት፣
- የዕፅዋትና እንስሳት ስብጥር እና የታዩ ለውጦች
- የውሃ ጥራትና ብዛት፣
- የአፈር መሸርሸር፣ የአፈር መደንደን፣ ለምነት እና የካርቦን ይዘት
- የዱር እንስሳት ብዛት፣ ብዝሃ ሕይወት* እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች*
- በጣም ጥንቃቄ የሚፈልጉ ባህላዊ እና አካባቢያዊ ሀብቶች፤
- በተሳትፎው የባለ ድርሻ አካላት እርካታ*
- ለአካባቢው ማህበረሰቦች የተሰጡ የአስተዳደር ስራዎች ጥቅሞች*
- ሥራ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎች ቁጥር*
- እንደ ዋና ጥብቅ ቦታዎች የሚከለሉ ያልተነኩ የደን ገጽታዎች መጠን
- ለደን አስተዳድር የተለየ ቦታ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት*

7.3.1 የሚረጋገጡ ዒላማዎች* እና የሚገመገሙበት ድግግሞሽ ለእያንዳንዱ የአስተዳደር ዓላማ* የሚደረገውን እድገት ለመከታተል ተዘጋጅተዋል።

NTFP 7.3.1.1 ከ NTFPs ጋር በተያያዘ የሚረጋገጡ ዒላማዎች* እና የሚገመገሙበት ድግግሞሽ ለእያንዳንዱ የአስተዳደር ዓላማ* የሚደረገውን እድገት ለመከታተል ተዘጋጅተዋል።

*አረጋጋጮች: - የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*

7.4 ድርጅቱ* የክትትልና የግምገማ ውጤቶችን፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን* ወይም አዲስ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ መረጃን ለማካተት እንዲሁም ለአካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ለውጥ ምላሽ ለመስጠት የአመራር እቅድ እና የአሰራር ሰነዶችን በየጊዜው ያዘምናል እንዲሁም ያሻሽላል።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

በ FSC ትርጉም መሠረት የደን አያያዝና አጠባበቅ ዕቅድ* ማለት የአስተዳደር ተግባራት የሚገልጹ፣ የሚያረጋግጡ እና የሚቆጣጠሩ ሰነዶችን፣ ሪፖርቶችን፣ መዝገቦችን እና ካርታዎችን ያቀፈ ነው። ስለሆነም የእነዚህ የተለያዩ ሰነዶች እና ካርታዎች ተደጋጋሚነት በ 7.4.1 ላይ ከተዘረዘሩት የመረጃ ምንጮች እንዲሁም በአባሪው **ሠ** ላይ በተጠቃለለው የዐቅድ ሰነድ ዓይነት ላይ የተመሠረተ ነው።

አባሪ **ረ** የዕቅድ ማዕቀፉን ወሰን ለማብራራት የታሰበ እንጂ ትዕዛዝ የሚሰጥ አይደለም። በአጠቃላይ፣ ከባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ አዲስ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ መረጃ እንዲሁም የአካባቢ፣ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ለውጥ የሚመጡ መረጃዎች፣ አግባብነት ያለው የአስተዳደር እቅድ ሰነድ ወይም ካርታ በተደጋጋሚ እንዲሻሻል ያደርጋሉ።

7.4.1 የደን አያያዝና አጠቃቅም ዕቅዱ ከአባሪ **ረ** ጋር በሚስማማ መልኩ እንደሚከተለው ለማካተት በየጊዜው ይሻሻላል እና ይዘምናል።

1) የምስክር ወረቀት ኦዲት ውጤቶችን ጨምሮ የክትትል ውጤቶች፣

2) የግምገማ ውጤቶች

3) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ* ውጤቶች፣

4) አዲስ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ መረጃ፣ እና

5) የአካባቢ፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መቀየር።

NTFP 7.4.1.1 የ NTFPs አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ እንደሚከተለው ለማካተት በየጊዜው ይሻሻላል እና ይዘምናል።

1) የምስክር ወረቀት ኦዲት ውጤቶችን ጨምሮ የክትትል ውጤቶች፣

2) የግምገማ ውጤቶች

3) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ* ውጤቶች፣

4) አዲስ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ መረጃ፣ እና

5) የአካባቢ፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መቀየር።

*አረጋጋጮች: -የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ፤ የክትትል ሪፖርቶች፤ የባለድርሻ አካላት* የምክክር ሪፖርቶች፤ ሳይንሳዊ ሪፖርቶች፤ የምርት መሰብሰብ ዕቅዶች፤ እና ህትመቶች*

7.5 ድርጅቱ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱን ማጠቃለያ* ያለክፍያ ለህዝብ ያቀርባል። ምስጢራዊ መረጃን* ሳያካትት ሌሎች የአስተዳደር ዕቅድ* አስፈላጊ ክፍሎች በተጠየቁ ጊዜ ለተጎዱት ባለድርሻ አካላት* እንዲገኙ ይደረጋል፣ እንዲሁም የማባዛት እና የአገልግሎት ወጪ ይከፈላል።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

የዚህ መስፈርት ዓላማ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱን ማጠቃለያ በማዘጋጀት ላይ ለድርጅቱ የአስተዳደር ሸክም በመቀነስ እና አጠቃላይ መረጃዎች እንዲቀርቡ በማረጋገጥ መካከል ሚዛን መፈለግ ነው። የአስተዳደር ሸክም የሚቀንስ ከሆነ አጠቃላይ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ* ሊቀርብ ይችላል። ምስጢራዊ መረጃ* ምሳሌዎች የሚከተሉትን መረጃ እና ይዘት ያካትታሉ፡-

- ከኢንቨስትመንት ውሳኔዎች ጋር የተያያዙ
- ስለ አዕምሯዊ ንብረት ሙብቶች*
- የደንበኛው ሚስጥራዊነት የጠበቀ
- በህግ ሚስጥራዊነት የጠበቀ
- ስርጭታቸው* የዱር እንስሳትን እና የኑሮ ቦታዎችን ጥበቃ* አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሲሆን* እና
- ለአገሬው ተወላጆች ወይም ለአካባቢው ማህበረሰቦች ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ስላላቸው ቦታዎች (መስፈርት 3.5 እና 4.7 ይመልከቱ) እነዚህ ቡድኖች በጠየቁት መሠረት

7.5.1 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ማጠቃለያ* ለባለድርሻ አካላት በሚገባ የሚረዳ ቅርጸት ካርታዎችን ጨምሮና ሚስጥራዊ መረጃን ሳይጨምር* ለሕዝብ በነፃ እንዲቀርብ ተደርጓል።

7.5.2 የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ አግባብነት ያላቸው ክፍሎች*፣ ምስጢራዊ መረጃን ሳይጨምር፣ ለተጎዱት ባለድርሻ አካላት* በተጠየቁበት ጊዜ በትክክለኛ የማባዛት እና የአገልግሎት ወጪዎች ይገኛሉ።

አረጋጋጮች: - የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ማጠቃለያ ምስጢራዊ መረጃን ሳይጨምር፣

**7.6 ድርጅቱ* በአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬና አደጋ* ላይ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ተጎጂዎቹን ባለድርሻ አካላት* በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ እና ክትትል ሂደቱ ውስጥ በንቃት እና በግልፅ ያሳትፋል፤ እንዲሁም ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት* ሲጠይቁ ያሳትፋል።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የትሰጠ መመሪያ**

**በባህል ተገቢ* የሆኑ ሂደቶች የባህል ልዩነቶችን ያስተናግዳሉ፤ እንደ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ድርድርን የመምረጥ ፍላጎት፤ ለፉክክር፣ ለትብብርና ለግጭት ያላቸው አመለካከት፤ በቅሬታ አቅራቢዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የመጠበቅ ፍላጎት፤ ሥልጣን፣ ማኅበራዊ ደረጃና አቋም፤ ዓለምን የመረዳትና የመተርጎም መንገዶች፤ የጊዜ አጠቃቀም ፅንሰ ሀሳቦች፤ ለሶስተኛ ወገኖች ያላቸው አመለካከት፤ እና ሰፋ ያለ ማህበራዊና ተቋማዊ አካባቢ።**

**የደረጃ አዘጋጆች በደረጃ አመልካች* 7.6.1 ላይ የተገለጹትን መስፈርቶች* ለመከታተል ከባህል ጋር የሚስማማ* የግንኙነት* ሂደቶችን* ያዘጋጃሉ፣ ይህም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንደ ዒላማው ቡድን የሚለዩ ለውጦችን ያካትታል።**

7፣6፣1 ባህላዊ ተገቢ* ተሳትፎ* ተጎጂዎቹ ባለድርሻ አካላት* በሚከተሉት ሂደቶች ውስጥ በንቃት እና በግልፅ እንዲሳተፉ ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል፡-

1) የግጭት መፍትሄ* ሂደቶች (መስፈርት 1.6፣ መስፈርት 2.6*፣ መስፈርት 4.6)፣
2) የኑሮ ምንዳ ትርጓሜ* (መስፈርት* 2.4)
3) መብቶችን መለየት (መስፈርት* 3.1፣ መስፈርት* 4.1) ፣ ሀገር-በቀል ባህላዊ የመሬት ገጽታ* (መስፈርት* 3.1)፣ ቦታዎች (መስፈርት 3.5፣ መስፈርት 4.7) እና ተፅእኖዎች (መስፈርት 4.5)፣
4) የአካባቢ ማህበረሰቦች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ተግባራት (መስፈርት 4.4*) እና
5) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ግምገማ፣ አስተዳደር እና ክትትል (መመዘኛ* 9.1፣ መመዘኛ* 9.2,፣ መመዘኛ* 9.4).

SLIMF 7.6.1.1* በ1-5 ላይ የተዘረዘሩትን መሠረታዊ ነገሮች በማዘጋጀት ረገድ የተጎዱ ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ ለማድረግ ባህላዊ ሁኔታ ተገቢ የሆነ* ተሳትፎ* ጥቅም ላይ ይውላል።

1) የግጭት መፍትሄ* ሂደቶች (መስፈርት 1.6፣ መስፈርት 2.6*፣ መስፈርት 4.6)፣
2) የኑሮ ምንዳ ትርጓሜ* (መስፈርት* 2.4)
3) መብቶችን መለየት (መስፈርት* 3.1፣ መስፈርት* 4.1) ፣ ቦታዎች (መስፈርት 3.5፣ መስፈርት 4.7) እና ተፅእኖዎች (መስፈርት 4.5)፣
4) የአካባቢ ማህበረሰቦች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ተግባራት (መስፈርት 4.4*) እና
5) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ግምገማ፣ አስተዳደር እና ክትትል (መመዘኛ* 9.1፣ መመዘኛ* 9.2,፣ መመዘኛ* 9.4).

7.6.2 በባህል ተገቢ* ተሳትፎ*

1) ተስማሚ ተወካዮችን እና የእውቂያ ነጥቦችን መወሰን (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአካባቢ ተቋማትን፣ ድርጅቶችን እና ባለሥልጣናት)

2) በጋራ የሚስማሙ የግንኙነት ሰርጦችን መወሰን መረጃ በሁለቱም አቅጣጫ እንዲፈስ፣

3) ሁሉም ተዋናዮች (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ አናሳዎች) በፍትሃዊነት የተወከሉና የተሰማሩ፣

4) ሁሉንም ስብሰባዎች፣ ሁሉንም ነጥቦች እና ስምምነቶችን ማረጋገጥ የደረሱበት ደረጃ ተመዝግቧል፣

5) የስብሰባዎች መዝገብ ይዘት እንዲፀድቅ ማድረግ፣ እና

6) በባህላዊ ሁኔታ ተገቢ* የሆነ ተሳትፎ* ውጤቱን ማረጋገጥ እንቅስቃሴዎች ከተሳተፉት ጋር ይጋራሉ።

7.6.3 የተጎዱት የመብት ባለቤቶች* እና የተጎዱት ባለድርሻ አካላት* በእነርሱ ፍላጎት ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ የአስተዳደር ተግባራት የክትትልና እቅድ አወጣጥ ሂደቶች ውስጥ በባህል ተገቢ* ተሳትፎ* እንዲያደርጉ እድል ይሰጣቸዋል።

NTFP 7.6.3.1 የተጎዱት የመብት ባለቤቶች* እና የተጎዱት ባለድርሻ አካላት* በእነርሱ ፍላጎት ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ የNTFPs አስተዳደር ተግባራት የክትትልና እቅድ አወጣጥ ሂደቶች ውስጥ በባህል ተገቢ* ተሳትፎ* እንዲያደርጉ እድል ይሰጣቸዋል።

SLIMF 7.6.3.1 የቁጥጥርና የክትትል ተግባራት በሚዘጋጁበትና በሚተገበሩበት ጊዜ ስጋቶቻቸው መመለሳቸውን ለማረጋገጥ ከባህል አንፃር ተገቢ የሆነ ተሳትፎ ከተጎዱት ባለድርሻ አካላት እና ከአገሬው ተወላጆች ጋር ይጠናቀቃል

7.6.4 ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ሲጠይቁ፤ ፍላጎታቸውን የሚነኩ የአስተዳደር ተግባራት በክትትልና እቅድ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እድል ይሰጣቸዋል።

NTFP 7.6.4.1 ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ሲጠይቁ፤ ፍላጎታቸውን የሚነኩ የNTFPs አስተዳደር ተግባራት በክትትልና እቅድ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እድል ይሰጣቸዋል።

አረጋጋጮች: - በምክክር ሂደት የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት መዝገብ*፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ምክክር ሪፖርት

## መርህ* 8: ክትትልና ግምገማ

ድርጅቱ የአስተዳደር ዓላማዎችን ለማሳካት የሄደበት ሂደት የአስተዳደር ተግባራት ተፅዕኖና ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ ሁኔታ ከአስተዳደር ተግባራት ስፋት፣ ጥንካሬና አደጋ ጋር የሚመሳሰል ክትትልና ግምገማ የሚደረግበት መሆኑን ማሳየት አለበት።

8.1 ድርጅቱ የፖሊሲዎቹን እና የአመራር ዓላማዎችን ጨምሮ የአመራር እቅዱን አፈፃፀም፣ የታቀዱትን ተግባራት የሄደበት ሂደት እና ሊረጋገጥ የሚችል ዒላማዎችን ማሳካት ይከታተላል

8.1.1 የአስተዳደር ዕቅዱን ተግባራዊነት፣የአስተዳደር ፖሊሲዎቹን እና የአስተዳደር ዓላማዎችን እንዲሁም ሊረጋገጡ የሚችሉ ዒላማዎችን ማሳካት ለመከታተል የሚያስችሉ ሂደቶች ሰነድ ተይዘዋል እንዲሁም ተተግብረዋል።

NTFP 8.1.1.1 የNTFPs አስተዳደር ዕቅዱን ተግባራዊነት፣የአስተዳደር ፖሊሲዎቹን እና የአስተዳደር ዓላማዎችን እንዲሁም ሊረጋገጡ የሚችሉ ዒላማዎችን ማሳካት ለመከታተል የሚያስችሉ ሂደቶች ሰነድ ተይዘዋል እንዲሁም ተተግብረዋል።

**አረጋጋጮች**: - የቁጥጥር ሂደቶች ሰነድ

8.2 ድርጅቱ* ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን እንዲሁም የአካባቢ ሁኔታ ለውጦችን ይከታተላል እንዲሁም ይገመግማል።

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

ይህ መስፈርት ሦስት የተለያዩ ምድቦች ክትትል እንዲደረግ ይጠይቃል፤ በመርህ 10 የተመለከቱ የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ፤ ከ1-5 መርሆዎች የተመለከቱትን ተግባራት ማህበራዊ ተፅዕኖ እንዲሁም በ9 መርህ የተመለከቱትን ተሳትፎ፤ በ5፣ 6 እና 9ኛው መርህ የተመለከቱት የአካባቢ ሁኔታዎች እና ለውጦች ለተለየ የክትትል መስፈርቶች እባክዎ ወደ አባሪ **ሰ** ይመልከቱ (አመልካች* 8.2.1 እና 8.2.2)።

8.2.1 የአስተዳደር ተግባራት ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎች ከአባሪ **ሰ** ጋር በሚስማማ መልኩ ይከታተላሉ።

NTFP 8.2.1.1 የ NTFP የአስተዳደር ተግባራት ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎች ከአባሪ **ሰ** ጋር በሚስማማ መልኩ ይከታተላሉ።

SLIMF 8.2.1.1 የአስተዳደር ተግባራት ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎች ከአባሪ **ሰ** ጋር በሚስማማ መልኩ ይከታተላሉ።

8.2.2 በአከባቢ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ለውጦች በአንቀጽ **ሰ** ላይ በተጠቀሰው መሠረት ክትትል ይደረግባቸዋል።

SLIMF 8.2.2.1 በአከባቢ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ለውጦች በአንቀጽ **ሰ** ላይ በተጠቀሰው መሠረት ክትትል ይደረግባቸዋል።

**አረጋጋጮች፡-** የክትትል ሪፖርቶች፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርቶች፤ የክትትል ሂደቶች እና ሪፖርቶች

8.3 ድርጅቱ የክትትል እና የግምገማ ውጤቶችን በመተንተን የዚህን ትንታኔ ውጤቶች ወደ እቅድ አወጣጥ ሂደቱ መልሶ ያስገባል።

8.3.1 የቁጥጥር ውጤቶች የዕቅድ ሂደቱን እና የተገኘውን የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ በየጊዜው ለማዘመን እንዲረዱ ከሁኔታዎች ጋር የሚስማሙ አስተዳደር ሂደቶች ይተገበራሉ።

NTFP 8.3.1.1 የቁጥጥር ውጤቶች የዕቅድ ሂደቱን እና የተገኘውን የNTFPs አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ በየጊዜው ለማዘመን እንዲረዱ ከሁኔታዎች ጋር የሚስማሙ የNTFPs አስተዳደር ሂደቶች ይተገበራሉ።

8.3.2 የክትትል ውጤቶች ከ FSC ደረጃ ጋር አለመጣጣም ካሳዩ ከዚያ የአስተዳደር ዓላማዎች፣ ሊረጋገጥ የሚችል ዒላማዎች እና/ወይም የአስተዳደር ተግባራት ይሻሻላሉ።

***አረጋጋጮች፡-*** የክትትል ሪፖርቶች; የተተነተኑ የክትትል መረጃዎች; የተከለሰ (የተሻሻለ) የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*

**8.4 ድርጅቱ በግላዊነት የተጠበቀ መረጃን ሳይጨምር የክትትል ውጤቶችን ማጠቃለያ በነፃ ለህዝብ ያቀርባል**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

የዚህ መስፈርት ዓላማ የክትትል ውጤቶችን ማጠቃለያ በማዘጋጀት የድርጅቱን አስተዳደር ጫና ለመቀነስ እና አጠቃላይ መረጃ እንዲሰጥ በማረጋገጥ መካከል ሚዛን መፈለግ ነው። ይህ የአስተዳደር ጫና የሚቀንስ ከሆነ የክትትል ውጤቶች በሙሉ ሊቀርቡ ይችላሉ። ምስጢራዊ መረጃ ምሳሌዎች ከመስፈርት 7.5 ጋር በሚገኘው መመሪያ ውስጥ ቀርበዋል።

8.4.1 የክትትል ውጤቶች ማጠቃለያ ለባለድርሻ አካላት በሚገባ በሚረዳ መልኩ ካርታዎችን ጨምሮ እና ሚስጥራዊ መረጃን ሳይጨምር ከአባሪ **ሰ** ጋር በሚስማማ መልኩ ያለክፍያ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል።

***አረጋጋጮች፡-*** የተጠቃለለ የክትትል ሪፖርት

8.5 ድርጅቱ የ FSC የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው ለገበያ የሚቀርቡ ከማንኛውም ለደን አስተዳደር የተለዩ ቦታዎች የሚመጡ ምርቶች በየዓመቱ ከሚታሰበው ምርት ጋር የሚመሳሰል ምንጭ እና መጠን ለማሳየት ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ ጋር የሚመጣጠን የመከታተያ እና የማረጋገጫ ስርዓት ይኖረዋል እንዲሁም ተግባራዊ ያደርጋል።

8.5.1 የFSC ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው ለገበያ የሚቀርቡ ሁሉም ምርቶች እንዲከታተሉ እና እንዲያረጋግጡ የሚያስችል ስርዓት ተተግብሯል። ከዚህም ውስጥ፡-

1) የንግድ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል በጠየቀው መሠረት የግብይት ማረጋገጫ* የ FSC ግብይት* መረጃዎችን በማቅረብ ይደገፋል።

2) የፋይበር ምርመራ በሰርተፊኬቱ አካል ጥያቄ መሠረት የቁሳቁስ ናሙናዎችን እና ሕብረ ሕዋሳት ናሙናዎችን እና ስለ ዝርያው ጥንቅር መረጃዎችን ለምርመራ በማቅረብ ይደገፋል።

NTFP 8.5.1.1 የFSC ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው ለገበያ የሚቀርቡ ሁሉም የNTFPs ምርቶች እንዲከታተሉ እና እንዲያረጋግጡ የሚያስችል ስርዓት ተተግብሯል።

8.5.2 ስለ ሁሉም የተሸጡ ምርቶች መረጃ ይዘጋጃል እና ይመዘገባል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ; -

1) የተለመደ እና ሳይንሳዊ የዝርያ ስም

2) የምርት ስም ወይም መግለጫ

3) የምርት መጠን (ወይም ብዛት)

4) ምርቱን ዛፎች ከሚቆረጡበትና ከሚጓጓዙበት ክፍል መነሻ ምንጭ ለመከታተል የሚረዳ መረጃ

5) ዛፎች የሚቆረጡበትና የተጓጓዙበት ቀን

6) መሰረታዊ የማምረት ሂደት ስራዎች በደን ውስጥ የሚከናወኑ ከሆነ ቀኑ እና የተመረተው መጠን፣ እና

7) ቁሳቁሱ የ FSC የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ የተሸጠ መሆን አለመሆኑ

NTFP 8.5.2.1 ስለተሸጡት የ NTFP ምርቶች ሁሉ መረጃ ተሰብስቦ እንዲሰነድ ይደረጋል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

1) የተለመደ እና ሳይንሳዊ የዝርያ ስም

2) የምርት ስም ወይም መግለጫ

3) የምርት መጠን (ወይም ብዛት)

4) የNTFPs ምርቱን ከመነሻ ምንጭ ለመከታተል የሚረዳ መረጃ

5) የNTFPs ምርት መነሻ ቀን

6) መሰረታዊ የማምረት ሂደት ስራዎች በደን ውስጥ የሚከናወኑ ከሆነ ቀኑ እና የተመረተው መጠን፣ እና

7) ቁሳቁሱ የ FSC የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ የተሸጠ መሆን አለመሆኑ

NTFP 8.5.2.2 ማር (እና/ወይም ሌሎች የንብ ምርቶች እና የሚመነጩ ነገሮች/exudates) ከ FSC የይገባኛል ጥያቄ ጋር ከመሸጡ በፊት ከተሰበሰበው የአበባ-ዱቄት ቢያንስ 50% የሚሆነው በ FSC-certified MU ውስጥ እንደሚመጣ ከሁሉ ተሽሎ በተገኘ መረጃ ወይም በአበባ-ዱቄት ትንታኔ ላይ የተመሠረተ ነው፤ FSC 100%።

SLIMF 8.5.2.3 ስለ ሁሉም የተሸጡ ምርቶች መረጃ ይዘጋጃል እና ይመዘገባል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ; -

1) የተለመደ እና ሳይንሳዊ የዝርያ ስም

2) የምርት ስም ወይም መግለጫ

3) የምርት መጠን (ወይም ብዛት)

4) ምርቱን ዛፎች ከሚቆረጡበትና ከሚጓጓዙበት ክፍል መነሻ ምንጭ ለመከታተል የሚረዳ መረጃ

5) ዛፎች የሚቆረጡበትና የተጓጓዙበት ቀን

6) መሰረታዊ የማምረት ሂደት ስራዎች በደን ውስጥ የሚከናወኑ ከሆነ ቀኑ እና የተመረተው መጠን፣ እና

7) ቁሳቁሱ የ FSC የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ የተሸጠ መሆን አለመሆኑ

NTFP 8.5.2.4 ስለተሸጡት የ NTFP ምርቶች ሁሉ መረጃ ተሰብስቦ እንዲሰነድ ይደረጋል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

1) የተለመደ እና ሳይንሳዊ የዝርያ ስም

2) የምርት ስም ወይም መግለጫ

3) የምርት መጠን (ወይም ብዛት)

4) የ ምርት የሚመረቱበት/የሚሰበሰቡበት ክፍል መነሻ ምንጭ ለመከታተል የሚረዳ መረጃ

5) የተሰበሰበበት ቀን

6) መሰረታዊ የማምረት ሂደት ስራዎች በደን ውስጥ የሚከናወኑ ከሆነ ቀኑ እና የተመረተው መጠን፣ እና

7) NTFP የFSC የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ የተሸጠ መሆን አለመሆኑ። አዎ ከሆነ፣ የ CoC የምስክር ወረቀት ቁጥር እና የደንበኛው የእውቂያ መረጃ

8.5.3 የሽያጭ ሂሳብ ወይም ተመሳሳይ ሰነዶች ከ FSC የይገባኛል ጥያቄ ጋር ለተሸጡ ሁሉም ምርቶች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ይቀመጣሉ፤ የሚከተሉትን መረጃዎች በትንሹ ያካትታል፡-

1) የገዢው ስም እና አድራሻ

2) የሽያጭ ቀን፤

3) የተለመደ እና ሳይንሳዊ ዝርያ ስም

4) የምርት መግለጫ

5) የተሸጠው መጠን (ወይም ብዛት)

6) የምስክር ወረቀት ኮድ፣ እና

7) የ FSC የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ምርቶች የተሸጡበት መለያ የ FSC ይገባኛል "FSC 100%"

NTFP 8.5.3.1 የሽያጭ ሂሳብ ወይም ተመሳሳይ ሰነዶች ከ FSC የይገባኛል ጥያቄ ጋር ለተሸጡ ሁሉም የNTFPs ምርቶች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ይቀመጣሉ፤ የሚከተሉትን መረጃዎች በትንሹ ያካትታል፡-

1) የገዢው ስም እና አድራሻ

2) የሽያጭ ቀን፤

3) የተለመደ እና ሳይንሳዊ ዝርያ ስም

4) የምርት አይነት

5) የተሸጠው መጠን (ወይም ብዛት)

6) የደን አያያዝና አጠቃቀም / የቁጥጥር ሰንሰለት የምስክር ወረቀት ኮድ እና

7) የ FSC የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ምርቶች የተሸጡበት መለያ የ FSC ይገባኛል “FSC 100%”

SLIMF 8.5.3.1 የሽያጭ ሂሳብ ወይም ተመሳሳይ ሰነዶች ከ FSC የይገባኛል ጥያቄ ጋር ለተሸጡ ሁሉም ምርቶች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ይቀመጣሉ፤ የሚከተሉትን መረጃዎች በትንሹ ያካትታል፡-

1) የገዢው ስም እና አድራሻ

2) የሽያጭ ቀን፤

3) የተለመደ እና ሳይንሳዊ ዝርያ ስም

4) የምርት መግለጫ

5) የተሸጠው መጠን (ወይም ብዛት)

6) የምስክር ወረቀት ኮድ፣ እና

7) የ FSC የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ምርቶች የተሸጡበት መለያ የ FSC ይገባኛል “FSC 100%”

አረጋጋጮች: የመከታተያ ሂደት፣ ሁሉም የግብይት መረጃዎች (የሂሳብ ሰነዶች፣ የግዢ ትዕዛዞች፣ የማስረከቢያ ወረቀቶች፣ የጭነት ወረቀቶች፣ ደረሰኞች)

**መርህ* 9: ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች***

ድርጅቱ* ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ* በመተግበር ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን* ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች* ይጠብቃል ወይም ያሻሽላል።

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

የደረጃ አዘጋጆች በሀገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመለየት፣ ለማስተዳደር እና ለመከታተል የሚያስችል መሣሪያ የሆነ ብሔራዊ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት* (HCV) ማዕቀፍ ያዘጋጃሉ።

ይህንን ብሔራዊ HCV ማዕቀፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ፣ የደረጃ አዘጋጆች የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡-

- በ HCV ሁብት ጥምረት/ Resource Network/ የተዘጋጀ የከፍተኛ ጥበቃ እሴቶችን ለመለየት የጋራ መመሪያ፣ (በ FSC ድረ-ገጽ ይገኛል)
- የ FSC ደረጃ በደረጃ መመሪያ ለ SLIMFs (በ FSC ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል)
- አግባብነት ያላቸው የመረጃ ቋቶችና ካርታዎች፣
- ግሎባል ፎረስት ዎች / Global Forest Watch / ያልተነኩ የደን ገጽታ ካርታዎች (2015) www.globalforestwatch.org፣ ወይም የተጣራ ምዝገባ ዘዴን በመጠቀም በቅርብ ጊዜ እና በትክክለኛው ያልተነኩ የደን መልክዓ ምድሮች ላይ የተመሠረቱ ሌሎች ካርታዎች፣

- ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች፣ ከተጎዱት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከሚመለከታቸው የአካባቢና የክልል ባለሙያዎች ጋር ባህላዊ ተገቢ የሆነ ተሳትፎ ማድረግ፣
- የ FSC መመሪያ ነፃ ቅድመ እና መረጃ የተገኘበት ስምምነት* ላይ (2017)
- ደረጃ አዘጋጆች ከደረጃ እና ጥንካሬ አንፃር ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራት አደጋ ለመቋቋም መመሪያ (2016) ፣
- የ FSC መመሪያ ለደን ሥራ አስኪያጆች ስለ HCV አያያዝ፣
- ከዚህ በታች የተቀመጡ አባሪ ሸ እና ቀ
- ሌሎች የሚገኙ ምንጮች

የደረጃ አዘጋጆች በብሔራዊ ደረጃ እና በጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃ ላይ በድርጅቱ ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን በመለየት እና እነዚህን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የአስተዳደር ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት ላይ ብሔራዊ የHCV ማዕቀፍ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ያብራራሉ።

የደረጃ አዘጋጆች ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን* ወሳኝ፣ መሠረታዊ፣ ጉልህ* ወይም ጠቃሚ አድርገው የሚመለከቱትን የጥንቃቄ አቀራረብ* መርህ የሚተገበሩ አመልካቾችን* ያዘጋጃሉ፤ ስለሆነም ማንኛውም ለከፍተኛ የጥበቃ እሴት* ስጋት የሚጋለጥ ከባድ ወይም የማይመለስ ጉዳት የሚያስከትል ስጋት ተደርጎ ይቆጠራል። የደረጃ አዘጋጆች ለሀገራዊ HCV ማዕቀፍ ማዘጋጀት የጥንቃቄ አካሄድ* መርህ ተግባራዊ ያደርጋሉ።

የደረጃ አዘጋጆች አስፈላጊ ከሆነ በመርህ 9 መሠረት ባሉት አመልካቾች ጽሑፍ ውስጥ ለሀገር አቀፍ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ማዕቀፍ (አባሪ በ) በግልፅ ማጣቀሻ ያደርጋሉ።

**9.1 ድርጅቱ ከተጎዱት ባለድርሻ አካላት፣ ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት እና ከሌሎች መንገዶችና ምንጮች ጋር በመተባበር የሚከተሉትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች መኖራቸውንና ሁኔታቸውን ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ፣ ከአስተዳደር ተግባራት ተፅዕኖዎች ስፋት፣ ጥንካሬና አደጋ እንዲሁም ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች የመከሰታቸው እድል ጋር የሚመሳሰል ሆኖ መገምገም እና መመዝገብ ይኖርበታል፡-**

**HCV 1-የዝርያዎች ብዝሃነት ማለት በዓለም፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጉልህ የሆኑ የአካባቢያዊ ዝርያዎችን እንዲሁም ብርቅዬ-ብቸኛ ዝርያ፣ ብርቅዬ፣ በመጥፋት ወይም አደጋ ላይ ያሉ ዝርያዎችን ጨምሮ የሥነ=ሕይወት ብዝሃነት መከማቸት።**

**HCV 2 የመሬት ገጽታ ደረጃ ሥርዓተ ምህዳሮች ሕብር ማለት ያልተነኩ የደን ገጽታዎች እና ትላልቅ የመሬት ገጽታ ደረጃ ሥርዓተ ምህዳሮች እና በዓለም፣ በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ ጉልህ የሆኑና በተፈጥሮ የስርጭትና የብዛት ንድፍ ውስጥ የአብዛኛው በተፈጥሮ ውስጥ የሚገኙትን ሊኖሩ-የሚችሉ ዝርያዎችን / viable population/ የሚይዙ።**

**HCV 3 ሥርዓተ ምህዳሮች እና መኖሪያ ቦታዎች ማለት ብርቅዬ፣ በመጥፋት ወይም አደጋ ላይ የወደቁ ሥርዓተ ምህዳሮች፣ መኖሪያ ቦታዎች ወይም መጠጊያዎች።**

**HCV 4 ወሳኝ* የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ማለት የውሃ ተፋሰሶችን መከላከል እና የተጋለጡ የአፈር እና ተዳፋትነት ያለው መሬት መሸርሸርን መቆጣጠር ጨምሮ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ መሠረታዊ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች።**

**HCV 5 የማህበረሰብ ፍላጎቶች ማለት ከአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም ከአገሬው ተወላጆች ጋር በመተባበር የተለዩትን የአካባቢው ማህበረሰቦች ወይም የአገሬው ተወላጆች መሠረታዊ ፍላጎቶች (ለኑሮ፣ ለጤና፣ ለምግብ፣ ለዉሃ ወዘተ) ለማሟላት ወሳኝ የሆኑ ቦታዎችና ሀብቶች።**

**HCV 6 ባህላዊ እሴቶች ማለት ዓለም አቀፍ ወይም ብሔራዊ ባህላዊ፣ አርኪኦሎጂያዊ ወይም ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸው እና/ወይም ለአካባቢያዊ ማህበረሰቦች ወይም ለአገሬው ተወላጆች ባህላዊ ባህል ወሳኝ* ባህላዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሃይማኖታዊ/መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸው፣ ከእነዚህ አካባቢያዊ ማህበረሰቦች ወይም ከአገሬው ተወላጆች ጋር በመተባበር የተለዩ ቦታዎች፣ ሀብቶች፣ መኖሪያ ቦታዎች እና የመሬት ገፅታዎች**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

*የደረጃ አዘጋጆች ድርጅቱ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመለየት የሚጠቀምበትን ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃ* (አመልካች* 9.1.1) ይገልጻሉ፤ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፡-*

*- ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች* ዳሰሳዎች እና ያልተነኩ የደን ገጽታዎች* ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ* ግምገማዎች፣*

*- አግባብነት ያላቸው የመረጃ ቋቶች እና ካርታዎች፤*

*- ግሎባል ፎረስት ዎች / Global Forest Watch / ያልተነኩ የደን ገጽታ ካርታዎች (2015) www.globalforestwatch.org፣ ወይም የተጣራ ምዝገባ ዘዴን በመጠቀም በቅርብ ጊዜ እና በትክክለኛው ያልተነኩ የደን መልክዓ ምድሮች ላይ የተመሠረቱ ሌሎች ካርታዎች፣*

*- ከተጎዱት የሙብት ባለቤቶች፣ ከተጎዱት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከሚመለከታቸው የአካባቢና የክልል ባለሙያዎች ጋር ባህላዊ ተገቢ የሆነ ተሳትፎ ማድረግ፣*

*- የ FSC መመሪያ ነፃ ቅድመ እና መረጃ የተገኘበት ስምምነት* ላይ (2017)*

*- ደረጃ አዘጋጆች ከደረጃ እና ጥንካሬ አንፃር ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራት አደጋ ለመቋቋም መመሪያ (2016) ፣*

*- የ FSC መመሪያ ለደን ሥራ አስኪያጆች ስለ HCV አያያዝ፣*

*- ሌሎች የሚገኙ ምንጮች፣ እና*

*- ከድርጅቱ ውጭ የሆኑ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች* ውጤቱን ይገመግማሉ።*

*የደረጃ አዘጋጆች ያልተነኩ የደን ገጽታዎች* ለመገምገም ከአባሪ ሸ ጋር የሚስማሙ አመልካቾችን* ያዘጋጃሉ።*

9.1.1 ግምገማው የሚጠናቀቀው በመስፈርት 9.1 ላይ በተገለጸው መሠረት ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ምድብ 1-6 አካባቢን እና ሁኔታን የሚይዝ ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃን በመጠቀም ነው፤ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸው ቦታዎች የሚተማመኑባችው እና ሁኔታቸው

SlIMF 9.1.1.1 ግምገማው የሚጠናቀቀው በመስፈርት 9.1 ላይ በተገለጸው መሠረት ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ምድብ 1-6 አካባቢን እና ሁኔታን የሚይዝ ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃን በመጠቀም ነው፤ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸው ቦታዎች የሚተማመኑባችው እና ሁኔታቸው

9.1.2 ይህ ግምገማ እ.ኤ.አ ከጥር 1 ቀን 2017 ጀምሮ ያልተነኩ የደን ገጽታዎች መለየትን ያጠቃልላል ።

9.1.3 ግምገማው በከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ጥበቃ ላይ ፍላጎት ካላቸው ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች እና ከተጎዱት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በባህል ተገቢ በሆነ መልኩ የተደረገውን ተሳትፎ ውጤቶችን ይጠቀማል።

SLIMF 9.1.3.1 ግምገማው በከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ጥበቃ ላይ ፍላጎት ካላቸው ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች እና ከተጎዱት እና ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በባህል ተገቢ በሆነ መልኩ የተደረገውን ተሳትፎ ውጤቶችን ይጠቀማል።

**አረጋጋጮች**:- የ HCV* ማዕቀፍ፣ የ HCV* የግምገማ ሪፖርት፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ዘዴዎች* *፤ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት* እና ስጋታቸውን የሚያሳይ መዝገብ፣ የባለድርሻ አካላት* ተሳትፎ* ውጤቶች፤ HCV * በግልጽ በካርታ ተቀምጧል

**9.2 ድርጅቱ ከተጎዱት ባለድርሻ አካላት፣ ፍላጎት ካላቸው ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች ጋር በመሳተፍ የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን የሚጠብቁ እና/ወይም የሚያሻሽሉ ውጤታማ ስልቶችን ያዘጋጃል።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:**

ያልተነኩ የደን ገጽታዎች ላሏቸው አገሮች/ክልሎች ደረጃ አዘጋጆች ከአባሪ **ሸ** ክፍል **ለ** ጋር የሚስማማ የ 80% ያልተነኩ የደን ገጽታዎች አጠቃላይ አካባቢን እንደ ዋና ቦታዎች ለደን አስተዳደር በተለየው ቦታ ውስጥ ተከልለው የሚጠብቁ አመልካቾችን ያዘጋጃሉ። ደረጃ አዘጋጆች ከ80 በመቶ የተለየ ገደብ ማዘጋጀት የሚችሉት በአባሪ **ሸ** ክፍል ***ሀ*** ጋር በሚስማማ ሂደት ነው።

9.2.1 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን አደጋ ላይ የምጥሉ ከሁሉ ተሽሎ የተገኘ መረጃዎች በመጠቀም ተለይተዋል።

9.2.2 የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል እና ሊጎዱ የሚችሉ የአስተዳደር ተግባራትን ከመተግበር በፊት ተጓዳኝ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸውን ቦታዎች ለመጠበቅ የአስተዳደር ስልቶችና እርምጃዎች ይዘጋጃሉ።

9.2.3 የተጎዱ የመብት ባለቤቶች፣ የተጎዱና ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የአስተዳደር ስልቶችን እና እርምጃዎችን በማዘጋጀት ላይ ተሳትፈዋል።

9.2.4 ዋና ጥብቅ ቦታዎችን ለመጠበቅ የአስተዳደር ስልቶች ተዘጋጅተዋል።

9.2.5 አብዛኛው ያልተንኩ የደን ገጽታ እንደ ዋና ጥብቅ ቦታ ተወስኗል።

9.2.6 የተቀረጹ ስልቶች ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል ውጤታማ ናቸው።

9.2.7 የአስተዳደር ስልቶች ዋና ጥብቅ ቦታዎች ውስጥ የተገደበ የኢንዱስትሪ ተግባራትን የሚፈቅዱት፣ ሁሉም የኢንዱስትሪ ተግባራት ተፅእኖዎች የተቆራረጡ የደን ቦታዎችን ጨምሮ:-

1) በዋና ጥብቅ ቦታዎች በጣም ውስን በሆነ ክፍል ውስጥ የተገደቡ ሲሆኑ፤

2) ዋና ጥብቅ ቦታ* ከ50 ሺህ ሄክታር በታች መቀነስ በማይቻልበት፣ እና

3) ግልጽ፣ ጉልህ፣ ተጨማሪ፣ የረጅም ጊዜ የጥበቃ እና ማህበራዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ከሆነ ነው።

*አረጋጋጮች፡- የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፤ አባሪ **ቀ**-HCV* ማዕቀፍ፤ የባለድርሻ አካላት የምክክር ሪፖርት፤ የHCV ክትትል መዝገቦች*

9.3 ድርጅቱ የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች የሚጠብቁ እና/ወይም የሚያሻሽሉ ስልቶችን እና እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋል። እነዚህ ስልቶች እና እርምጃዎች ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤ እንዲሁም ከአስተዳደሩ ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናሉ።

9.3.1 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸው ቦታዎች* እነሱ የሚወሰኑበት ቦታ እንዲሁም የተዘጋጁትን ስልቶች ተግባራዊ በማድረግም ጭምር ይጠበቃሉ እና/ወይም ይሻሻላሉ።

SLIMF 9.3.1.1 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያላቸው ቦታዎች* እነሱ የሚወሰኑበት ቦታ እንዲሁም የተዘጋጁትን ስልቶች ተግባራዊ በማድረግም ጭምር ይጠበቃሉ እና/ወይም ይሻሻላሉ።

9.3.2 ሳይንሳዊ መረጃው ያልተሟላ ወይም አሳማኝ ባልሆነበት ጊዜም ቢሆን እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ተጋላጭነት እና በጣም ጥንቃቄ መፈለጉ እርግጠኛ ባልሆነበት ጊዜም ቢሆን ስልቶቹ እና እርምጃዎቹ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ጉዳቶችን ይከላከላል እና ሰጋቶችን ያስወግዳል።

SLIMF 9.3.2.1 ሳይንሳዊ መረጃው ያልተሟላ ወይም አሳማኝ ባልሆነበት ጊዜም ቢሆን እና ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ተጋላጭነት እና በጣም ጥንቃቄ መፈለጉ እርግጠኛ ባልሆነበት ጊዜም ቢሆን ስልቶቹ እና እርምጃዎቹ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ጉዳቶችን ይከላከላል እና ሰጋቶችን ያስወግዳል።

9.3.3 ዋና ጥብቅ ቦታዎች* በመስፈርት 9-2 በሚስማማ መልኩ የተከለሉ* ናቸው።

9.3.4 በዋና ጥብቅ ቦታዎች* ያለው አነስተኛ የኢንዱስትሪ ተግባራት ከአመልካች* 9.2.7 ጋር የሚስማማ ነው።

9.3.5 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን የሚጎዱ እንቅስቃሴዎች ወዲያውኑ ያቆማሉ እናም ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመመለስ እና ለመጠበቅ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

SLIMF 9.3.5.1 ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን የሚጎዱ እንቅስቃሴዎች ወዲያውኑ ያቆማሉ እናም ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመመለስ እና ለመጠበቅ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

***አረጋጋጮች***: የክትትል ሪፖርቶች፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶች፤ የመስክ ጉብኝቶች

9.4 ድርጅቱ የከፍተኛ ጥበቃ እሴቶችን ሁኔታ ለመገምገም በየጊዜው ክትትል መደረጉን ያረጋግጣል እንዲሁም ውጤታማ ጥበቃቸውን ለማረጋገጥ የአስተዳደር ስልቶቹን ያስተካክላል። ክትትሉ ከአስተዳደሩ ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ ጋር የሚመጣጠን ሲሆን የተጎዱ ባለድርሻ አካላትን፣ ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት* እና ባለሙያዎችን ማሳተፍ ያካትታል።

9.4.1 የጊዜያዊ ክትትል ፕሮግራም የሚከተሉትን ይገመግማል፡-

1) የስልቶች አፈፃፀም

2) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ሁኔታ እና የሚደገፉባቸዉ ቦታዎች ጨምሮ፤ እንዲሁም

3) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ እና/ወይም ለማጎልበት፣ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ የአስተዳደር ስልቶች እና እርምጃዎች ውጤታማነት

SLIMF 9.4.1.1 የጊዜያዊ ክትትል ፕሮግራም የሚከተሉትን ይገመግማል፡-

1) የስልቶች አፈፃፀም

2) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ሁኔታ እና የሚደገፉባቸዉ ቦታዎች ጨምሮ፤ እንዲሁም

3) ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ እና/ወይም ለማጎልበት፣ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ የአስተዳደር ስልቶች እና እርምጃዎች ውጤታማነት

9.4.2 የክትትል ፕሮግራሙ የተጎዱ የሙብት ባለቤቶችን፣ የተጎዱ እና ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎችን ያካትታል።

SLIMF 9.4.2.1 የክትትል ፕሮግራሙ የተጎዱ የሙብት ባለቤቶችን፣ የተጎዱ እና ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎችን ያካትታል።

9.4.3 ለእያንዳንዱ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ከመጀመሪያው ግምገማ እና ሁኔታ አንፃር የክትትል ፕሮግራሙ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለውጦች ለመለየት በቂ ስፋት፣ ዝርዝር እና ድግግሞሽ አለው

9.4.4 የአስተዳደር ስልቶች እና እርምጃዎች ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል በቂ አለመሆናቸውን የሚጠቁም ክትትል ወይም ሌሎች አዳዲስ መረጃዎች ሲገኙ ይስተካከላሉ።

***አረጋጋጮች፡-*** *የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፤ የክትትል ሂደቶች; የክትትል ሪፖርቶች; የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ* ሪፖርቶች፤ የመስክ ጉብኝቶች፣ ከባለድርሻ አካላት* የተደረጉ ቃለ መጠይቆች፤ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት መዝገብ።*

***መርህ* 10: የአስተዳደር ተግባራት አፈፃፀም***

**በድርጅቱ ወይም ለድርጅቱ ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች የሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት ከድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎችና ዓላማ ጋር የሚስማሙና በመመሪያዎቹና መመዘኛዎቹ ጋር በሚጣጣም መልኩ ይመረጣሉ እንዲሁም ይተገበራሉ።**

**10.1 ምርት ከተሰበሰበ በኋላ ወይም በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዱ መሠረት፤ ድርጅቱ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ዳግም ብቅለት ዘዴዎችን በመጠቀም የእጽዋት ሽፋኑን ምርቱ ከመሰብሰቡ በፊት ወደ ነበረበት ወይም የበለጠ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች በወቅቱ ዳግም ማብቀል አለበት።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

ከምርት መሰብሰብ በፊት* ያለው ሁኔታ ሠው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ ደን ሊሆን ይችላል። የደረጃ አዘጋጆች አመላካቾችን ሲያዘጋጁ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ያስገባሉ፡-

- ለነባር ሠው ሰራሽ የተሰበሰቡት ዝርያዎች ለመልሶ ማልማት ከሚጠቀሙት ጋር ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ ። ይሁን እንጂ ዝርያውን ለመቀየር የሚያስችሉ ጠንካራ ሥነ ምህዳራዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

የተመረጡት ዝርያዎች ከሥነ ምህዳራዊ ሁኔታ አንጻር ለቦታው ተስማሚ መሆን አለባቸው በተጨማሪም የአስተዳደር ዓላማዎች ከመስፈርት 10.2 ጋር መስማማት ይገባቸዋል።

◆ ለባዕድ ዝርያዎች ጥቅም ላይ መዋል በመስፈርት 10.2 ላይ ለነባር ዝርያዎች ምርጫ እና በመስፈርት 10.3 ላይ ለወራሪ ዝርያዎች ተጽዕኖዎች የቁጥጥር እና የመቀነስ እርምጃዎች የተገደበ ነው።

◆ ተፈጥሯዊ ደኖችን በተመለከተ ዳግም ብቅለት ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ ቀደም ሲል በተከናወኑ የምርት መሰብሰብ እና የደን ልማት ተግባራት/Siliviculture/ ወይም መሬቱ በተጎሳቆለበት ሁኔታ ውስጥ እንዲኖር ባደረጉ የተፈጥሮ ክስተቶች ምክንያት ከምርት መሰብሰብ በፊት* ባለው ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑን መወሰን ነው። ዓላማው* ከተሰበሰቡ በኋላ የተጎሳቆሉ ቦታዎችን ወደ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ማሻሻል መሆን አለበት።

◆ ተፈጥሯዊ ደኖችን በተመለከተ አንድ አስፈላጊ ዓላማ ለደን አስተዳደር የተለየ አጠቃላይ ቦታ ላይ በየዝርያዎች ያለ ብዛት/ Population/ እና የመጠን ክልል በአንጻራዊነት ተፈጥሯዊ የዝርያዎች ብዛት ማረጋገጥ ነው። ይህ የተፈጥሮ ልዩነት ክልል የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በመከተል ሊታይ ይችላል ምክንያቱም ደኖች በጊዜ ሂደት የማይለዋወጡ አይደሉም። ይህ አቀራረብ ድርጅቱ* በደንብ የተያዙ ደን ቦታዎች ውስጥም ጭምር በመላው ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ያለው የዝርያዎች ብዝሃነት* በተፈጥሮ ልዩነት ክልል ውስጥ እስከሚገኝ ድረስ ደን ቦታዎች ወይም የደን ምርት በሚሰበስብበት ቦታዎች ላይ የተወሰነ ተለዋዋጭነት እንዲኖረው ያስችለዋል፤ ይህ ደግሞ ነባር ዝርያዎች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የመሰደድ እድል እንዲኖራቸው ያደርጋል።

◆ ለዳግም ብቅለት የሚያስፈልገው ጊዜ ከሚተከሉት ቦታዎች (ሰው ሰራሽ ዳግም-ብቅለት) ለተፈጥሮ ዳግም-ብቅለት ከተመደቡ ወይም ከተመረጡ ቦታዎች አብዛኛውን ጊዜ ያነሰ ነው። ይሁን እንጂ ይህ መስፈርት የዳግም ብቅለትን ጊዜን ለማጥበብ የመትከል ዘዴን አይመርጥም ምክንያቱም በተወሰኑ ሁኔታዎች የተፈጥሮ ዳግም ብቅለት ዘዴዎች የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት ይበልጥ ተስማሚ ሲሆኑ በሌሎች ሁኔታዎች የመትከል ፕሮግራሞች የበለጠ ተስማሚ ናቸው።

◆ የዳግም ብቅለት ተግባራት መርህ 6 ላይ ያሉትን መስፈርቶች ሊጥሱ አይገባም። ከመስፈርት 6.9 እና 6.10 ጋር በሚስማማ መልኩ እነዚህ ተግባራት ወደ መለወጥ ሊያመሩ፣ ለደን አስተዳደር በተለዩ ቦታዎች ደረጃ የሚለካው የዘረመል እና የዝርያ ብዝሃነት መጥፋት ወይም ሌሎች የአካባቢ እሴቶችን ሊጎዱ አይችሉም።

10.1.1 ምርት የተሰበሰበባቸው ቦታዎች በወቅቱ እንደገና እንዲበቅሉ*:-

1) የተጎዱ የአካባቢያዊ እሴቶችን ይከላከላል* እና

2) አጠቃላይ የቅድመ ምርት* ወይም የተፈጥሮ የደን* ስብጥር/Composition/ እና መዋቅርን /Structure/ መልሶ ለማግኘት ተስማሚ ነው።

10.1.2 የዳግም ብቅለት ተግባራት የሚከናወኑት በሚከተሉት መልኩ ነው:-

1) ለነባር ሰው ሠራሽ ደኖች ምርት መሰብሰብ፣ ምርት ከመሰብሰቡ በፊት ወደነበረው የእፅዋት ሽፋን እንደገና ለማብቀል ወይም ከሥነ ምህዳር አንፃር በደንብ የተስማሙ ዝርያዎችን በመጠቀም ይበልጥ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ለመፍጠር

2) የተፈጥሮ ደኖችን ምርት ለመሰብሰብ፣ ምርት ከመሰብሰቡ በፊት ወደ ነበረበት እንደገና ማብቀል ወይም ወደ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ለመመለስ፣ ወይም

3) የተጎሳቆሉ የተፈጥሮ ደኖችን ለመሰብሰብ፣ ወደ ተሻለ ተፈጥሯዊ ሁኔታ እንደገና ማብቀል

NTFP 10.1.2.1 የ NTFPs በየዝርያዎች ያለ ብዛት ተፈጥሯዊ ስብጥር እና አወቃቀር እንዲቆዩ የሚደረጉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ (ለምሳሌ፡- ተፈጥሯዊ ዳግም ብቅለት አያያዝ፣ በተከላ ማበልፀግ፣ የዘር ዛፎች ምርጫ እና ጥበቃ) ፡፡

አረጋጋጮች፡- መልሰው የበቀሉ ቦታዎች እና ጥቅም ላይ የዋሉ ዝርያዎች መዝገብ፤ የተገኙ የአካባቢ እሴቶች፤ የመስክ ጉብኝቶች

10.2 ድርጅቱ* ለዳግም ብቅለት ከሥነ-ምህዳር አንጻር ቦታውን እና የአስተዳደር ዓላማዎችን* ለመጠበቅ ተስማሚ የሆኑ ዝርያዎችን ይጠቀማል። ድርጅቱ* ሌሎች ዝርያዎችን ለመጠቀም ግልጽና አሳማኝ ማስረጃ ካልተገኘ በስተቀር ነባር ዝርያዎች* እና አካባቢያዊ ዘረመል ለዳግም ብቀለት ይጠቀማል።

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***

አካባቢያዊ ያልሆኑ ነባር የዘረመል ዝርያዎችን መጠቀም ወይም ነባር ያልሆኑ ዝርያዎችን መጠቀም በብሔራዊ ደረጃ ከተስማሙ፣ የደረጃ አዘጋጆች አጠቃቀማቸውን ለመፍቀድ የሚያስችል ምክንያታዊነት ማዘጋጀት አለባቸው (አመልካች* 10.2.1) ፡፡

ይህ ምክንያት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡

- የአስተዳደር ዓላማዎችን የማያሟሉ የእድገት መጠኖች*
- ለአከባቢው ዝርያዎች ምርቶች አዋጭ ሳይሆን ሲቀር
- የነባር ዝርያዎች* እና/ወይም አካባቢያዊ ዘረመሎች* ሲጠፉ፣
- ነባር ዝርያዎች* እና/ወይም አካባቢያዊ ዘረመሎች* ለበሽታ እና ተባዮች መቋቋም የማይችሉ ሲሆኑ፣
- እንደ ውኃ ያሉ ለቦታው አጥረት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች፤
- የተጎሳቆሉ የእርሻ እና የግጦሽ መሬቶች ደን ማልማት፣
- የአየር ንብረት ለውጥ ጋር መላመድ፣ ወይም
- የካርቦን ክምችት አቅም

10.2.1 ለዳግም ብቅለት የተመረጡት ዝርያዎች ከሥነ ምህዳራዊ ሁኔታ አንጻር ለቦታው በደንብ የተስማሙ፣ የነባር ዝርያዎችና የአካባቢያዊ ዝርያዎች ሲሆኑ፣ የአካባቢያዊ ያልሆኑ ዘረመሎች እና ነባር ያልሆኑ ዝርያዎችን ለመጠቀም ግልጽና አሳማኝ ማስረጃ ካልተሰጠ በስተቀር

NTFP 10.2.1.1 ለዳግም ብቅለት የተመረጡት የ NTFP ዝርያዎች ከሥነ ምህዳራዊ ሁኔታ አንጻር ለቦታው በደንብ የተስማሙ፣ የነባር ዝርያዎችና የአካባቢያዊ ዝርያዎች ሲሆኑ፣ የአካባቢያዊ ያልሆኑ ዘረመሎች እና ነባር ያልሆኑ ዝርያዎችን ለመጠቀም ግልጽና አሳማኝ ማስረጃ ካልተሰጠ በስተቀር

10.2.2 ለዳግም ብቅለት የተመረጡት ዝርያዎች ከመልሶ ማልማት ዓላማዎች* እና ከአስተዳደር ዓላማዎች* ጋር የሚስማሙ ናቸው።

***አረጋጋጮች***: - ዝርያዎችን የመምረጥ ምክንያት፣ የተጠቀሙባቸው ዝርያዎች መዝገብ፣ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ* እና የመስክ ጉብኝቶች

10.3 ድርጅቱ ባዕድ ዝርያዎችን የሚጠቀመው ማንኛውም ወራሪ ተፅዕኖ መቆጣጠር እንደሚቻልና ውጤታማ የመቀነስ እርምጃዎች መወሰድ እንደሚችሉ ዕውቀትና/ወይም ልምድ ሲያሳይ ብቻ ነው።

10.3.1 የባዕድ ዝርያዎች ጥቅም ላይ የሚውሉት ቀጥተኛ ተሞክሮ እና/ወይም የሳይንሳዊ ምርምር ውጤቶች ወራሪ ተፅዕኖዎችን መቆጣጠር እንደሚቻል ሲያሳዩ ብቻ ነው።

NTFP 10.3.1.1 NTFPs የባዕድ ዝርያዎች ሲሆኑ ጥቅም ላይ የሚውሉት ቀጥተኛ ተሞክሮ እና/ወይም የሳይንሳዊ ምርምር ውጤቶች ወራሪ ተፅዕኖዎችን መቆጣጠር እንደሚቻል ሲያሳዩ ብቻ ነው።

10.3.2 ባዕድ ዝርያዎች ጥቅም ላይ የሚውሉት ከተቋቋሙበት አካባቢ ውጭ ስርጭታቸውን ለመቆጣጠር ውጤታማ የመቀነስ እርምጃዎች ሲኖሩ ብቻ ነው።

NTFP 10.3.2.1 NTFPs ባዕድ ዝርያዎች ሲሆኑ ጥቅም ላይ የሚውሉት ከተቋቋሙበት አካባቢ ውጭ ስርጭታቸውን ለመቆጣጠር ውጤታማ የመቀነስ እርምጃዎች ሲኖሩ ብቻ ነው።

10.3.3 ድርጅቱ* ያስገባቸውን ወራሪ ዝርያዎች* ስርጭት ይቆጣጠራል።

NTFP 10.3.3.1 ድርጅቱ* ያስገባቸውን ባዕድ ወራሪ የNTFPs ዝርያዎች* ስርጭት ይቆጣጠራል።

10.3.4 በድርጅቱ ባልተተዋወቁ ባዕድ ዝርያዎች ወረራ ተፅዕኖዎችን ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ የአስተዳደር ተግባራት በተቻለ መጠን ከተለያዩ የቁጥጥር አካላት ጋር በመተባበር ይከናወናሉ።

NTFP 10.3.4.1 በድርጅቱ ባልተተዋወቁ ባዕድ የNTFPs ዝርያዎች ወረራ ተፅዕኖዎችን ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ የአስተዳደር ተግባራት በተቻለ መጠን ከተለያዩ የቁጥጥር አካላት ጋር በመተባበር ይከናወናሉ።

**አረጋጋጮች**: የምርምር ሪፖርቶች፤ የዝርያ ማስገባት ፍቃዶች፤ የእጽዋት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች፤ የመቀነስ እርምጃዎች፤ ስለ ዝርያው የሚገልፅ መዝገብ፤ ዝርያዎቹ የተመረጡበት ምክንያት፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ ምልልሶች፤ የመስክ ጉብኝቶች፤ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ፤ የባዕድ ዝርያዎችን ስርጭት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የተቀመጡ የመቀነሻ እርምጃዎች

10.4 ድርጅቱ ለደን አስትዳደር በተለዩ ቦታዎች ውስጥ በዘረመል መንገድ የተሻሻሉ ተህዋሲያንን አይጠቀምም።

10.4.1 በዘረመል መንገድ የተሻሻሉ ተህዋሲያንን አይጠቀሙም።

NTFP 10.4.1.1 በዘረመል መንገድ የተሻሻሉ የNTFPs ተህዋሲያንን አይጠቀሙም።

**አረጋጋጮች**: - የተጠቀሙባቸው ዝርያዎች መዝገብ፤ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ

10.5 ድርጅቱ ለእፅዋት፣ ዝርያዎች፣ ቦታዎች እና አስተዳደር ዓላማዎች ሥነ ምህዳራዊ ተስማሚ የሆኑ የደን ልማት/Siliviculture/ ልምዶችን ይጠቀማል።

10.5.1 ከሥነ ምህዳራዊ እይታ አንጻር ለእፅዋት፣ ዝርያዎች፣ ቦታዎች እና አስተዳደር ዓላማዎች ተስማሚ የሆኑ የደን ልማት/Siliviculture/ ልማዶች ይተገበራሉ።

NTFP 10.5.1.1 ከሥነ ምህዳራዊ እይታ አንጻር ለእፅዋት፣ ዝርያዎች፣ ቦታዎች እና NTFP አስተዳደር ዓላማዎች ተስማሚ የሆኑ የደን ልማት/Siliviculture/ ልማዶች ይተገበራሉ።

**አረጋጋጮች**: - የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ፣ የመስክ ጉብኝቶች

10.6 ድርጅቱ የማዳበሪያዎችን አጠቃቀም በትንሹ ይቀንሳል ወይም ያስወግዳል። ማዳበሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ድርጅቱ ማዳበሪያዎችን የማይጠይቁ የደን ልማት ስርዓቶችን /Silivicultural system/ ከመጠቀም እኩል ወይም የበለጠ ሥነ ምህዳራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዳለው እና የአካባቢ እሴቶችን አፈረን ጨምሮ መከላከል ማቃለል እና/ወይም ማረም መቻሉን ያሳያል።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**:

የደረጃ አዘጋጆች ማዳበሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ በብርቅዬ ማህበረ-እፅዋት ሰቦች፣ በወንዞች ዳርቻ ዞኖች፣ በውሃ ፍሰቶች እና በውሃ አካላት ዙሪያ ማዳበሪያዎችን መጠቀምን የሚከለክሉ የመከላከያ ዞኖች/Buffer Zones/ በብሔራዊ ደረጃዎች እና በጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ውስጥ እንዲካተቱ የሚያረጋግጡ አመልካቾችን ያዘጋጃሉ (አመልካች * 10.6.4) ።

10.6.1 የማዳበሪያዎችን በትንሹ መጠቀም ወይም ከነጭራሹ አለመጠቀም።

NTFP 10.6.1.1 NTFPs ለማምረት ማዳበሪያዎችን በትንሹ መጠቀም ወይም ከነጭራሹ አለመጠቀም።

10.6.2 ማዳበሪያዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚገኘው ሥነ ምህዳራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማዳበሪያ የማያስፈልጋቸው የደን ልማት ሥርዓቶች ከሚያስገኙት ጥቅም ጋር እኩል ወይም ከዚያ በላይ ነው።

NTFP 10.6.2.1 ማዳበሪያዎች NTFPs ለማምረት ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚገኘው ሥነ ምህዳራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማዳበሪያ የማያስፈልጋቸው የደን ልማት ሥርዓቶች ከሚያስገኙት ጥቅም ጋር እኩል ወይም ከዚያ በላይ ነው።

10.6.3 ማዳበሪያዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ዓይነቶቻቸው፣ መጠኖቻቸው፣ ድግግሞሾቻቸው እና የመተግበሪያ ቦታቸው በሰነድ ይመዘገባሉ።

NTFP 10.6.3.1 ማዳበሪያዎች NTFPs ለማምረት ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ ዓይነቶቻቸው፣ መጠኖቻቸው፣ ድግግሞሾቻቸው እና የመተግበሪያ ቦታቸው በሰነድ ይመዘገባሉ።

10.6.4 ማዳበሪያዎችን ሲጠቀሙ የአካባቢ ጥበቃ እሴቶች ይጠበቃሉ፣ ይህም ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚረዱ እርምጃዎችን በመተግበርም ጭምር ነው።

NTFP 10.6.4.1 ማዳበሪያዎችን NTFPs ለማምረት ሲጠቀሙ የአካባቢ ጥበቃ እሴቶች ይጠበቃሉ፣ ይህም ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚረዱ እርምጃዎችን በመተግበርም ጭምር ነው።

10.6.5 በማዳበሪያ አጠቃቀም የተከሰተው የአካባቢ ጉዳት ይቀንሳል ወይም ይስተካከላል።

NTFP 10.6.5.1 ለNTFPs ማምረት በማዳበሪያ አጠቃቀም የተከሰተው የአካባቢ ጉዳት ይቀንሳል ወይም ይስተካከላል።

***አረጋጋጮች***: - ማዳበሪያን ለመጠቀም ምክንያታዊነት*፤ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ፤ የማዳበሪያ አጠቃቀም እና ድግግሞሽ መዝገብ*፤ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እና የተወሰዱ የመቀነስ እርምጃዎች መዝገብ ፣

10.7 ድርጅቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል መድኃኒቶችን መጠቀምን የሚከለክሉ ወይም ብሎም ለማስወገድ የተቀናጀ የፀረ ተባይ መከላከያ/Integrated Pest Managment/ እና የደን ልማት ስርዓቶችን ይጠቀማል። ድርጅቱ በ FSC ፖሊሲ የተከለከሉ ፀረ ተባይ ኬሚካል መድኃኒቶችን አይጠቀምም። ፀረ ተባይ መድኃኒቶች ጥቅም ላይ ሲውሉ ድርጅቱ ለአካባቢያዊ እሴቶች እና ለሰው ጤና የሚደርሰውን ጉዳት መከላከል፣ መቀነስ እና/ወይም መጠገን አለበት።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**:

የደረጃ አዘጋጆች በFSC-የተረጋገጡ ደኖች እና ሰው ሠራሽ ደን ተከላዎች ውስጥ የተቀናጀ የፀረ ተባዮች ፣ በሽታዎች እና አረም አያያዝ የ FSC መመሪያ (2009) እና ተጓዳኝ ፖሊሲዎችን ፣ መመሪያዎችን ፣ የምክር ማስታወሻዎችን እና ሌሎች የ FSC ደንብ ሰነዶችን አመልካቾችን ለማዘጋጀት ማካተት አለባቸው (አመልካች 10.7.1).

የደረጃ አዘጋጆች የ ILO ሰነድ “በሥራ ቦታ ኬሚካሎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ደህንነት” (ጄኔቫ፣ ILO፣ 1993) ወይም የዚህ ሰነድ ማንኛውም ብሔራዊ ትርጓሜ በሀገር አቀፍ ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ውስጥ የሚያመለክቱትን ወይም የሚያካትቱትን አግባብነት ያላቸውን ገጽታዎች ያካትታሉ (መለያ *10.7.4) ።

10.7.1 የፀረ ተባይ ኬሚካል መድኃኒቶችን አጠቃቀምን ድግግሞሽ፣ መጠን እና ብዛት ለማስወገድ ወይም ብሎም ለማጥፋት የደን ልማት ሥርዓቶችን መምረጥ ጨምሮ የተቀናጀ የፀረ ተባይ አያያዝ ጥቅም ላይ ይውላል፣ ይህም አጠቃቀምን ለመተው ወይም አጠቃላዩን መቀነስ ውጤት ያስከትላል።

NTFP 10.7.1.1 NTFPs በሚመረቱበት ጊዜ የፀረ ተባይ ኬሚካል መድኃኒቶችን አጠቃቀምን ድግግሞሽ፣ መጠን እና ብዛት ለማስወገድ ወይም ብሎም ለማጥፋት የደን ልማት ሥርዓቶችን መምረጥ ጨምሮ የተቀናጀ የፀረ ተባይ አያያዝ ጥቅም ላይ ይውላል፣ ይህም አጠቃቀምን ለመተው ወይም አጠቃላዩን መቀነስ ውጤት ያስከትላል።

10.7.2 በ FSC የፀረ ተባይ መድኃኒቶች ፖሊሲ የተከለከሉ ፀረ ተባይ ኬሚካላዊ መድኃኒቶች በ FSC ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ጥቅም ላይ አይውሉም ወይም አይከማቹም።

NTFP 10.7.2.1 የንብ በሽታ በአካላዊ/Physically/ መንገድ ለምሳሌ በእንፋሎት ወይም በእሳት ተይዞ የንብ ቀፎዎችን በማጠን ተባዮችን በማጥፋት ማከም። ቫሮአ ማይትስን /varroa mites/ ለማጥፋት የሚከተሉት ንጥረ ነገሮች ጥቅም ላይ ይውላሉ;

-

- ፎርሚክ አሲድ / formic acid/፣ ላክቲክ አሲድ / lactic acid/ ፣ አሲቲክ አሲድ / acetic acid / እና ኦክሳሊክ አሲድ / oxalic acid/

- ሜንቶል / menthol/ ዩካሊፕቶል / eucalyptol / እና ካምፎር / camphor/

10.7.3 የፀረ-ተባይ መድኃኒት አጠቃቀም መዝገብ መያዝ አለበት፣ የንግድ ስም፣ ዋና ንጥረ ነገር፣ የተጠቀመበት ዋና ንጥረ ነገር ብዛት፣ የአጠቃቀም ጊዜ፣ የአጠቃቀም ቦታና አካባቢ እንዲሁም የአጠቃቀም ምክንያት።

NTFP 10.7.3.1 NTFPs በሚመረቱበት ጊዜ የፀረ-ተባይ መድኃኒት አጠቃቀም መዝገብ መያዝ አለበት፣ የንግድ ስም፣ ዋና ንጥረ ነገር፣ የተጠቀመበት ዋና ንጥረ ነገር ብዛት፣ የአጠቃቀም ጊዜ፣ የአጠቃቀም ቦታና አካባቢ እንዲሁም የአጠቃቀም ምክንያት።

10.7.4 የፀረ-ተባይ መድኃኒቶች አጠቃቀም በአጋጣሚ በሚፈስሱ ኬሚካሎች ላይ ለትራንስፖርት ፣ ለማከማቸት ፣ ለማስተናገድ ፣ ለመተግበር እና ለአደጋ ጊዜ የጽዳት ሂደቶች መስፈርቶችን በተመለከተ የ ILO ሰነድ "በሥራ ላይ ኬሚካሎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ደህንነት" ያሚላል።

10.7.5 ፀረ ተባይ መድኃኒቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ የመተግበሪያ ዘዴዎች ውጤታማ ውጤቶችን በማምጣት ጥቅም ላይ የዋሉትን መጠኖች ወደ ዝቅተኛ ይቀንሳሉ እንዲሁም በአከባቢው ላሉት የመሬት ገጽታዎች ውጤታማ ጥበቃ ይሰጣሉ።

NTFP 10.7.5.1 ፀረ ተባይ መድኃኒቶች* በ NTFPs ምርት ማምረት ውስጥ ጥቅም ላይ ሲውሉ የመተግበሪያ ዘዴዎች ውጤታማ ውጤቶችን በማምጣት ጥቅም ላይ የዋሉትን መጠኖች ወደ ዝቅተኛ ይቀንሳሉ እንዲሁም በአከባቢው ላሉት የመሬት ገጽታዎች ውጤታማ ጥበቃ ይሰጣሉ።

NTFP 10.7.5.2 NTFPs በሚመረቱበት ጊዜ የፀረ-ተባይ መድኃኒቶች አጠቃቀም በአጋጣሚ በሚፈስሱ ኬሚካሎች ላይ ለትራንስፖርት ፣ ለማከማቸት ፣ ለማስተናገድ ፣ ለመተግበር እና ለአደጋ ጊዜ የጽዳት ሂደቶች መስፈርቶችን በተመለከተ የ ILO ሰነድ "በሥራ ላይ ኬሚካሎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ደህንነት" ያሚላሉ።

10.7.6 በአካባቢያዊ እሴቶች እና በሰው ጤና ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፀረ-ተባይ መድኃኒቶች አጠቃቀም ከሆነ ጉዳት በሚከሰትበት ጊዜ ይከላከላል እና ይቀንሳል ወይም ይጠግናል።

NTFP 10.7.6.1 NTFPs በሚመረቱበት ጊዜ በአካባቢያዊ እሴቶች እና በሰው ጤና ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፀረ-ተባይ መድኃኒቶች አጠቃቀም ከሆነ ጉዳት በሚከሰትበት ጊዜ ይከላከላል እና ይቀንሳል ወይም ይጠግናል።

10.7.7 የፀረ ተባይ መድኃኒቶች* ሲጠቀሙ፡-

1) የተመረጠው ፀረ ተባይ መድኃኒት፣ የመተግበሪያ ዘዴ፣ የአጠቃቀም ጊዜና ንድፍ ለሰው እና ዒላማ ላልሆኑ ዝርያዎች አነስተኛ አደጋ ያስከትላል፣ እና
2) ተጨባጭ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ፀረ ተባይ መድኃኒቱ* ብቸኛው ውጤታማ፣ ተግባራዊና ወጪ ቆጣቢ የሆነ ተባይ መቆጣጠሪያ መንገድ ነው።

NTFP 10.7.7.1 1 NTFPs በሚመረቱበት ጊዜ የፀረ ተባይ መድኃኒቶች* ሲጠቀሙ፡-

1) የተመረጠው ፀረ ተባይ መድኃኒት፣ የመተግበሪያ ዘዴ፣ የአጠቃቀም ጊዜና ንድፍ ለሰው እና ዒላማ ላልሆኑ ዝርያዎች አነስተኛ አደጋ ያስከትላል፣ እና
2) ተጨባጭ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ፀረ ተባይ መድኃኒቱ* ብቸኛው ውጤታማ፣ ተግባራዊና ወጪ ቆጣቢ የሆነ ተባይ መቆጣጠሪያ መንገድ ነው።

***አረጋጋጮች*፡-** የተጠቀሙበት የተቀናጀ የፀረ-ተባይ መቆጣጠሪያ ስርዓት፤ የተጠቀሙት ፀረ ተባይ የኬሚካል መድኃኒቶች ዋና ንጥረ-ነገሮች ዓይነት፤ የተጠቀሙበት ፀረ ተባይ መድኃኒቶች መዝገብ፤ የመስክ ጉብኝቶች፤ ከሰራተኞችና ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቆች፤ ጥቅም ላይ የዋሉ የደህንነት ዘዴዎች፤ የፀረ ተባይ መድኃኒቶች አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች*፤ የኬሚካል አጠቃቀም ሂደቶች፤ የኬሚካል አጠቃቀም መዝገቦች፤ ፀረ ተባይ መድኃኒት መምረጥ ምክንያታዊነት*

10. 8 ድርጅቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባላቸው ሳይንሳዊ ፕሮቶኮሎች መሠረት የስነ ሕይወት መቆጣጠሪያዎችን አጠቃቀም ይቀንሳል፣ ይከታተላል እንዲሁም በጥብቅ ይቆጣጠራል። ሥነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ድርጅቱ ለአካባቢያዊ እሴቶች የሚደርሰውን ጉዳት መከላከል፣ ማቃለል እና/ወይም መጠገን አለበት።

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

የደረጃ አዘጋጆች ከሥነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎች ጋር የተያያዙ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ሳይንሳዊ ፕሮቶኮሎች፣ የFAO የሥነ ምግባር ደንብ ኮድ ለመጤ ስነ ሕይወታዊ መቆጣጠሪያ ማስመጣትና መልቀቅ እና እነዚህ ካሉ ማናቸውንም ብሔራዊ ደንቦች የሚመለከቱ ወይም የሚያካትቱት ናቸው (አመልካች* 10.8.2)።

10.8.1 የስነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎች አጠቃቀም ይቀነሳል፣ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል።

NTFP 10.8.1.1 NTFPs በሚመረቱበት ጊዜ የስነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎች አጠቃቀም ይቀነሳል፣ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል።

10.8.2 የስነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎችን መጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን ሳይንሳዊ ፕሮቶኮሎች ያሟላል።

NTFP 10.8.2.1 በ NTFPs ምርት ማምረት ውስጥ የስነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎችን መጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን ሳይንሳዊ ፕሮቶኮሎች ያሟላል።

10.8.3 የስነ ሕይወታዊ መቆጣጠሪያ አድራጊዎች አጠቃቀም፣ ዓይነት፣ ብዛት፣ ጊዜ፣ ቦታ እና የአጠቃቀም ምክንያት ጨምሮ ይመዘገባል።

NTFP 10.8.3.1 በ NTFPs ምርት ማምረት ውስጥ የስነ ሕይወታዊ መቆጣጠሪያ አድራጊዎች አጠቃቀም፣ ዓይነት፣ ብዛት፣ ጊዜ፣ ቦታ እና የአጠቃቀም ምክንያት ጨምሮ ይመዘገባል።

10.8.4 በአካባቢያዊ እሴቶች የሚደርሰው ጉዳት ከስነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎች አጠቃቀም ከሆነ ጉዳት በሚከሰትበት ጊዜ ይከላከላል እና ይቀንሳል ወይም ይጠግናል።

NTFP 10.8.4.1 በ NTFPs ምርት ማምረት ውስጥ በአካባቢያዊ እሴቶች የሚደርሰው ጉዳት ከስነ ሕይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎች አጠቃቀም ከሆነ ጉዳት በሚከሰትበት ጊዜ ይከላከላል እና ይቀንሳል ወይም ይጠግናል።

***አረጋጋጮች***፦ የመስክ ጉብኝቶች፣ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፣ ከሠራተኞች ጋር የተደረጉ ቃለምልልሶች*፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ቃለምልልሶች፤ የአጠቃቀም መዝገብ፤ የመከላከልና የመቀነስ እርምጃዎች

**10.9 ድርጅቱ አደጋዎችን ይገመግማል እንዲሁም ከተፈጥሮ አደጋዎች ሊመጡ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የሚረዱ ተግባራትን በመጠን፣ በጥንካሬ እና በስጋት ላይ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ይተገብራል።**

**ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ**

የደረጃ አዘጋጆች በክልል እና በብሔራዊ ደረጃ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎችን ድግግሞሽ፣ ስርጭት እና ከባድነት መለየት አለባቸው (አመላካች* 10.9.1)።

በተጨማሪም የደረጃ አዘጋጆች በአስተዳደር ተግባራት ሊጨመሩ የሚችሉትን አደጋዎች (አመላካች* 10.9.3) እና የተጨመረው አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ መንገዶችን (አመላካች* 10.9.4) መለየት አለባቸው።

የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ነፋስ እና እሳት ያሉ የተፈጥሮ ዑደትን የሚያዛቡ ክስተቶችን እንደሚያካትቱ በመገንዘብ የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመቆጣጠር ወይም ለመከላከል ከመሞከር ይልቅ የተፈጥሮ አደጋዎች ተፅእኖን መቋቋምን ማረጋገጥ ላይ ማተኮር አለበት (አመላካች* 10.9.2 እና 10.9.4 )።

10.9.1 የተፈጥሮ አደጋዎች በመሠረተ ልማት፣ በደን ሀብቶች እና ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ የሚገኙ ማህበረሰቦች ላይ ያስከትሉ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ይገመገማሉ።

SLIMF 10.9.1.1 የተፈጥሮ አደጋዎች በመሠረተ ልማት፣ በደን ሀብቶች እና ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ የሚገኙ ማህበረሰቦች ላይ ያስከትሉ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ይገመገማሉ።

10.9.2 የአስተዳደር ተግባራት እነዚህን ተጽዕኖዎች ይቀንሳሉ ።

NTFP 10.9.2.1 የአስተዳደር ተግባራት የተፈጥሮ አደጋዎች በ NTFPs ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተጽዕኖ ይቀንሳሉ።

SLIMF 10.9.2.1 አቅም እና ሀብቶች በሚፈቅዱበት ጊዜ የአስተዳደር ተግባራት ተቀባይነት የሌላቸውን የተፈጥሮ አደጋዎች አሉታዊ ተፅእኖዎች ይቀንሳሉ። አቅም ወይም ሀብት የማይፈቅድ ከሆነ ድርጅቱ ወይም ሥራ አስኪያጁ ስለ ቅነሳ አቅም እና አማራጮች ከመንግስት ወይም ከሚመለከታቸው አካባቢያዊ ድርጅቶች ጋር ይነጋገራሉ።

10.9.3 የአስተዳደር ተግባራት የተፈጥሮ አደጋዎችን ድግግሞሽ፣ ስርጭት ወይም ከባድነት የመጨመር አደጋ በአስተዳደር ተፅዕኖ ሊደረግባቸው የሚችሉ አደጋዎች ተለይቷል።

SLIMF 10.9.3.1 የአስተዳደር ተግባራት የተፈጥሮ አደጋዎችን ድግግሞሽ፣ ስርጭት ወይም ከባድነት የመጨመር አደጋ በአስተዳደር ተፅዕኖ ሊደረግባቸው የሚችሉ አደጋዎች ተለይቷል።

10.9.4 የአስተዳደር ተግባራት ተለውጠዋል እና/ወይም የተለዩትን አደጋዎች የሚቀንሱ እርምጃዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ተደርገዋል።

SLIMF 10.9.4.1 የአስተዳደር ተግባራት ተለውጠዋል እና/ወይም የተለዩትን አደጋዎች የሚቀንሱ እርምጃዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ተደርገዋል።

***አረጋጋጮች:-*** *የተፈጥሮ አደጋ* ግምገማ ሪፖርቶች፤ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፤ የተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች* መዝገብ፤ ከሠራተኞች* እና ከባለድርሻ አካላት* ጋር የተደረጉ ቃለምልልሶች፤ ስጋቶችን ለመቀነስ የመቀነሻ እርምጃዎች፤ ሥራ አስኪያጁ ስለ ቅነሳ አቅም እና አማራጮች ከመንግስት ወይም ከሚመለከታቸው አካባቢያዊ ድርጅቶች ጋር የተደረጉ ግንኙነቶች ሰነድ*

**10.10 ድርጅቱ *የመሠረተ-ልማት ልማትን፣ የትራንስፖርት እንቅስቃሴዎችን እና የደን ልማት ሥራዎችን የሚተገበረው የውሃ ሀብቶች እና አፈር እንዲጠበቁ እንዲሁም ብርቅዬና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን፣ የመኖሪያ ቦታዎችን፣ ሥርዓተ ምህዳሮችን እና የመሬት ገጽታ እሴቶችን ተፈጥሮዓዊ ሂደቶችን የሚያውክ እና የሚጎዳ መከላከል፣ መቀነስ እና/ወይም መጠገን እንዲቻል ነው።***

10.10.1 የመሠረተ-ልማት ልማት፣ ጥገና እና አጠቃቀም እንዲሁም የትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች በ6.1 መስፈርት የተገለጹትን የአካባቢያዊ እሴቶች ለመጠበቅ የሚተገበሩ ናቸው።

NTFP 10.10.1.1 የመሠረተ-ልማት ልማት፣ ጥገና እና አጠቃቀም እንዲሁም የትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች በ6.1 መስፈርት የተገለጹትን የአካባቢያዊ እሴቶች እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ለመጠበቅ የሚተገበሩ ናቸው።

10.10.2 የደን ልማት/Siliviculture/ ተግባራት የሚተዳደሩት በ6.1 መስፈርት የተገለጹትን የአካባቢያዊ እሴቶች ጥበቃ ለማረጋገጥ ነው።

NTFP 10.10.2.1 ከNTFPs የተገናኙ የደን ልማት/Siliviculture/ ተግባራት የሚተዳደሩት በ6.1 መስፈርት የተገለጹትን የአካባቢያዊ እሴቶች ጥበቃ ለማረጋገጥ ነው።

10.10.3 የውሃ ፍሰቶች፣ የውሃ አካላት፣ አፈር፣ ብርቅዬና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች፣ የመኖሪያ ቦታዎች፣ ሥርዓተ ምህዳሮች እና የመሬት ገጽታ እሴቶች ላይ የሚደርሰው የተፈጥሮ ዑደት መረበሽ ወይም ጉዳት በወቅቱ መከላከል፣ መቀነስ እና መጠገን እንዲሁም ተጨማሪ ጉዳትን ለመከላከል የአስተዳደር ተግባራት መለወጥ አለባቸው።

NTFP 10.10.3.1 የውሃ ፍሰቶች፣ የውሃ አካላት፣ አፈር፣ ብርቅዬና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች፣ የመኖሪያ ቦታዎች፣ ሥርዓተ ምህዳሮች እና የመሬት ገጽታ እሴቶች ላይ የሚደርሰው የተፈጥሮ ዑደት መረበሽ ወይም ጉዳት በወቅቱ መከላከል፣ መቀነስ እና መጠገን እንዲሁም ተጨማሪ ጉዳትን ለመከላከል የNTFPs አስተዳደር ተግባራት መለወጥ አለባቸው።

***አረጋጋጮች***: የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፤ የመሠረተ-ልማት* ልማት እና ጥገና ሂደቶች፤ የደን ልማት/Siliviculture/ አስተዳደር ክንውን *መመሪያ*

**10.11 ድርጅቱ ከእንጨት እና ከእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች መሰብሰብ እና ማውጣት ጋር የተያያዙ ተግባራትን የሚቆጣጠረው የአካባቢ ጥበቃ እሴቶች እንዲጠበቁ፣ ለገበያ የሚውል ተረፈ-ምርት እንዲቀንስ እና ለሌሎች ምርቶች እና አገልግሎቶች ጉዳት እንዳይደርስ ነው።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ***:

የደረጃ አዘጋጆች በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩ ከሆነ የእነዚህን ሰነዶች አግባብነት ያላቸውን ገጽታዎች ማመልከት ወይም ማካተት አለባቸው (አመልካቾች* 10.11.1 እና 10.11.4)።

- የFAO ሞዴል የደን ምርት አሰባሰብ አጠቃቀም ደንብ፣
- የደን መቁረጥና ማጓጓዝ ተፅዕኖ መቀነስ መዝገብ

የተመረጠ የደን መቁረጥና ማጓጓዝ ለመከላከል የደረጃ አዘጋጆች አመላካቾችን* ያዘጋጃሉ* (አመልካች* 10.11.2)

10.11.1 የእንጨት እና የእንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች የመሰብሰብ እና የማውጣት ልምዶች በመስፈርት 6.1 የተለዩትን የአካባቢያዊ እሴቶችን እና በመስፈርት 9.1 እና 9.2 የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን በሚጠብቅ መንገድ ይተገበራሉ።

NTFP 10.11.1.1 የ NTFPs የመሰብሰብ እና የማውጣት ልምዶች በመስፈርት 6.1 የተለዩትን የአካባቢያዊ እሴቶችን እና በመስፈርት 9.1 እና 9.2 የተለዩትን ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን በሚጠብቅ መንገድ ይተገበራሉ።

10.11.2 የመሰብሰብ ተግባራት የደን ምርቶችን እና ለገበያ የሚውሉ ቁሳቁሶችን አጠቃቀምን ያመቻቻሉ/ያሳድጋሉ።

NTFP 10.11.2.1 የመሰብሰብ ተግባራት የNTFPs ምርቶችን እና ለገበያ የሚውሉ ቁሳቁሶችን አጠቃቀምን ያመቻቻሉ/ያሳድጋሉ።

10.11.3 በቂ መጠን ያለው የሞተ እና የሚበሰብስ ባዮማስ/Biomass/ እና የደን መዋቅር የአካባቢ እሴቶችን ለመጠበቅ ይቀመጣል።

10.11.4 የመሰብሰብ ተግባራት በቆሙ ቀሪ ዛፎች፣ መሬት ላይ የሚገኘውን የእንጨት ቁርጥራጭ/Debris/ እና ሌሎች የአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ያስወግዳሉ.

NTFP 10.11.4.1 የNTFPs የመሰብሰብ ተግባራት በቆሙ ቀሪ ዛፎች፣ መሬት ላይ የሚገኘውን የእንጨት ቁርጥራጭ/Debris/ እና ሌሎች የአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ያስወግዳሉ.

***አረጋጋጮች:-*** የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ*፤ የምርት አሰባሰብ አሰራሮች፣ የመስክ ጉብኝቶች፣ ከሠራተኞች ጋር የተደረጉ ቃለ መጠይቆች፤ ምርት የተሰበበት መዝገብ

**10. 12 ድርጅቱ የቆሻሻ ቁሳቁሶችን በአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ያስወግዳል።**

***ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ:***

የደረጃ አዘጋጆቹ የቆሻሻ ቁሳቁሶችን በአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ለማስወገድ የሚረዱ ብሔራዊ ደንቦችን ያመለክታሉ ወይም ብሔራዊ ደንቦች በቂ ካልሆኑ ወይም ከሌሉ ተጨማሪ አመልካቾችን ያዘጋጃሉ።

10.12.1 ሁሉም የቆሻሻ ቁሳቁሶች መሰብሰብ፣ ማጽዳት፣ ማጓጓዝ እና ማስወገድ የሚከናወነው በአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ሲሆን ይህም በ6.1 መስፈርት ውስጥ የተገለጹትን የአካባቢያዊ እሴቶች ይጠብቃል።

NTFP 10.12.1.1 በNTFPs ጊዜ ሁሉም የቆሻሻ ቁሳቁሶች መሰብሰብ፣ ማጽዳት፣ ማጓጓዝ እና ማስወገድ የሚከናወነው በአካባቢ ተስማሚ በሆነ መንገድ ሲሆን ይህም በ6.1 መስፈርት ውስጥ የተገለጹትን የአካባቢያዊ እሴቶች መጠበቃቸውን ያረጋግጣል።

***አረጋጋጮች:-*** የቆሻሻ መሰብሰቢያ መዝገቦች፤ የቆሻሻ አያያዝ አሰራር፤ የመስክ ጉብኝት፤ ከሠራተኞች* እና ከባለድርሻ አካላት* ጋር የተደረጉ ቃለምልልሶች

## ሸ. አባሪዎች

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

በFSC-STD-60-004 ዓለምአቀፍ አጠቃላይ አመላካቾች ክፍል 5 ለደረጃ አዘጋጆች የሚሆኑ ዘጠኙን አባሪዎች መመሪያዎች ደረጃውን እንዲያሟሉ የሚረዱ ልዩ መስፈርቶች ይዟል።

አስገዳጅ ሁኔታቸው በእያንዳንዱ አባሪ መጀመሪያ ላይ ይንጸባረቃል እና በሚከተለው ሠንጠረዥ የተጠቃለለ እና በ ISO 'የፍሬ ነገር መግለጫ ድንጋጌዎች ማለትም 'ይሆናል' ወዘተ. የተገለፀ (ከFSC-STD-60-004 V2-0 EN የተወሰደ)።

| አባሪ ሞዴል | ርዕስ | ለደረጃ አዘጋጆች የትግበራ መመሪያ |
|---|---|---|
| አባሪ ሀ | ቢያንስ ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የያዘ ዝርዝር (መርህ 1) | ደረጃ አዘጋጆች በአገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች፣ አስገዳጅ የአሰራር ደንቦች እና ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶችን እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በንዑስ ብሄራዊ ደረጃ በአባሪ ሀ ላይ የተዘረዘሩትን ያጠናቅቃሉ። ይህ ዝርዝር በብሔራዊ ደረጃ ወይም በጊዜያዊ ብሄራዊ ደረጃዎች መካተት አለበት። |
| አባሪ ለ | ለሠራተኞች የሥልጠና መስፈርቶች (መርህ 2) | የደረጃ አዘጋጆች የብሔራዊ ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ውስጥ የስልጠና መስፈርቶች ከመጠን፣ ከጥንካሬ እና ከአደጋ ጋር በማመጣጠን እና አሁን ካሉ ብሔራዊ እና በክልል ካሉ የስልጠና መስፈርቶች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።ደረጃ አዘጋጆችም የዚህን አባሪ አስፈላጊ ክፍሎች በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም በጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ውስጥ ባሉ አመልካቾች ውስጥ ማካተት ይችላሉ |
| አባሪ ሐ | የጥበቃ ቦታዎች መረብ ጽንሰ-ሀሳባዊ ንድፍ (መርህ 6) | ደረጃ አዘጋጆች ይህንን ንድፍ በመጠቀም የተጠበቁ የጥበቃ ቦታዎች መረብ ለመፍጠር በብሔራዊና በክልል ደረጃ ተገቢውን መመሪያ ለማዘጋጀት ይጠቀማሉ። |
| አባሪ መ | በአገሪቱ ወይም በክልል ውስጥ ያሉ ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች ዝርዝር (መርህ 6) | ደረጃ አዘጋጆች በሀገሪቱ ወይም በክልሉ የሚገኙ ብርቅዬና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎችን ወቅታዊ ዝርዝር ለህዝብ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን ምንጮች ይዘረዝራሉ። |

| | | |
|---|---|---|
| አባሪ ረ | የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ክፍሎች (መርህ 7) | ደረጃ አዘጋጆች የዚህ አባሪ አግባብነት ያላቸውን ነገሮች በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዶችንይዘት መስፈርቶች ውስጥ መካተታቸውን፣ በመጠን ፣ ጥንካሬ እና በአደጋ የተመጣጠነ እና ከሀገር አቀፍ እና ከክልላዊ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ማዕቀፎች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። |
| አባሪ ሰ | የዕቅድ እና የክትትል ጽንሰ-ሐሳብ ማዕቀፍ (መርህ 7) | ደረጃ አዘጋጆች የተለያዩ የአስተዳደር ዕቅድ እና የክትትል ሰነዶችን የክለሳ ጊዜን ለመለየት ይህንን ንድፍ መጠቀም ይችላሉ ። |
| አባሪ ሸ | የክትትል መስፈርቶች (መርህ 8) | ደረጃ አዘጋጆች የዚህ አባሪ ተዛማጅነት ያላቸውን ነገሮች በክትትል ዕቅዶች ይዘት ውስጥ መካተታቸውን እና ከነባራዊ ሀገራዊ እና ክልላዊ የክትትል ሂደቶች ጋር ወጥነት ያለው እና በመጠን ፣ በጥንካሬ እና በአደጋ የተመጣጠነ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። |
| አባሪ ቀ | ለደረጃ አዘጋጆች ያልተነካ የደን መሬት ገጽታ ዋና ቦታዎች አመልካቾችን ማዘጋጃ መመሪያዎች (መርህ 9) | ያልተነካ የደን መሬት ገጽታዎች ላሏቸው አገሮች የደረጃ አዘጋጆች የሚከተሉትን መመሪያዎች ለመወሰን በዚህ አባሪ ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች ይጠቀማሉ፡ሀ)<br>የአብዛኛዎቹ ያልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎች ዋና አካባቢዎች የመሆን ገደብ፣ እና<br>ለ) ያልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎችለመገምገም እና ለመጠበቅ የሚረዱ አመላካቾች |
| አባሪ በ | ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስልቶች (መርህ 9) | ደረጃ አዘጋጆች ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች ለመጠበቅ የሚያስችሉ የአስተዳደር ስልቶችን ዝግጅት ለማሳወቅ ይህን አባሪ ግምት ውስጥ ያስገባሉ፡፡ |
| አባሪ ተ | የከፍተኛ ጥበቃ እሴቶች ማዕቀፍ (መርህ 9) | ደረጃ አዘጋጆች የሚከተሉተን የከፍተኛ ጥበቃ እሴቶች ማዕቀፎችን የጠቀማሉ። "Guidance for Standard Development Groups: Developing National High |

| | | |
|---|---|---|
| | | Conservation Value Frameworks" (FSC-GUI-60-009 V1-0 EN) and the "Template for National High Conservation Value Frameworks" (FSC-GUI-60-009a V1-0 EN) as the basis for the national *High conservation Values** framework. |
| አባሪ ቸ | የቃላት መፍቻ | ደረጃ አዘጋጆች በቃላት መፍቻ ውስጥ ያሉት ሁሉም ቃላት በቃላት አወጣጥ ውስጥ ወጥነት ያላቸው መሆናቸውን እና በሰያፍ እና ኮከብ ምልክቶች መያዛቸውን በሁሉም የደረጃ ክፍሎች ባሉ "አመልካችዎች" እና "ተጨማሪዎች" ማረጋገጥ አለባቸው። እንዲሁም IGIsን ለሀገራዊ ሁኔታዎች ስራ ላይ ስናውል፣ ደረጃ አዘጋጆች በቃላት መፍቻ ውስጥ ያሉትን ቃላቶች መጠቀምን ወይም በአዲስ የቃላት መፍቻ ቃላት መተካትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ። |

## አባሪ ሀ ቢያንስ የሚመለከታቸውን ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የያዘ ዝርዝር (መርህ 1)

**የሚከተለው በFSC-STD-60-004 (አለምአቀፍ አጠቃላይ አመላካቾች) ውስጥ**ቢያንስ የሚመለከታቸውን ህጎች፣ ደንቦች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የያዘ ዝርዝር **ነው።**

**ማስታዎሻ**፡- ይህ የሚመለከታቸው የህግ ድንጋጌዎች የተሟላ ዝርዝር ሆኖ የቀረበ አይደለም። ማንኛውም ተጨማሪ ህግ ተፈጻሚ ከሆነ፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጣቸው ድርጅቶች (Certificate Holders-CHs) እንዲሁ ማክበር አለባቸው።

| 1. ለመቁረጥ ህጋዊ መብቶች | |
|---|---|
| 1.1 የመሬት ይዞታ እና አስተዳደር መብቶች | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት 1994 ዓ.ም.፤ አዋጅ ቁ. 1223/2020 የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት፣ አስተዳደር እና አጠቃቀም፤ አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳትን ልማት ጥበቃና አጠቃቀምን ስለማቅረብ አዋጅ፤<br>አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135.12007 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለንብረት ማካካሻ ክፍያ ደንብ ለሕዝብ ዓላማዎች በተዘረጉ የመሬት ይዞታዎች ላይ የሚገኝ፤ አዋጅ ቁጥር. 197/2000 የኢትዮጵያ የውሃ ሃብት አስተዳደር |

| | |
|---|---|
| | አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1161/2019 ለሕዝብ ዓላማ ሲባል የመሬት ይዞታዎችን መውረስ፣ የካሳ ክፍያ እና መልሶ ማቋቋምን መወሰን፤ አዋጅ ቁጥር 240/2021፤ ደንብ ቁጥር 10/2021 የኦሮሚያ ክልል የጉምሩክ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ፤ አዋጅ ቁ. 89/1199 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር፤ አዋጅ ቁጥር 769/2012 የኢንቨስትመንት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 839/2004 የባህል ቅርሶችን ለሀገር አቀፍ እና ክልላዊ የባህል ቅርሶች ስለ ክፍፍል ስለማቅረብ፤ አዋጅ ቁጥር 575/2008 የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ምስረታ አዋጅ፤ የ1980 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 192 የደን እና የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ፤ አዋጅ ቁጥር 1236/2021 የተሻሻለው የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፤ ደንብ ቁጥር 151/2012 የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 147/2010 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/2005 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም፤ አዋጅ ቁ. 545/2007 ሙስናን በመከላከል እና በመዋጋት ላይ የአፍሪካ ህብረትን ስምምነትን ማፅደቂያ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 8911997 የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ። |
| 1.2 የኮንሴሽን ፍቃዶች | አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳትን ልማት ጥበቃና አጠቃቀምን ስለማቅረብ አዋጅ ቁጥር 8911997 የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 456/2005 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ። |
| 1.3 የአያያዝና ምርት የመሰብሰብ እቅድ | አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 8911997 የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 456/2005 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ |
| 1.4 ምርት የመሰብሰብ ፍቃድ | አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም |
| 2. ግብር እና ክፍያዎች | |
| 2.1 የሮያሊቲ እና ምርት የመሰብሰቢያ ክፍያዎች | አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ |
| 2.2 የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሌሎች የሽያጭ ግብሮች | አዋጅ ቁ. 1180/2020 የኢንቨስትመንት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 የሠራተኛ አዋጅ |
| 2.3 የገቢ እና የትርፍ ግብሮች | አዋጅ ቁ. 1180/2020 የኢንቨስትመንት አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 የሠራተኛ አዋጅ |

| | |
|---|---|
| 3. የእንጨት ምርት መሰብሰብ ተግባራት | |
| 3.1 የእንጨት ምርት መሰብሰብ ደንቦች | አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም |
| 3.2 ጥብቅ ቦታዎች እና ዝርያዎች | አዋጅ ቁጥር 993/2017 የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የፓሪስ ስምምነትን ለማጽደቅ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 634/2009 በዱር እንስሳት ፍልሰት ላይ ያለውን ስምምነት ለማጽደቅ አዋጅ። |
| 3.3 አካባቢያዊ መስፈርቶች | አዋጅ ቁጥር 482/2006 የጄኔቲክ ሀብቶችን፣ የማህበረሰቡን እውቀት እና የማህበረሰቡን መብት ተደራሽነት ለማቅረብ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 575/2008 የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ምስረታ አዋጅ ለደን እና የዱር እንስሳት ጥበቃ እና ልማት ለማቅረብ የወጣው አዋጅ ቁጥር 192 የ1980 ዓ.ም. አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 197/2000 የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር፤ አዋጅ ቁጥር 1090/2018 አደገኛ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ቁጥጥር አዋጅ፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 327/2014 የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ አካባቢ እና የደን ምርምር ተቋም ማቋቋሚያ ደንብ፤ አዋጅ ቁጥር 300/2002 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር፤ አዋጅ ቁጥር 674/2010 ፀረ ተባይ ምዝገባ እና ቁጥጥር አዋጅ፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጨረር መከላከያ አዋጅ ቁጥር 79/1993፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ 299/2002፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ ፖሊሲ፣ 1997 ዓ.ም፤ አዋጅ ቁጥር 29912002 የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ፡፡ |
| 3.4 ጤና እና ደህንነት | አዋጅ ቁጥር 690/2010 የማህበራዊ ጤና ኢንሹራንስ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 200/2000 የምግብ ጥራት ደረጃዎች ቁጥጥር፤ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 ሰራተኛ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 377/2003 ሠራተኛ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 513/2007 ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፤ አዋጅ ቁጥር 661/2009 የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር፤ የህዝብ ጤና አዋጅ ቁጥር 200/2000፡፡ |
| 3.5 ሕጋዊ የሥራ ቅጥር | አዋጅ ቁጥር 1156/2019 ሰራተኛ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 377/2003 ሠራተኛ አዋጅ፤ የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 515/2006 የፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1113/2019 የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 715/2011 የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ፤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008 |
| 4. የሶስተኛ ወገን መብቶች | |
| 4.1 የተለመዱ መብቶች | የክልሎች ባሕላዊ ሕጎች እና ፍርድ ቤቶች፤ አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፤ የኦሮሚያ ክልል ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ አዋጅ ቁጥር 240/2021፣ ደንብ ቁጥር 10/2021፤ አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ፤ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2012፤ አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ፤ |

| | |
|---|---|
| | አዋጅ ቁጥር 147/2011 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ |
| 4.2 ነፃና አስቀድሞ የተሰጠ ስምምነት* | የክልሎች ባሕላዊ ሕጎች እና ፍርድ ቤቶች፤ አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፤ የኦሮሚያ ክልል ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ አዋጅ ቁጥር 240/2021፣ ደንብ ቁጥር 10/2021፤ አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ፤ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2012፤ አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 147/2011 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ |
| 4.3 የአገሬው ተወላጆች መብቶች | የክልሎች ባሕላዊ ሕጎች እና ፍርድ ቤቶች፤ አዋጅ ቁጥር 85/2010 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፤ የኦሮሚያ ክልል ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ ደንብ አዋጅ ቁጥር 240/2021፣ ደንብ ቁጥር 10/2021፤ አዋጅ ቁጥር 66/2000 ታህሣሥ 24/2007 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ፤ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2012፤ አዋጅ ቁጥር 133/2006 የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጣ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 147/2011 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 482/2006 የጄኔቲክ ሀብቶችን፣ የማህበረሰቡን እውቀት እና የማህበረሰቡን መብት ተደራሽነት ለማቅረብ አዋጅ |
| **5. ንግድ እና** ትራንስፖርት<br>**ማስታዎሻ፡**- ይህ ክፍል ለደን አስተዳደር ስራዎች እንዲሁም ለምርት ማምረት ሂደት እና ለንግድ ስራ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ይሸፍናል። | |
| 5.1 የዝርያዎች፣ መጠኖች እና ጥራቶች ምደባ | አዋጅ ቁጥር 769/2012 የኢንቨስትመንት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም |
| 5.2 ንግድ እና ትራንስፖርት | አዋጅ ቁጥር 769/2012 የኢንቨስትመንት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም፤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008 |
| 5.3 የባህር ዳርቻ ንግድ እና የዝውውር ዋጋ | አዋጅ ቁጥር 1236/2021 የተሻሻለው የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 545/2007 ሙስናን በመከላከል እና በመዋጋት ላይ የአፍሪካ ህብረትን ስምምነትን ማፅደቂያ አዋጅ |
| 5.4 የጉምሩክ ደንቦች | የኢትዮጵያ ጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859-2014፤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008 |

| | |
|---|---|
| 5.5 በመጥፋት አደጋ ላይ የሚገኙ ዝርያዎች ዓለም አቀፍ ንግድ ስምምነት(CITES) | አዋጅ ቁጥር 575/2008 የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ምስረታ አዋጅ፤ የ1980 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 192 የደን እና የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ |
| **6. ተገቢ ጥንቃቄ / ተገቢ እንክብካቤ** | |
| 6.1 ተገቢ ጥንቃቄ / ተገቢ እንክብካቤ አሰራሮች | የኢትዮጵያ ጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859-2014፤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587-2008፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ |
| **7. የስርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች** | |
| | አዋጅ ቁጥር 1065/2018 የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር. 197/2000 የኢትዮጵያ የውሃ ሃብት አስተዳደር አዋጅ፤ የ1980 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 192 የደን እና የዱር እንስሳትን ጥበቃና ልማት አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 300/2002 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 513/2007 ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 541/2007 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ |

# አባሪ ለ ለሠራተኞች የሚያስፈልጉ ሥልጠናዎች (መርህ 2)

## *ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ*

*በዚህ አባሪ ውስጥ ያለው የስልጠና መስፈርቶች ዝርዝር የተዘጋጀው ከብሔራዊ ደረጃ ወይም ጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃ ትግበራ ጋር የተያያዙ የተወሰኑ የሥራ ኃላፊነቶች ላሏቸው ሠራተኞች ነው።*

*ሠራተኞቹ የሚከተሉትን ማድረግ እንዲችሉ:-*

1) የሚመለከታቸው የሕግ መስፈርቶችን ለማሟላት የደን ተግባራትን ማከናወን (መስፈርት 1.5)፤
2) የስምንቱን ዓለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት (ILO) ዋና የስራ ስምምነቶችን ይዘት፣ ትርጉም እና ተፈጻሚነት መረዳት (መስፈርት 2.1)፤
3) የፆታዊ ትንኮሳ እና የፆታ መድልዎ ሁኔታዎችን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ (መስፈርት 2.2)፤
4) አጠቃቀሙ ለጤንነት ስጋት እንዳይፈጥር ለማረጋገጥ አደገኛ ንጥረ ነገሮችን በአስተማማኝ ሁኔታ መያዝ እና ማስወገድ* (መስፈርት 2.3)፤
5) በተለይ አደገኛ ለሆኑ ወይም ልዩ ኃላፊነት ለሚጠይቁ ሥራዎች ኃላፊነትን መወጣት (መስፈርት 2.5)፤
6) የአገሬው ተወላጆች ከደን አስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ ሕጋዊና ልማዳዊ መብቶች ያሉባቸውን ቦታዎች መለየት (መስፈርት 3.2)፤
7) የ UNDRIP እና ILO ኮንቬንሽን 169 የሚመለከታቸው ነገሮች መለየት እና መተግበር (መስፈርት 3.4)፤
8) ለአገሬው ተወላጆች ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች መለየት እና አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለማስወገድ የደን አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ከመጀመሩ በፊት እነሱን ለመጠበቅ አስፈላጊውን እርምጃ መተግበር (መስፈርት 3.5 እና መስፈርት 4.7)፤
9) የአካባቢ ማህበረሰቦች ከደን አስተዳደር ተግባራት ጋር የተያያዙ ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸውን መለየት (መስፈርት 4.2)፤

10) የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማዎችንማካሄድ እና ተገቢውን የመከላከል እርምጃዎችን ማዘጋጀት (መስፈርት 4.5)፤
11) የFSC ሥርዓረ-ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ከሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ጥገና እና/ወይም ማሻሻል ጋር የተያያዙ ተግባራትን መተግበር (መስፈርት 5.1)፤
12) የፀረ ተባይ መድኃኒቶችን አያያዝ፡ አጠቃቀምእና ማከማቸት (መስፈርት 10.7)፤
13) የቆሻሻ ፍሳሾችን ለማጽዳት የሚያስችሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ (መስፈርት 10.12)፤

## አባሪ ሐ የጥበቃ ቦታ መረብ /Conservation Arera Network/ ጽንሰ-ሀሳባዊ ንድፍ (መርህ 6)




ሥዕላዊ መግለጫው በአካባቢ ጥበቃ ቦታ መረብ ውስጥ የተካተተው ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ በአጠቃላይ ከ 10% ዝቅተኛው መጠን ጀምሮ በመጠን ፣ የአስተዳደር ጥንካሬ እና/ወይም በመሬት ገጽታ ደረጃ የሥርዓተ ምህዳሮች ሁኔታ እና እሴት በእያንዳንዱ ጭማሪ እንደሚጨምር ያሳያል። ቀስቶቹና አቅጣጫቸው እነዚህን እድገቶች ይወክላሉ።

በስተቀኝ በኩል ያለው "የሥርዓተ-ምህዳሮች ያሉበት ሁኔታ/በመሬት ገጽታ ውስጥ ያለው እሴት" የተሰኘው አምድ ነባር ሥርዓተ-ምህዳሮች በመሬት ገጽታ ደረጃ የተጠበቁበትን ሁኔታ እና ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ለተጨማሪ ጥበቃ የሚያስፈልጉትን ተዛማጅ መስፈርቶች ያሳያል።
ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ መጠን የተሰኘው የግራው በኩል ያለው አምድ እንደሚያሳየው ለደን አስተዳደር የተለየው ቦታ ስፋት እየጨመረ ሲሄድ ለደን አስተዳደር የተለየው ቦታ ራሱ በመሬት ገጽታ ደረጃ ላይ እንደሚሆን እና ስለሆነም በዚያ መሬት ገጽታ ውስጥ በተፈጥሮ የሚከሰቱትን ሁሉም ሥርዓተ- ምህዳሮች ተግባራዊ ምሳሌዎችን የያዘ የጥበቃ አካባቢ መረብ እንደሚኖር ይጠበቃል።

## አባሪ መ (መርህ 6) በአገሪቱ ወይም በክልሎች ውስጥ ያሉ ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች ዝርዝር

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

ደረጃ አዘጋጆች ከመርህ 6 በተጨማሪ ለመርህ 8፣ ለመርህ 9 እና ለመርህ 10 አመላካቾችን ሲያዘጋጁ ይህንን አባሪ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

---

**ዕፅዋት**

**Hagenia abyssinica - African Redwood**
**Juniperus procera - African Pencil Cedar**
**Acacia bricchettiana**
**Acacia prasinata**
**Podocarpus falcatus**
**Taverniera abyssinica**
**Cordeauxia edulis**

**አጥቢዎች**

Capra walie - Walia Ibex
Tragelaphus buxtoni - Mountain Nyala
Tragelaphus scriptus - meneliki Menelik's bushbuck
Alcelaphus buselaphus swaynei - Swayne's Hartebeest
Canis simensis - Ethiopian Wolf
Chlorocebus djamdjamensis - Bale monkey
Cercopithecus mitis boutourlinii Boutourlini's - Blue Monkey
Graphiurus sp. "B"
Lophuromys brevicaudus - Short-tailed Brush-furred Rat
Lophuromys brunneus Thomas's - Ethiopian Brush furred Rat
Lophuromys chercherensis - Mount Chercher Brush-furred Rat
Lophuromys chrysopus - Ethiopian Forest Brush furred Rat
Lophuromys flavopunctatus - Ethiopian yellow-spotted Brush-furred Rat
Lophuromys melanonyx - Black-clawed Brush-furred Rat
Lophuromys menageshae - North Western Rift Brush-furred Rat
Lophuromys simeinsis
Lophuromys pseudosikapusi - Sheko Forest Brush-furred Rat
Mylomys rex - Ethiopian Mylomys
Mastomys awashensis - Awash Mastomys
Mus imberbis - Striped-back Mouse
Mus proconodon
Mus Mahomet - Mahomet Mouse
Mus sp. "Harena"
Mus sp.1 (M. cf. triton)

Nilopegamys plumbeus - Ethiopian Water Mouse
Otomys typus - Ethiopian Vlei Rat
Otomys fortiori - Ethiopian Vlei Rat
Otomys helleri - Ethiopian Vlei Rat
Otomys yalden - Ethiopian Vlei Rat
Otomys cheesmani - Ethiopian Vlei Rat
Otomys simiensis - Ethiopian Vlei Rat
Stenocephalemys sp. A
Crocidura thalia - Thalia's Shrew
Crocidura afeworkbekelei - Sanetti Shrew
Crocidura yaldeni - Beletta Shrew
Rodentia Nesomyidae
Dendromus lovati Lovat's - Climbing Mouse
Megadendromus nikolausi - Nikolaus's Mouse
Dendromus mystacalis - Chestnut Climbing Mouse
Arvicanthis abyssinicus - Abyssinian Grass Rat
Arvicanthis blicki - Blick's Grass Rat
Arvicanthis saturatus
Desmomys harringtoni - Harrington's Desmomys
Dasymys griseifrons - Grayish brown shaggy rat
Desmomys yaldeni - Yalden's Desmomys
Theropithecus gelada - Gelada
Colobus guereza gallarum - Neumann's black-and-white colobus
Eulipotyphla Soricidae
Crocidura baileyi - Bailey's Shrew
Crocidura bottegoides - Bale Shrew
Crocidura glassi - Glass's Shrew
Crocidura harenna - Harenna Shrew
Crocidura Lucina - Lucina's Shrew
Crocidura macmillani - Macmillan's Shrew
Crocidura phaeura - Guramba Shrew
Stenocephalemys albipes - White-footed Stenocephalemys
Stenocephalemys albocaudata - Ethiopian Narrow-headed Rat
Stenocephalemys griseicauda - Gray-tailed Narrow-headed Rat
Stenocephalemys “pseudogriseicauda”
Stenocephalemys ruppi - Rupp's Stenocephalemy
Spalacidae
Tachyoryctes macrocephalus - Big-headed Mole Rat
Chiroptera Vespertilionidae
Myotis scotti - Scott's Mouse-eared Bat
Plecotus balensis - Ethiopian Big-eared Bat
Scotophilus ejetai - Ejetas’s house mouse

Lagomorpha Leporidae
Lepus starcki - Ethiopian Highland Hare

አዕዋፍ
Harwood's Francolin - Pternistis harwoodi
Moorland Francolin - Scleroptila psilolaema
Blue-winged Goose - Cyanochen cyanoptera
Nechisar Nightjar - Caprimulgus solala
Brown-faced Go-away-bird - Corythaixoides personatus
Ruspoli's Turaco - Tauraco ruspolii
Spot-breasted Lapwing - Vanellus melanocephalus
Yellow-fronted Parrot - Poicephalus flavifrons
Ethiopian Bushcrow - Zavattariornis stresemanni
White-tailed Swallow - Hirundo megaensis
Abyssinian Catbird - Parophasma galinieri
Red-billed Pytilia - Pytilia lineata
Abyssinian Longclaw - Macronyx flavicollis
Yellow-throated Seedeater - Crithagra flavigula
Salvadori's Seedeater - Crithagra xantholaema
Ankober Serin - Crithagra ankoberensis
Ethiopian Siskin - Serinus nigriceps
Abyssinian Woodpecker - Dendropicos abyssinicus
Sidamo Lark - Heteromirafra sidamoensis

## አባሪ ሠ የደን አያያዝና አጠቃቀም እቅድ መሰረታዊ ነገሮች (መርህ 7)

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

*ደረጃ አዘጋጆች በብሔራዊ ደረጃዎች እና በጊዜያዊ ብሔራዊ ደረጃዎች ውስጥ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መሰረት አግባብነት ያላቸውን የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ መሰረታዊ ነገሮችን ዝርዝር ማካተት አለባቸው። ይህ ዝርዝር ከነባር ሀገራዊ እና ክልላዊ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ ማዕቀፎች ጋር መጣጣም አለበት።*

*ደረጃ አዘጋጆች ለተለያዩ የድርጅት ዓይነቶች የተለያዩ ዝርዝሮችን ማዘጋጀት ይችላሉ፣ ይህም ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ ጋር የሚመጣጠን ነው።*

---

1) የግምገማ ውጤቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡-
   ፩. በመርህ 6 እና በመርህ 9 ተለይቶ እንደተገለፀው የተፈጥሮ ሀብቶች እና የአካባቢ እሴቶች፤
   ሀ. በመርህ 6 ፣ መርህ 2 እስከ መርህ 5 እና በመርህ 9 ላይ ተለይቶ እንደተገለፀው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ሀብቶች እና ሁኔታዎች፤

ለ. በመርህ 9 ተለይቶ እንደተገለጸው ያልተነኩ ደኖች መሬት ገፅታዎች እና ዋና ቦታዎች፤

ሐ. በመርህ 3 እና በመርህ 9 ላይ ከተገኙት የመብት ባለቤቶች ጋር የተለዩት ነባር ባህላዊ ገጽታዎች፤

መ. በቦታው ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ማህበራዊ እና አካባቢያዊ አደጋዎች በመርህ 6፣ በመርህ 2 እስከ 5 እና በመርህ 9 የተገለጹ ናቸው፣ እና

ሠ. በመስፈርት 5.1 መሠረት የማስተዋወቂያ የይገባኛል ጥያቄዎች የሚቀርቡባቸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች መጠበቅ እና/ወይም ማሻሻል፡፡

2) የሚከተሉትን ፕሮግራሞች እና ተግባራት በተመለከተ፡-

፩. በመርህ 2 እንደተገለጸው የሰራተኞች መብት፣ በስራ ላይ ጤና እና ደህንነት፣ የፆታ እኩልነት፤

ሀ. በመርህ 3፣ መርህ 4 እና መርህ 5 የተገለጹት የአገሬው ተወላጆች፣ የማህበረሰብ ግንኙነቶች፣ የአካባቢው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት፤

ለ. በመርህ 1፣ መርህ 2 እና መርህ 7 እንደተገለፀው የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና አለመግባባቶች እና ቅሬታዎች ስለመፍታት፤

ሐ. በመርህ 10 ላይ እንደተገለጸው የታቀዱ የደን አያያዝ ተግባራት እና የጊዜ ሰሌዳዎች፣ ጥቅም ላይ የዋሉ የደን ልማት /ሲልቪካልቸር/ ሥርዓቶች፣ የተለመዱ የምርት መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና መሳሪያዎች፤

መ. በመርህ 5 ላይ እንደተገለጸው የእንጨት እና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችን የመሰብሰቢያ መጠን ምክንያታዊነት፡፡

3) ጥበቃ ለማካሄድ እና/ወይም ወደነበረበት ለመመለስ የሚወሰዱ እርምጃዎች፡-

፩. ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች እና መኖሪያዎቻቸው፤

ሀ. የውሃ አካላት እና የወንዝ ዳርቻዎች ዞኖች፤

ለ. የዱር አራዊት መተላለፊያዎች ጨምሮ የመሬት ገጽታ ግንኙነት፤

ሐ. በመስፈርት 5.1 ላይ እንደተገለጸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የ FSC የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ፤

መ. በመርህ 6 ላይ እንደተገለጸው የሚወክሉ ናሙና ቦታዎች፤ እና

ሠ. በመርህ 9 እንደተገለጸው ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች፡፡

4) በደን አያያዝ ተግባራት ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመገምገም፣ ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች፡-

፩. በመርህ 6 እና በመርህ 9 እንደተገለፀው የአካባቢ እሴቶች፤

፪. በመስፈርት 5.1 ላይ እንደተገለጸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የ FSC ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ፤

፫. ከመርህ 2 እስከ መርህ 5 እና መርህ 9 ላይ እንደተገለጸው ማህበራዊ እሴቶች እና ነባር ባህላዊ የመሬት ገፅታዎች፤ እና

፬. በመርህ 9 ተለይቶ እንደተገለጸው ያልተነኩ ደኖች መሬት ገፅታዎች እና ዋና ቦታዎች፡፡

5) በመርህ 8 ላይ የተገለጸውን የክትትል መርሃ ግብር መግለጫ፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

፩. እድገት እና ምርት፣ በመርህ 5 እንደተገለፀው፤

፪. በመስፈርት 5.1 ላይ እንደተገለጸው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የ FSC ሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ፤

ሀ. በመርህ 6 ላይ እንደተገለፀው የአካባቢ እሴቶች፤

ለ. በመርህ 10 ላይ እንደተገለጸው የአሠራር ተፅእኖዎች፤

ሐ. በመርህ 9 ላይ እንደተገለጸው ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች፤

መ. በመርህ 2 እስከ መርህ 5 እና መርህ 7 እንደተገለጸው በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ላይ የተመሰረቱ የክትትል ስርዓቶች የታቀዱ ወይም በሥራ ላይ ያሉ፤

ሡ. ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት እና የመሬት አጠቃቀም አከላለል የሚገልፁ ካርታዎች፤

ረ. የጥንቃቄ አካሄድን ለመተግበር ውጤታማነታቸውን ጨምሮ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች እና ዋና ቦታዎች ውስጥ የሚፈቀዱትን ማንኛውንም የልማት እና የመሬት አጠቃቀም አማራጮችን ለመገምገም እና ለመከታተል የሚያስችል ዘዴ መግለጫ፤

ሰ. ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ ለመተግበር ውጤታማነታቸውን ጨምሮ የነባር ባህላዊ የመሬት ገፅታዎች ላይ የሚፈቀዱትን ማናቸውንም የልማት እና የመሬት አጠቃቀም አማራጮች ለመገምገም እና ለመከታተል የሚያስችል ዘዴ መግለጫ፣ እና

ሸ. ግሎባል ፎረስት ዎች / Global Forest Watch / ወይም ይበልጥ ትክክለኛ የሆነ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ካርታ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን እና የመሬት አጠቃቀምን ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ላይ ያብራራል፣ ይህም ያልተነኩ የደን የመሬት ገፅታዎች ዋና ቦታዎችን ያጠቃልላል።

## አባሪ ረ የዕቅድ እና የክትትል ፅንሰ-ሀሳባዊ ማዕቀፍ (መርህ 7)

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

ደረጃ አዘጋጆች የዚህ አባሪ አግባብነት ያላቸውን ነገሮች በደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅዶችንይዘት መስፈርቶች ውስጥ መካተታቸውን፣ በመጠን ፣ ጥንካሬ እና በአደጋ የተመጣጠነ እና ከሀገር አቀፍ እና ከክልላዊ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድን ማዕቀፎች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

---

| የደን አያያዝና አጠቃቀም እቅድ ሰነድ ናሙና (ማስታወሻ፡ እነዚህ በSIR እና በስልጣን ይለያያሉ) | የደን አያያዝና አጠቃቀም እቅድ የማሻሻያ ጊዜ | ክትትል የሚደረግበት መሰረታዊ ነገር (ከፊል ዝርዝር) | የክትትል ጊዜ | ይህን መሰረታዊ ነገር የሚከታተለው ማነው? (ማስታወሻ፡ እነዚህ በSIR እና በስልጣን ይለያያሉ) | የ FSC መርህ / መስፈርት |
|---|---|---|---|---|---|
| የቦታ ፕላን (የምርት መሰብሰቢያ ፕላን) | ዓመታዊ | ጅረት መሻገሪያዎች | በመስክ ላይ እና በየዓመቱ | ስራውን የሚተገብሩ ሰራተኞች | መር10 |
| | | መንገዶች | በመስክ ላይ እና በየዓመቱ | ስራውን የሚተገብሩ ሰራተኞች | መር10 |
| | | የማቆያ ፓችስ | ዓመታዊ ናሙና | ስራውን የሚተገብሩ ሰራተኞች | መር6፣ መር10 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብርቅዬ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች | በየዓመቱ | አማካሪ የስነ-ህይወት ባለሙያ | መር6 |
| | | ዓመታዊ ምርት መሰብሰቢያ ደረጃዎች | በየዓመቱ | ዝቅተኛ ጥግግት ያለው ደን /woodland/ ስራ አስኪያጅ | መስ5.2 |
| | | የነፍሳት በሽታ ወረርሽኝ | ዓመታዊ ናሙና | አማካሪ የስነ-ህይወት ባለሙያ / የደን ሚኒስቴር | |
| በጀት ማውጣት | ዓመታዊ | ወጪዎች | በየዓመቱ | ዋና የሒሳብ ባለሙያ | መር5 |
| | | ለአካባቢው ኢኮኖሚ ሚያበረክተው አስተዋፅኦ | በየሩብ ዓመቱ | ዋና ስራ አስኪያጅ | መር5 |
| የተሳትፎ እቅድ | ዓመታዊ | የቅጥር ስታቲስቲክስ | በየዓመቱ | ዋና ስራ አስኪያጅ | መር3፣ መር4 |
| | | ማህበራዊ ስምምነቶች | በየዓመቱ ወይም እንደ ተሳትፎ እቅድ ስምምነት | የማህበራዊ ዘርፍ አስተባባሪ | መር3፣ መር4 |
| | | ቅሬታዎች | በመካሄድ ላይ | የሰው ኃይል አስተዳደር | መር2፣ መር3፣ መር4 |
| የ5-አመት የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ | 5 ዓመት | የእያንዳንዱ የዱር እንስሳት እና ዕፅዋት ብዛት | የሚወሰን | የአካባቢ ሚኒስቴር | መር6 |
| | | ደቃቅ ያልሆነ የእንጨት ቁርጥራጮች | በየዓመቱ | የደን ሚኒስቴር | መር10 |
| | | በራሱ የሚበቅል / ዳግም ብቅለት | ዓመታዊ ናሙና | | |
| ዘላቂ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ | 10 ዓመት | የዕድሜ ምድብ ስርጭት፣ የመጠን ምድብ ስርጭት | 10 ዓመት | የአካባቢ ሚኒስቴር | መር6 |
| | | ለ10 አመት የሚፈቀድ አመታዊ ቆረጣ | በየዓመቱ፣ 10 ዓመት | የደን ሚኒስቴር / ዝቅተኛ ጥግግት ያለው ደን | መስ5.2 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | /woodland/ ስራ አስኪያጅ | |
| የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ማረጋገጫ ሰነድ | 5 ዓመት | ከማረጋገጫ እና ማፅደቂያ በፊት | ከማረጋገጫ እና ማፅደቂያ በፊት | ዋና አስተዳዳሪ | FSC-PRO-30-006 |

## አባሪ ሰ ለክትትል የሚያስፈልጉ ነገሮች (መርህ 8)

### ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ

የክትትል ውጤቶች በአዲሱ የክትትል ዑደት ዕቅድ መጀመሪያ ላይ ውሳኔ ላይ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የክትትል ስራ በአመራር ዕቅድ ዑደቶች ውስጥ ይዘጋጃል። መርህ 7፣ አባሪ ረ ተመልከቱ፡፡

ደረጃ አዘጋጆች የክትትል ሂደቶች ወጥነት ያለቸው እና በጊዜ ሂደት የሚደጋገሙ፣ ለውጦችን በጊዜ ሂደት ለመለካት ተስማሚ የሆኑ እና አደጋዎችን እና ተቀባይነት የሌላቸውን ተፅእኖዎችን ለመለየት ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አመልካቾችን ማዘጋጀት አለባቸው። ክትትሉ ለደን አስተዳደር የተለየ ቦታ ሁኔታን የሚመለከቱ ለውጦችን ስራው ከመጀመሩ በፊት እና በኋላ የሉ ክንውኖችን ማካተት አለበት፡፡ ይህ የሚያመለክተው የመነሻ መረጃ መኖሩን ነው።

ለመስፈርት 8.1 እና 8.2 ከሚደረገው ክትትል በተጨማሪ፣ ደረጃ አዘጋጆች በብሔራዊ ደረጃዎች እና ጊዜያዊ ብሄራዊ ደረጃዎች ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አግባብነት ያላቸውን መሰረታዊ ነገሮች ያካተተ ዝርዝር የክትትል መስፈርቶች ማካተት አለባቸው። ይህ ዝርዝር ከብሄራዊ እና ክልላዊ የክትትል ማዕቀፎች ጋር መጣጣም አለበት።

የደረጃ አዘጋጆች ለተለያዩ የድርጅት ዓይነቶች የተለያዩ ዝርዝሮችን ማዘጋጀት ይችላሉ፣ ይህም ከአስተዳደር ተግባራት መጠን፣ ጥንካሬ እና አደጋ ጋር የሚመጣጠን ነው።

---

1) በ 8.2.1 ላይ የተጠቀሰው ክትትል የአስተዳደር ተግባራት በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ለመለየት እና ለመግለጽ በቂ ነው፣ አስፈላጊ ከሆነም የሚከተሉትን ጨምሮ፡
  ፩. የዳግም ብቀለት ተግባራት ውጤቶች (መስፈርት 10.1)፤
  ሀ. ለሥነ-ምህዳር ተስማሚ የሆኑ ዝርያዎችን ለዳግም ብቀለት መጠቀም (መስፈርት 10.2)፤
  ለ. ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ እና ውጭ ከየትኛውም የባዕድ ዝርያ ጋር የተያያዙ ወራሪነት ወይም ሌሎች አሉታዊ ተጽእኖዎች (መስፈርት 10.3)፤
  ሐ. 'በዘረመል የተሻሻሉ ተህዋሲያን' አጠቃቀምን በተመለከተ ጥቅም ላይ እንዳልዋሉ ለማረጋገጥ (መስፈርት 10.4)፤
  መ. የደን ልማት /ሲልቪካልቸር/ ተግባራት ውጤቶች (መስፈርት 10.5)፤
  ሠ. ማዳበሪያዎች በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ (መስፈርት 10.6)፤
  ረ. ፀረ-ተባይ መድኃኒቶችን መጠቀም የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ (መስፈርት 10.7)፤
  ሰ. ከስነ-ህይወታዊ ቁጥጥር አድራጊዎች መጠቀም የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ (መስፈርት 10.8)፤
  ሸ. ከተፈጥሮ አደጋዎች የሚመጡ ተፅዕኖዎች (መስፈርት 10.9)፤

ቀ. የመሠረተ-ልማት ልማት፣ የትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች እና የደን ልማት /ሲልቪካልቸር/ ብርቅየ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች፣ መኖሪያ ቦታዎች፣ ሥርዓተ ምህዳሮች፣ የመሬት ገጽታ እሴቶች፣ ውሃ እና አፈር ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ (መስፈርት 10.10)፤

በ. የእንጨት መሰብሰብ እና ማውጣት በእንጨት ነክ ባልሆኑ የደን ምርቶች ፣ በአካባቢያዊ እሴቶች ፣ ለገቢያ የሚውል ተረፈ ምርት እና በሌሎች ምርቶች እና አገልግሎቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ (መስፈርት 10.11) ፤ እና

ተ. ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ (መስፈርት 10.12)፡፡

2) በ 8.2.1 ውስጥ ያለው ክትትል የደን አያያዝ ተግባራት ማህበራዊ ተጽእኖዎችን ለመለየት እና ለመግለጽ በቂ ነው፤ አስፈላጊ ከሆነም የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

፩. ሕገወጥ ወይም ያልተፈቀዱ ድርጊቶች ማስረጃ (መስፈርት 1.4)፤

ሀ. ከሚመለከታቸው ህጎች፣ የአካባቢ ህጎች፣ የጸደቁ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የግዴታ የአሰራር ደንቦች ጋር መጣጣም (መስፈርት 1.5)፤

ለ. አለመግባባቶች እና ቅሬታዎች መፍታት (መስፈርት 1.6፣ መስፈርት 2.6፣ መስፈርት 4.6)፤

ሐ. የሰራተኞችን መብቶች በተመለከተ ፕሮግራሞች እና ተግባራት (መስፈርት 2.1)፤

መ. የፆታ እኩልነት፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና የፆታ መድልዎ (መስፈርት 2.2)፤

ሠ. የሙያ ጤና እና ደህንነትን የሚመለከቱ ፕሮግራሞች እና ተግባራት (መስፈርት 2.3)፤

ረ. የምንዳ ክፍያ (መስፈርት 2.4)፤

ሰ. የሰራተኞች ስልጠና (መስፈርት 2.5)፤

ሸ. ፀረ-ተባይ መድሃኒቶች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ቦታ፣ ለፀረ-ተባይ መድሃኒቶች የተጋለጡ ሰራተኞች ጤና (መስፈርት 2.5 እና መስፈርት 10.7)፤

ቀ. የአገሬው ተወላጆች እና የአካባቢ ማህበረሰቦች እና ህጋዊ እና ልማዳዊ መብቶቻቸውን መለየት (መስፈርት 3.1 እና መስፈርት 4.1)፤

በ. አስገዳጅ ስምምነቶች ውስጥ ያሉ ውሎችን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ (መስፈርት 3.2 እና መስፈርት 4.2)፤

ተ. የአገሬው ተወላጆች እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች (መስፈርት 3.2፣ መስፈርት 3.3 እና መስፈርት 4.2)፤

ቸ. ለአገሬው ተወላጆች እና ለአካባቢው ማህበረሰቦች ልዩ ባህላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች ጥበቃ (መስፈርት 3.5 እና መስፈርት 4.7)፤

ኀ. ነባር ባህላዊ ገጽታዎች እና ከእነሱ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ለአገሬው ተወላጆች አስፈላጊ የሆኑ እሴቶች መኖራቸው (መስፈርት 3.1፣ መስፈርት 3.5)፤

ነ. ባህላዊ እውቀት እና አእምሯዊ ንብረት አጠቃቀም (መስፈርት 3.6 እና መስፈርት 4.8)፤

ኘ. የአካባቢ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት (መስፈርት 4.2፣ መስፈርት 4.3፣ መስፈርት 4.4፣ መስፈርት 4.5)፤

አ. የተለያዩ ጥቅሞችን እና/ወይም ምርቶችን ማምረት (መስፈርት 5.1)፤

ከ. የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶችን መጠበቅ እና/ወይም ማሻሻል (መስፈርት 5.1)፤

ኸ. የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶችን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል ተግባራት፤

ወ. እንጨት እና እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች ዓመታዊ ትክክለኛ እና ታሳቢ ምርት ሲነጻጸር (መስፈርት 5.2)፤

ዐ. የአካባቢ ምርት የማምረት ሂደት፣ የአካባቢ አገልግሎቶች እና የአካባቢያዊ የተጨማሪ እሴት ማምረቻ አጠቃቀም (መስፈርት 5.4)፤

ዘ. የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ዘላቂነት (መስፈርት 5.5) ፤ እና

ዠ. ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች 5 እና 6 በመስፈርት 9.1 ውስጥ ተለይተው የታወቁ ፡፡

3) የ 8.2.2 የክትትል አሰራሮች የአካባቢ ሁኔታዎችን ለውጦች ለመለየት እና ለመግለጽ በቂ ናቸው፣ አስፈላጊ ከሆነም የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

፩. የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶችን መጠበቅ እና/ወይም ማሻሻል (መስፈርት 5.2) (ድርጅቱ የFSC ስነ-ምህዳር አገልግሎቶችን የይገባኛል ጥያቄዎችን ሲጠቀም)፤
፪. የካርበን ማመቅ እና ማከማቸት ጨምሮ የአካባቢ እሴቶች እና የሥርዓተ ምህዳር ተግባራት (መስፈርት 6.1)፤ በአካባቢያዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመከላከል፣ ለመቀነስ እና ለመጠገን ተለይተው የታወቁ እና የተተገበሩ ድርጊቶች ውጤታማነትን ጨምሮ (መስፈርት 6.3)፤

ሀ. ብርቅዬ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች፣ እና እነሱን እና መኖሪያዎቻቸውን ለመጠበቅ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.4)፤

ለ. ተወካይ ናሙና ቦታዎች እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ ድርጊቶች ውጤታማነት (መስፈርት 6.5)፤

ሐ. በተፈጥሮ የተገኙ ነባር ዝርያዎች እና የስነ-ህይወት ብዝሀነት እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.6)፤

መ. የውሃ ፍሰቶች፣ የውሃ አካላት፣ የውሃ መጠን እና የውሃ ጥራት እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.7)፤

ሠ. የመሬት ገፅታ እሴቶች እና እነሱን ለመጠገን እና/ወይም ወደነበሩበት ለመመለስ የተተገበሩ እርምጃዎች ውጤታማነት (መስፈርት 6.8)፤

ረ. የተፈጥሮ ደንን ወደ ሰው ሰራሽ ደኖች ወይም ደን ያልሆነ መለወጥ (መስፈርት 6.9)፤

ሰ. ከ 1994 በኋላ የተተከሉ የሰው ሰራሽ ደኖች ሁኔታ (መስፈርት 6.10)፤ እና

ሸ. በመስፈርት 9.1 ውስጥ ተለይተው የታወቁ ከ1 እስከ 4 ያሉት ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶች እና እነሱን ለመጠበቅ እና/ወይም ለማሻሻል የተተገበሩ ድርጊቶች ውጤታማነት፡፡

## አባሪ ሸ ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታ ዋና ቦታዎች የሚመለከቱ አመልካቾችን ለማዘጋጀት ለደረጃ አዘጋጆች የተሰጠ መመሪያ (መርህ 9)

*ሀ. ለብዙሃኑ የተሰጠ ገደብ*

የብዙሃን ገደብ ትርጉም ከጥር 1 ቀን 2017 እአአ ጀምሮ 80% የሚሆነው አጠቃላይ ያልተነካ የደን መሬት ገጽታ ቦታ ለደን አስተዳደር በተለየ ቦታ ውስጥ ሲገኝ ነው። ብዙሃን የሚለው ያልተነካ የደን መሬት ገፅታ ትርጉምን ያሟላል ወይም ይበልጣል፡፡

ለብዙሃኑ የተሰጠ ገደብ ከ 80% በታች ሊመሰረት ይችላል፣ ይህም ከፍተኛ መጠን ያለው የጥበቃ ውጤት በብሔራዊ ወይም ኢኮ-ክልላዊ ታሳቢዎች ላይ ሲያሳካ እና ያልተነካ የደን መሬት ገፅታ ትርጉምን ሲያሟላ ወይም ሲበልጥ ነው።

ከ 80% በላይ የሆኑ ገደቦች በሀገሮች እና/ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች /eco-regions/ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች በአንጻራዊ ሁኔታ ውስን እና/ወይም የተበታተኑ ሲሆኑ እና/ወይም ከ2000 ወዲህ ከፍተኛ መጠን ያለው ያልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎች የጠፋባቸው አካባቢዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

ደረጃ አዘጋጆች በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች /eco-regions/ የተለየ ለብዙሃኑ የተሰጠ ገደብ ሲያዘጋጁ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

1) ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች አንጻራዊ ብዛት እና በሰው ተግባራት ምክንያት ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች የመጐሳቆል አደጋ ደረጃን የሚያሳይ ማስረጃ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

ሀ. በብሔራዊ ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች /eco-regions ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታዎች አንጻራዊ እጥረት፡፡ ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታዎች በጣም ሲጠፉ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

ለ. ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ በሰው ልጅ ተግባራት የተጐሳቆሉ ብሔራዊ ወይም ሥነ ምህዳራዊ ክልሎች /eco-regions ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታዎች መጠን እና ስለሆነም የተመናመኑ፣ አልፎ አልፎ የሚገኙ ወይም የተበታተኑ ናቸው፡፡ ያልተነኩ የደን የመሬት ገጽታዎች በፍጥነት ሲጎሳቆሉ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

ሐ. ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* በፍጥነት እንዲጎሳቆሉ ምክንያት የሆኑት የሰው ልጆች እንቅስቃሴ አይነቶች፤ የሰዎች ተግባራት ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* አለመነካት ይበልጥ የሚጎዱ ከሆነ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

መ. በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ምክንያት ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* የመጉዳት አደጋ፡፡ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* ላይ የሚጋለጠው አደጋ እየጨመረ በሄደ መጠን የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

ሠ. የተለያዩ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎችን* ከብደት በማወዳደር ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ዋና ቦታዎች* የተጠበቁበት መጠን እና አንጻራዊ ዘላቂነት፡፡ ጥበቃ* ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ዋና ቦታዎች* አንድነት እና ሌሎች ሥነ ምህዳራዊ ባህሪያትን መጠበቅ ወይም ማሻሻል አለበት*፡፡ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ጥበቃ* ይበልጥ ዘላቂ ከሆነ የብዙሃን ገደብ ዝቅተኛ ይሆናል፤

ረ. ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* ውስጥ እና በአቅራቢያ ያሉ ሥነ ምህዳራዊ እሴቶች ተፈጥሮ እና ስርጭት፡፡ የእነዚህ እሴቶች ክምችት ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* ውስጥ እና በአቅራቢያቸው የበለጠ ከሆነ፣ የብዙሃን ገደብ ከፍተኛ ይሆናል፤

ሰ. ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች ውስጥ እና አጠገብ የባህላዊ እሴቶች እና ህጋዊና ልማዳዊ መብቶች* ተፈጥሮና ስርጭት፤ እና

ሸ. ከተጎዱት የመብት ባለቤቶች*፣ የተጎዱ* እና ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት* ጋር ባህሉን የጠበቀ* ተሳትፎ* ውጤቶች፡፡

ለ. ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎች* ለመገምገም እና ለመጠበቅ አመልካቾችን* ማዘጋጀት

ደረጃ አዘጋጆች ለመስፈረት 9.1 እና 9.2 አመላካቾችን በሚያዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

ለብዙሃኑ እና ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎችን እንደ ዋና ቦታዎች ለመለየት፣ ለመገምገም እና ለመጠበቅ ውጤቱ በብሔራዊ ወይም በሥነ ምህዳራዊ ክልሎች /eco-regions/ ደረጃ ተገቢ የሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች መሆን አለባቸው፡፡

ዋና ቦታዎች አለመነካታቸው ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተግባራት እንዲጠበቁ የታሰቡ ሲሆን ይህም የንግድ ሥራን ለማካሄድ የሚውል የእንጨት ማውጣት፣ የማዕድን ማውጣት እንዲሁም የመንገድ፣ የግድብ እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ይጨምራል።

1. ዋና ቦታዎችን ለመለየት እና ለመሰየም የተዘጋጁ አመልካቾች የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡-

   ሀ. የተጎዱትን የመብት ባለቤቶች ነፃ ቅድመ እና መረጃ የተገኘበት ስምምነት የማግኘት መብት ማክበር (መስፈርት* 3.1 እና 4.1) ፤

   ለ. የተጎዱት የመብት ባለቤቶች ዋና ቦታዎችን የመጠቀም ሕጋዊና የተለመዱ መብቶች እንዲከበሩ ማረጋገጥ፤

   ሐ. ዋና ቦታዎች በሥነ ምህዳራዊ ሁኔታ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ፣ ተያያዥነት ያላቸው እና ጥቅጥቅ ያልተነኩ የደን መሬት ገፅታዎችን ክፍሎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤

   መ. የዋና ቦታዎች ቅርፅ የውስጥ መኖሪያ ቦታዎቻቸውን ከፍ ለማድረግ የተነደፈ መሆኑን ማረጋገጥ፤

   ሠ. ዋና ቦታዎች በስፋት የተያያዙ እና ያልተለወጡ የደን ቦታዎች ላይ ለሚገኙ ብርቅዬ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ እና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎች እና ሌሎች የዱር እንስሳትና ዕፅዋት መኖሪያ ቦታዎችን እንደያዙ ማረጋገጥ፤

   ረ. ዋና ቦታዎች ለደን አስተዳደር በተለየው ቦታ ውስጥም ሆነ በአቅራቢያቸው ያሉ ዋና ቦታዎች መካከል ግንኙነታቸው መጠበቁን ወይም መመለሱን ማረጋገጥ፤ እና

   ሰ. ዋና ቦታዎች ከ50 ሺህ ሄክታር በታች እንዳይሆኑ ማረጋገጥ።

2. ዋና ቦታዎችን ለመጠበቅ የተዘጋጁ አመልካቾች የሚከተሉትን ያረጋግጣሉ፡-
ሀ. የተጎዱ የመብት ባለቤቶች ዋና ቦታዎች የመጠቀም ሕጋዊና የተለመዱ መብቶች ተከብረዋል፤
ለ. የአገሬው ተወላጆች፣ ለብዙ ዓመታት ለብቻቸው የተውሰነ ቦታ የሚኖሩ ሕዝቦች እና በደን ላይ ጥገኛ የሆኑ ማህበረሰቦች ከዋና ቦታዎች ጥበቃ ጋር የሚጣጣሙ አማራጭ የአስተዳደር እና የጥበቃ ተግባራትን ለመቅረፅ እና ለመተግበር ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፤
ሐ. በዋና ቦታዎች ውስጥ ህገ ወጥ የዛፍ መቁረጥና ማጓጓዝ፣ በነፋስ መውደቅ፣ መጎሳቆል /degradation/ እና ሌሎች የዳርቻ ውጤት ተፅዕኖዎች መከላከል፤
መ. የመንገድ ግንባታ አስተዳደር እና ከዋና ቦታዎች አጠገብ ያሉ ሌሎች ተግባራት ጥንካሬ በዋና ቦታዎች ውስጥ ህገወጥ የዛፍ መቁረጥና ማጓጓዝ፣ በነፋስ መውደቅ፣ መጎሳቆል/degradation እና ሌሎች የዳርቻ ውጤት ተፅዕኖዎች ለመከላከል፤ እና
ሠ. በዋና ቦታዎች ውስጥ የዳርቻ ውጤት ተፅዕኖዎች ለመከላከል የመንገድ ግንባታ እና ሌሎች ተግባራት የሚተዳደሩባቸው ዋና ቦታዎች አጠገብ የሚገኙ ተስማሚ የመከላከያ ዞኖች ስፋት መለየት።

3. ለዋና ቦታዎች ጥበቃ የተዘጋጁ አመልካቾች ዋና ቦታዎች በአለመነካታቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተግባራት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የንግድ ሥራን ለማከናወን የሚያስችሉ ዛፎችን መቁረጥና ማጓጓዝ፣ ማዕድን ማውጣት፣ እና የመንገድ፣ የግድብና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን መገንባት ጨምሮ ፍፁም ያልተነኩ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ፍፁም ያልተነኩ ዋና ቦታዎችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ የአስተዳደር ስራዎች ምሳሌዎች፤ የጥበቃ ቀጠናዎች እንዲሁም የሕግ ጥበቃ ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው የሚችሉ ቦታዎችን ለምሳሌ የተተው ቦታዎች፣ መጠባበቂያ ቦታዎች፣ ውሳኔ ያላገኙ ቦታዎች፣ የማህበረሰብ መጠባበቂያ ቦታዎች እና ነባር የተጠበቁ ቦታዎችያካትታሉ።
4. ለያልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎች የተዘጋጁ አመልካቾች እንደ ዋና ቦታዎች ያልተሰየሙ ያልተነኩ የደን መሬት ገጽታዎች ክፍሎች ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ምድብ 2 ለመጠበቅ እና/ወይም ለማቆየት የሚያገለግሉ መሆናቸውን ያብራራሉ።

## አባሪ ቀ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስልቶች (መርህ 9)

ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ ስትራቴጂዎች የግድ የምርት መሰብሰብን ሊከለክሉ አይችሉም። ይሁን እንጂ አንዳንድ ከፍተኛ የጥበቃ እሴቶችን ለመጠበቅ ብቸኛው መንገድ እነሱን የሚደግፍ ከፍተኛ የጥበቃ እሴት ያለው ቦታን በመጠበቅ ነው።

